### የኢትዮጵያ

# ጥንታዊ ምሳሌ

(በአማርኛ)

ግርማዊ ን. ነ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ
በነገሡ በ፲፮ኛው ዓመት።

በ፲፱፻፴፱ ዓመተ ምሕረት
ከሊቀ መዘምራን ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ
ተጻፈ።

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

# የኢትዮጵያ ጥንታዊ ምሳሌ

(በአማርኛ)

========

ግርማዊ ን. ነ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ

በነገሡ በ፴፰ኛው ዓመት።

==========

በ፲፱፻፶፱ ዓመተ ምሕረት

ከሊቀ መዘምራን ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ

ተጻፈ።

============

በማኅበረ ሐዋርያት ማተሚያ ቤት በኮከብ ጽባሕ ታተመ።

አሥመራ።

ይህ ሞገስ ነው ትሉኝ ይሆናል ግን ምሳሌው እንጂ ሞገስ አይደለሁም። ሞገስ ፩ድ ነው እኔ ግን አንድም ብዙም ነኝ። ሞገስ ካንድ ቦታ ካንድ ቤት ብቻ ነው የሚገኘው። እኔ ግን በየትም ቦታ እገኛለሁ። ሞገስ ዛሬ አለ ነገ እንጃ ተነገ ወድያ ግን በእርግጥ የለም። እኔ ግን ዓለም እስካለ ድረስ ከናንተው ጋር አለሁ። ይሁን እንጂ እርሱ ሲታመም የማይታመም እርሱ ቢሞት የማይሞት አንድ ነገር በአደራ ሰጥጥቶኛል። እሱም በ፫ ቀለሞች የቆመ «ስሙ» ነው እስካለሁ ድረስ አደራዬን እጠብቃለሁ እያንዳንዱ ሰው ሁሉ የሀገሩን ምሳሌና ተረት ማወቅ ይኖርበታል።

የአንድ ሀገር ሕዝብ ጠባይ ጭውነት ሥልጣኔ ጠቅላላ ሁኔታና ይዘታ የሚገመተውና የሚመዘነው በምሳሌውና በተረቱ ነው።

እንደዛሬ የየክፍለ ዓለሙ ሕግጋንትችና ደምቦች ተቀላቅለው የሀገራችንን ሕግ ሳያሳክሩ አባቶቻችን ሲሚገቱና ሲፈርዱ ከምሳሌዎችና ከተረቶች እየጠቀሱ ነበር።

አሁንም ከግብር ማዋሉና አለማዋሉ እንጂ አይቀርም ይኸውም ሕጎቻችን በምሳሌዎቻችን ላይ እንደተመሠረቱ ያስረዳል።

የአገር ምሳሌ ከአሁንም በፊት ሌሎችም ጽፈዋል ቢሆንም እላይ እንደገለጥኩት የሀገር ጠቅላላው ሕግ ወግ ታሪክና ቋንቋን አጣምሮ የያዘ ቅርስ ስለሆነ አንድ ጊዜ ተጽፎ ይበቃል አይባልም። ባንድ ሁለት ሰዎች ብቻ ተጽፎም የሚፈጸም አይደለም። ብዙ ጊዜና ዘመን በየጊዜው እየሰሙ ማጠራቀም ያስፈልጋል። ለምሳሌ አንዱ የሰማውን አንዱ አይሰማውም በአንዱ ክፍለ ግዛት የሚነገረው ባንዱ ያልተሰማ ይሆናል። አንዱ ያልጻፈውን አንዱ ይጽፈዋል አንዱ ችላ ያለውን አንዱ አያልፈውም። በዚህ መሠረት ሌሎች ያልጻፉዋቸው እኔ የጻፍኩዋቸው አሉ ሌሎቹ ከጻፉዋቸው እኔ የዘለልኩዋቸውም አሉ።

ስጽፈውና ሳጠራቅመው ከኔ በፊት ከጻፉ ሰዎች መጻሕፍትና ከብዙ ጊዜ ጀምሬ ከሽማግሌዎች እየሰማሁም ነው። እንደ ዛሬ አታሚ መኪናዎች ሳይኖሩ ከ፴ ዓመት በፊት የተከበሩ አዝማች ገብረ ሚካኤል ግርሙ ዘባራቂት በእጅ የጻፉዋቸው የአማርኛና የትግርኛ መጻሕፍት ስላሉ ከነዚሁ መጻሕፍት የሚበቃኝን ያህል ጽፌ አለሁ።

ስለዚህም አዝማች ገብረ ሚካኤል ግርሙ ዘበራቂነትን ሳላመሰግናቸው አላልፍም። ከራሴ ያሻሻልኩት መሻሻልና የመሰልኩትም ቢኖር የጥንቶቹን መሠረት አልቀቅሁም። ትግርኛና አማርኛ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ስለሆነ የገጠመልኝን በግጥም ያልገጠመልኝን በስድ ንባብ አጉራርሼዋለሁ። አጻጻፉ ከ፬ የተከፈለ ነው ፩ኛ ግጥም ምሳሌ ፪ኛ ስድ ምሳሌ ፫ኛ አንድ አንድ ሽማግሌዎች ከተናገርዋቸው ምርጥ ቃላት ፬ኛ እንቆቅልሽ ሲሆን ጠያቂና መላሽ በመሆን እየተነገረ ብዙ ጥልቅ ምሥጢር ይገኝበታል።

ይኸውም ከ‹ሀ› ጀምሮ እስከ ‹ፈ› ባሉት ፊደሎች ተራ ሲሆን ሀ-ሐ-ኀ-አ-ዐ-ጸ-ፀ እነዚህ ፊደሎች ድምፃቸው ፩ ስለሆነ እንደ አንድ ፊደል በማድረግ የቀሩት እንደየ ተራቸው ተጽፈዋል። ግጥሙን ስድ ንባብ በቅደም ተከተል አድርጌ ስጽፍ እንቆቅልሹን ጥያቄው በአንድ ወገን መልሱ በአንድ ወገን አድርጌዋለሁ።

እላይ እንዳልኩት ከአሁን በፊት የተጻፉ መጻሕፍተ ምሳሌ መኖራቸው ሲታወቅ ወደዚህ ክፍለ ግዛት በብዛት ስላልመጡ አብዛኛው የኤርትራ ሕዝብ በተለይ ተማሪዎቹ እንዲጠቀሙበት በማሰብ ሲሆን ለአስተማሪዎቹም ማስታወሻ ይሆን ይሆናል እላለሁ።

አነስተኛው ወንድማችሁ

ሊቀ መዘምራን ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ።

# ማውጫ

ሀ - ሂ - ሂ - ሃ - ሄ - ህ - ሆ ..... 5
ስድ ምሳሌ። ..... 5
ስድ ምሳሌ። ..... 6
ለ - ላ - ል- ሎ ..... 6
ስድ ምሳሌ። ..... 8
መ - ሙ - ሚ - ማ -ሜ - ም - ሞ ..... 8
ስድ ምሳሌ። ..... 10
ሠ - ሥ ..... 10
ስድ ምሳሌ። ..... 10
ሰ - ሲ - ሳ - ሴ - ስ ..... 11
ስድ ምሳሌ። ..... 13
ሸ - ሹ - ሻ - ሽ - ሾ ..... 13
ስድ ምሳሌ። ..... 13
ረ- ሩ - ራ - ሬ ..... 14
ስድ ምሳሌ። ..... 14
ቀ - ቁ - ቂ - ቄ - ቅ ..... 14
ስድ ምሳሌ። ..... 15
በ - ቢ - ባ - ቤ - ብ ..... 15
ስድ ምሳሌ ..... 17
ተ - ታ - ት - ..... 18
ስድ ምሳሌ ..... 19
ነ - ኑ - ን ..... 19
ስድ ምሳሌ ..... 20
አ - እ ..... 20
ስድ ምሳሌ ..... 24
ዐ - ዓ - ዕ ..... 24
ስድ ምሳሌ ..... 25
ከ - ካ - ክ - ኮ ..... 25
ስድ ምሳሌ ..... 28

ወ - ዋ- ዉ - ዎ ........ 28
ስድ ምሳሌ ........ 29
ዘ - ዛ - ዝ - ዞ ........ 29
ስድ ምሳሌ ........ 30
የ - ያ - ይ ........ 30
ስድ ምሳሌ ........ 36
ደ - ዱ - ዲ- ዳ - ዴ - ድ - ዶ ........ 38
ስድ ምሳሌ ........ 39
ጀ - ጅ ........ 39
ገ - ጉ - ጊ - ጋ - ጌ - ግ - ጎ - ጉ ........ 39
ስድ ምሳሌ ........ 40
ጠ - ጡ - ጣ - ጥ - ጨ - ጩ - ጫ - ጭ - ጮ ........ 41
ስድ ምሳሌ ........ 41
ፈ - ፊ - ፌ - ፍ ........ 42
ጸ - ጻ - ጽ - ፀ ........ 42

# ጥንታዊ ምሳሌ

## ሀ - ሂ - ሂ - ሃ - ሄ - ህ - ሆ

- ሀብታም በገንዘቡ ድኃ በጥበቡ እርስ በርስ ይቃረቡ
- ሀብታም በወርቁ ድኻ በጨርቁ
- ሀብታም በከብቱ ድኻ በጉልበቱ
- ሀብታም ለሀብታም ይጠቃቀሱ ድኻ ለድኻ ይለቃቀሱ
- ሀብታም እንደሚበላለት ድኻ እንደሚከናወንለት
- ሀብታም ገንዘቡን ያስባል ድኻ ቀኑን ይቆጥራል
- ሀብታም ያለ ድኻ አይኮራም ድኻ ያለ ሃብታም አይበላም
- ሀብታም በመመጽወቱ ድኻ በጸሎቱ
- ሀብትና ዕውቀት አይገኙም አንድነት
- ሀብታም በገንዘቡ ይኮራል ድኻ በጥበቡ ይከብራል
- ሀብታም ነው መባል ያኮራል ድኻ ነው መባል ያሳፍራል
- ሀ በሉ ተዝካር ይበሉ
- ሁለት ጊዜ ይፈርዱ ጉድ ይወልዱ
- ሁለት ባላ ትከል አንዱ ሲነቀል ካንዱ ተንጠልጠል
- ሁለት አይወዱም ከመነኰሱ አይወልዱም
- ሁለተኛ ግፍ ልብሴን ይገፍ ጀርባዬን ይገርፍ
- ሁለተኛ ጥፋት ቆሞ ማንቀላፋት
- ሁለት ጊዜነው የዶሮ ልደት ፩ዱ በእንቁላል ፩ዱ በጫጩት
- ሁለት የተመኘ የአንዱንም አላገኘ
- ሁለት ጊዜ ተናገርህ ከፋህ ሁለት ጊዜ በላህ ተፋህ
- ሁሉም ያልፋል ግን እስኪያልፍ ያለፋል
- ሁሉም እውነት ብቻ ይተርፋል
- ሁሉ ሄደ ተበተነ እህና እኔ ቀረን (አለ ያዘነ)
- ሁሉ የሚገኘ ከርሱ የሚገኝ የለም ያለርሱ
- ሁለት አፎት ባይናከሱ ይናቀሱ።
- ሂድ አትበለው እንደሚሄድ አርገው
- ሃይማኖት ያለ ፍቅር ጸሎት አለ ግብር
- ሃይማኖት ከግብር ጸሎከፍቅር
- ሆድ ዘመድ ሳይወድ አፍ እህል ሳይለምድ
- ሆዱ ወድዶ አፉ ከዶ ከፉ ለምዶ
- ሆዱ ለተባባሰው ማጭድ አታውሰው
- ሆዱ ፈሪ እግሩ ዳተኛ አዳም ሲዋጋ እርሱ ይተኛ
- ሆዱ ናረት (ዘርጣጣ) ሙያው ከዠረት

### ስድ ምሳሌ።

- ሀብታም ሲሰጥ የድኻው ሙ.. ያብጣል
- ሁለት እግር አለኝ ብሎ እሁለት ዛፍ ላይ አይወጣም
- ሁሉን ቢናገሩት ሆድ ባዶ ይቀራል
- ሁለት ቁና ሰጥቼ አንድ ጥንቅል
- ሁለት ጉድጓድ ያላት አይጥ አትሞትም
- ሁሉም አካል ነው ግን አንድ ዓይን አይሆንም
- ሂዳ ጉበት ይነሷታል ታላቅ ቅናሽ ላኩልኝ አለች
- ሃይማኖት የሌለው ሰው ልጓም የሌለው ፈረስ ነው
- ሆዳም ቢተፈትፍ የበላ ይመስለዋል
- ሆዳም ቢሸከም የጠገበ ይመስለዋል
- ሆዳም ሰው ፍቅር አያውቅም። ሆድና ግንባር አይሸሸግም
- ሆድን በጐመን ቢደልሉት ጉልበት በዳገት ይለግማል
- ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ። ሆድ ባዶን ይጠላል
- ሆዴ ሆዴ የሚለውን ጌታ ያየዋል ዓይኔ ዓይኔ የሚለው
- ሰው ያየዋል፡ ሆድህና ልጅህ አይጣላህ
- ሆድህን ጐመን ሙላው ጀርባህን ለጠላት አታሳይ
- ሆድ ሲሞላ ራስ ባዶ ይቀራል
- ሆድ የሸሸገው ብቅል ያወጣዋል
- <u>ሐ - ሕ - ኃ - ኅ</u>

- ሐምሌን በብጣሪ ነሐሴን በእንጥርጣሪ
- ሐሰት እያደር ይቀላል እውነት እያደር ይበራል
- ሐሰተኛ በቃሉ ስደተኛ በቅሉ ይታወቃሉ
- ሐሰተኛ ሲናገር ይታወቃል ስሱ ሲበላ ይታነቃል
- ሐሰተኛን ሲረቱ በወንድሙና በእኅቱ
- ሐሰተኛን ምስክር ጉልበት ይሰብር
- ሐሰትና ስንቅ እያደረ ያልቅ
- ሐሰት አያቀላ እውነት አያደላ
- ሐረግ ለመጻፍ አልጋ ለምንጻፍ
- ሐረጉን ሳብ ዛፍ እንዲሳሳብ
- ሐሳብ ያገኛል ፍራት ያሸኛኛል
- ሕመሙን የደበቀ መድኃኒቱም አልታወቀ
- ሕግ ይኖራል ተተክሎ ሥርዓት ይኖራል ተዛውሮ
- ኃጢአት በንስሐ እድፍ በውሃ
- ኀዳር መማረፊያ ሰኔ መቃጠሪያ

## ስድ ምሳሌ።

- ሐሰተኛ ያወራውን ፈረሰኛ አይመልሰውም
- ሐምሌና ሙሽራ ሳይገለጡ ነው
- ሐሜትና ጅራት በስተኋላ ነው
- ሐኪሞች እስኪመካከሩ በሽተኛው ይሞታል
- ሕመሙን የደበቀ መድኃኒት የለውም
- ኃዘንና ደስታ ጐን ለጐን ናቸው
- ኃጢአት ሲደጋገሙት ጽድቅ ይመስላል

# ለ - ላ - ል- ሎ

- ለሃብት መትጋት ሰውነት ያከሳል ገንዘብን ማሰብ እንቅልፍ ይነሳል። ለሃያጅ የለውም ወዳጅ።
- ለሆዴ ጠግቤ ለልብሴ አንግቤ
- ለሆድ ቍርጠት ብላበት ለራስ ምታት ጨህበት
- ለሌለው ምን ትለው። ለሙት የለው መብት
- ለልጅ ጥርስህን ለዝምብ ቊስልህን (አታሳይ)
- ለልጅ ከሳቁለት ለውሻ ከሮጡለት
- ለልጅ ሲሉ ይበሉ ለወገን ሲሉ ይጠሉ
- ለልደት ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ
- ለምን ያለው ስልቻውን ጫን ያለው ኮርቻውን
- ለማን ይፈርዱ? ለወደዱ አይደለም ለወደዱ ለወለዱ
- ለማን አለው ፈጣሪ አለው ጠጅ ለሌለው ውኃ አለው
- ለሰው የማይል ሰው ሞትም ሲያንሰው
- ለሰይጣን አትስጠው ሥልጣን
- ለሰው ጠላቱ ይወጣል ከቤቱ። ለደጎና ሰው ዋጋ አነሰው
- ለሰው ብትል ትጠፋለህ ለግዚሔር ብትል ትለማለህ
- ለሞኝ ንገረው ምን ይሰማ ብዬ ለብልህ ንገረው ምን ይስተው ብዬ። ለሺ ፍልጥ ማሰሪያው ልጥ
- ለሰማይ ምሰሶ የለው ለባዕድ ሥር የለው
- ለሴትና ለጉም አይዘገኑም። ለሴት ጠላ ለፈረስ ቆላ
- ለስሱ ፍትፍት አሳይቶ እበት ማጉረሱ
- ከሹመት ካልመከሩለት ለጥርስ ካልነከሩለት
- ለራሱ የማይረባ የሌላም አይረባ
- ለራስ ሲቈርሱ አያሳንሱ። ለራሱ ሲቆርስ አያሳንስ
- ለረዥም መንገድ አትሩጥበት ለረዥም ነገር አትቸኩልበት
- ለራሱ አያውቅ ነዳይ ቅቤ ለመነ ላዋይ
- ለራሱ አያውቅ ጠንቋይ መድኃኒቱ ላዋይ
- ለቀን ቀጠሮ ለሴት ወይዘሮ። ለቅናት የለውም ጥናት
- ለቀሊል ሰው ምሥጢር መንገር በቀዳዳ አቍማዳ ጤፍ መቋጠር። ለቀለብላባ አማት ሲሶ ብትር አላት
- ለቀማኛ የለውም እጅ ለበቅሎ የለውም ልጅ
- ለቅዘን እግር አንሥተውለት ለውሻ ሸሽተውለት
- ለብልህ አይነግሩ ለአንበሳ አይመትሩ
- ለባዕድ የሰጡት ኮሶ ይወጣል ደም ጐርሶ
- ለቤት ሳንቃ ለሰው አለቃ ለነገር ጠበቃ
- ለተሾመው ይመሰክሩለታል በተሻረው ይመሰክሩበታል
- ለተማሪ ቆሎ ለወታደር በቅሎ
- ለተራብ ቂጣ ለተጠማ ዋንጫ
- ለተንኰለኛ ሲሉ ይሰበሰባሉ ለቅን ይፈርዳሉ
- ለችግር የፈጠረው ቢነግድ አይተርፈው

- ለንጉሥ የሚረዳ ከባሕር የማይቀዳ
- ለእባብ እግር የለው ለሞች ልብ የለው
- ለእግሩ የተጠየፈ ለቂጡ አተረፈ
- ለእጅ ርቆ ለዓይን ጠልቆ
- ለእብለት ሥር የለው ለእባብ እግር የለው
- ለእውነት ማማ ለውሸት ጨለማ
- ለአበባ የለው ገለባ። ለወሬ የለው ፍሬ
- ለዕውር ዝማሜ ለመላጣ ጋሜ (አይስማማውም)
- ለከሳሽ የለው መላሽ። ለወርቅ ያሉት አንገት ላሽከት
- ለወጡ እዘኑለት አንዳንድ ጊዜስ ከደረቁም ጉረሱለት
- ለውሽማ ሞት ፊት አይነጭለት
- ለዋስ አፍ የለው ለጉንዳን ደም የለው
- ለይቶ እንደ ፈፋ አንኋሎ እንዳረፋ
- ለደኅና ሰው ውሸት ለጅብ እሸት
- ለዳባ ለባሽ ነገርኽን አታበላሽ
- ለዳኛ ዳኛ አለው ለአንበሳ ተኩላ አለው
- ለዳኛ አመልክት እንዲሆን መሠረት
- ለዳርቻው ሲሳሱ ከነ ማኸሉም ተነሡ
- ለገደለ ጐፈሬ ላረጋገጠ ወሬ
- ለግዚሄር የተቀናቀነ ስድቅ ለንጉሥ የተቀናቀነ ወርቅ
- ለጉንዳን ደም የለው ለዝንም ቤት የለው
- ለጨለማ ጊዜ መብራት ለመከራ ጊዜ ብልሃት
- ለፍቅር ብተኛት ለጠብ አረገዘች። ለፊሪ ይበቃል ፍርፋሪ
- ላህያ ያልከበደው ለመጫኛ ከበደው
- ላለፈው አይጠየቁም ለሚመጣው አይበለጡም
- ላለፈው ጸሎት ከንቱ ጩኸት ላሊበላ አደራውን አይበላ
- ላሜ ቦራ ላሜ ቦራ የልጆቼን ነገር አደራ
- ላም ነጂዋን እንጂ አታውቅም ጌታዋን
- ላም እሳት ወለደች እንዳትልሰው ነደደች እንዳትጥለው ወለደች። ላላወቀው ፎገራ ዱር ነው
- ላም አለችኝ በሰማይ ወተቷንም አላይ
- ላታመልጠኝ አታሩጠኝ። ላንድ አራሚ ፱ኝ ቋሚ
- ላንድ ብርቱ ሁለት መዳኒቱ
- ላይሆን ዘመድ ገንዘብህን አትስደድ
- ላዋቂ አትወቅበት ለረኸም አትከንዳበት
- ላይኛው ከንፈር ለክርክር ታችኛው ከንፈር ለምስክር
- ላይምረው አማስነው ላይበላው አበላሸው
- ላይቀር መሞቱ መንጠራወቱ። ላገሩ እንግዳ ለሰዉ ባዳ
- ላይታች አይፈርድ ሳያተርፍ አይነግድ
- ሌባ ውሻ ላፏ ሊጥ ለወገቧ ፍልት
- ሌባ ሌባውን ሲሰርቀው እንዴት ይደንቀው
- ሌባ ቢያዩኝ እስቅ ቢያዩኝ እሰርቅ
- ሌባ ላመሉ ዳቦ ይልሳል አሉ
- ልሂድ ልሂድ ባይ ስንቅ አጉዳይ
- ልባብ መሳቢያ ልጓም ማረሚያ
- ልቡ ከቂም ከበቀል እጁ ከመግደል
- ልብ ደስ ሲለው ፊት ይበራል ልብስ ሲያዝን ፊት ይጠቁራል
- ልብ ሳይዙ ነገር አያበዙ ልባልባ ታጥቆ ዓዛባ ጠጉር ሳይኖር ወለባ። ልብ ሲያውቅ ገንፎ ያንቅ
- ልጅ አባቱን አይብ አጓቱን (ይመስላል)
- ልጅና ጦጣ ውሀውን ይጠጣ። ልጅ ከወረሰ ቤት ከፈረሰ
- ልጅ አይወልድ አንድ አይፈርድ
- ልጅ ያባቱን ወቄራ ያፎቱን። ልጅ ካርጣጣ እህል ከዘባጣ
- ልጅ ቢያስብ ምሳውን አዝማሪ ቢያስብ ጠላውን
- ልጅ ያለ እናት ቤት ያለ ጉልላት (ከፍ አይልም)
- ልጅ ካበጀው አባት ያበላሸው
- ልጅ ያለ ልጅ አከለ። ልጅ ተውር እህል ከጉራንጉር
- ልጅና ቄስ በሰው ገንዘብ ያለቅስ
- ልጅ ካባቱ ሾተል ካፎቱ። ሎሌ ለስሕተት ጌታ ለምሕረት
- ሎሌ ሲከብር ጌታውን ይከሳል ሙክት ሲሰባ ሾተሉን ይልሳል። ልጅ በጡት እህል በጥቅምት (ይፋፋል)
- ሎሌ ያገለገለውን ይቆጥራል ጌታ ያስቀየመውን ያስባል

- ሎሚና ትርንጎ ሞልቶ ባገር እምቧይ ያሸታል አወይ የድሃ ነገር። ልጡ የተራሰ መቃብሩ የተማሰ

## ሰድ ምሳሌ።

- ለሆዳም በሬ ጭድ ያልዘታል
- ለልጅ ጥርስ ለዝምብ ቊስል አታሳይ
- ለመስጠት አለመቸኰል ከሰጡም ወዲያ አለመጸጸት
- ለማይሞት መድኃኒት አለው። ለላም ቀንዷ አይከብዳትም
- ለሞኝ ሰኔ በጋው መስከረም ክረምቱ ነው
- ለስሟ መጥሪያ ቁና ሰፋች ለሰባቂ ጆሮህን አትስጠው
- ለተቀማጭ ሰማይ ቅርቡ ነው
- ለቸኰለ ሰው ዋንጫ አስጨብጠው
- ለዓይንና ለወዳጅ ጥቂት ይበቃል
- ለንፉግ ሰው የገበያ መንገድ ይጠበው
- ለጋስ ቢለግስ አበደረ እንጅ አልሰጠም
- ለውጠኝ ባይ የሚሻለውን አውቆ
- ለጥልና ለዳኛ ያለው ገንዘብ አፋፍ ይቆያል
- ለፈሪ ሜዳ አይነሱም ለፈሪና ለንፉግ እያደር ይቆጫዋል
- ላለው ቅንጭብ ያረግዳል። ላህያ ማር አይጥመውም
- ላፈ ግም ድፍን አፍንጫ ያዝለታል
- ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ
- ላም ነጅዋን እንጂ ጌታዋን አታውቅም
- ላምሳ ጋን አንድ አለሎ ይበቃል
- ላለፈው ክረምት ቤት አይሠራም
- ልብ ካዘነ እንባ አይገድም። ሎሌና አሞሌ ካዘዙት ይውላል
- ልብ ሲፈቅድ መግደርደር ራስን መግደል

## መ - ሙ - ሚ - ማ -ሜ - ም - ሞ

- መሆን በሆነ ዳሩ ግን ምን ይሆናል አገርህ ሩቅ ሆነ
- መልካም ሱሪ ለተማሪ። መልካም ጭራ ለደብተራ
- መልካም ቆንጆ የላት መቀናጆጅ
- መልካም በሬ ለርሻ ዶማም አያሻ
- መልካም ፈረስ ለሩጫ ሲጋር በቅሎ ለኮርቻ
- መሄድ መመለስ ካሰቡት ለመድረስ
- መልካም አድራጊ አበደረ ክፉ አድራጊ ተግደረደረ
- መልካም ንግግር ቁጣን ያበርዳል መጥፎ ንግግር ልብን ያናድዳል። መልካም ወጥ እጅ ያስመጥጥ
- መልካም ወሬ አጥንት ያለመልማል መጥፎ ወሬ ልብን ያደክማል። መሄድና መምጣት ማግኘትና ማጣት
- መመከት ጋሻ አንግቦ መጸለይ ዳዊት አቅርቦ
- መመራመር ያደርሳል ከቁም ነገር
- መምከርማ ድኻ ይመክራል ሰሚ አጥቶ ይቀራል
- መምህራን ካሉ አዋቂዎች ይበዛሉ
- መምህራን ካሉ አዋቂቶች ይበዛሉ
- መምህረ ኮነ በበደውሉ ፊደላተ ዘጕልቈ ኵሉ
- መሳሳሚያ ከንፈር መገናኛ ድንብር (የለንም)
- መሣሪያ ይዞ ጸሎት (ቤት) ካፓ ላንቃ ለብሶ ማድ ቤት
- መስጠት አያውቅ እራት መምታት አያውቅ እናት
- መስከረም የሚወልደው ንጉሥ የሚፈርደው አይታወቅም
- መሰስ ሲሉ ምን ደስ ይሉ መስሎ ከመታየት ሆኖ መገኘት
- መለመን የለመደ ምላስ በሕልሙ አቊማዳ ይዋስ
- መሬት ክሰባ ግዳይ ከሰለባ
- መሬት በአቅጣጫ ውበት (መልክ) ባፍንጫ
- መሬት ለአራሽ ነፍጥ ለተኳሽ
- መሬት በወንዙ እባብ በመርዙ
- መቀመጥ መቆመጥ። መታፈር በከንፈር
- መበለት በቁስ ገበሬ በንጉሥ ደብተራ በጳጳስ ቢቀኑ አይገናኙ። መተው ነገሬን ከተተው
- መቼ መጣሽ ሙሽራ መቼ ቆረጠምሽ ሸንብራ
- መታዘን ሳያውቅ ማዘዝ ታላቅ መዘዝ
- መነኵሴ ከደብሩ አንበሳ ከዱሩ ወጥተው ካደሩ
- መነኵሴ በቆቡ ወንበር በከታቡ
- መናኝ ለነፍሱ አዳኝ (ለከርሡ) ለጥርሱ (ይገሰግሱ)

- መናፍቅ ለትርጓሜ ጥምቦሆ ለልምላሜ
- መንገድ ሳለ በዱር በቅሎ ሳለ በእግር
- መንገድ ታገር ልጅ ስደት ተሹም ልጅ
- መንግሥቴን የነሱ ክብሬን የወረሱ
- መንካት ያደርሳል ከመነካት። መነዛነዝ ያመጣል መዘዝ
- መንደር ከዋለ ንብ አደባባይ የዋለ ዝምብ (ይሠለጥናል)
- መኖሪያውን ትተው መናገሪያውን
- መከሮ ልብ አይደል አሟጭቶ ጥርስ አይደል
- መኰርኰሚያን ያላገኘ መዘርጊያን ተመኘ
- መውደዱንስ አንተን እወዳለሁ ኋላ ወዴት እገባለሁ
- መዝሙር በሃሌ ነገር በምሳሌ። መከፈልት ሲሹ መቅሠፍት
- መዋዕል ለፍሥሓ ዕድሜ ለንስሓ
- መጀመሪያ ስተት ኋለኛው ዕብደት
- መጠጥ ለጨዋታ ወንድም ለግርግርታ
- መግረፉን ግረፍ ግን ከባት አትለፍ
- መፍረሱ ላይቀረኝ ለምን ፈጠረኝ
- ሙልጭ እንደ ስብቆ እናጥ እንደፌቆ
- ሙት መውቀስ ድንጋይ መንከስ
- ሙዙን፥ ሰላይ መዘዙን። ሙቶ የተነሣ እግዜርን ረሳ
- ሙክት ሲሰባ ከባራ ይታከካል ባለጌ ሲከብር ያፎክፋካል
- ሚስትህን አመዳም ጕራዲህ ጐመዳም
- ሚያ ባለ ፍየል ከፈለ። ማሽላ ለማሽላ ተያይዞ ቆላ
- ማኅበርህ ቀረ ሴረኛህ ተሻረ (አይበሉህ)
- ማኅፀን መዋኛ ቤተ መቅደስ መገኛ
- ማሽላ ሲያርር ይስቃል ትዕቢተኛ ሲንደላቀቅ ይወድቃል
- ማሩን አምርሮ ወተሩን አጥቁሮ። ማር ሲሰፍሩ ማር ይናገሩ
- ማር ሲበዛ ያስተፋል ነገር ሲበዛ ያጠፋል
- ማገር ቢስ እራቱ ገማስ። ማን አለ መርማሪ አለ ፈጣሪ
- ማተብና አንገት ክታብና ደረት (ስምም)
- ማን ያውቅ አገር ማን ይጠብቅ ማገር
- ማቅ ይሞቃል ሻሽ ይደምቃል የሚበጀውን ባለቤቱ ያውቃል። ማን ያልነበረ ማን ያልተቀበረ
- ማን ይንገር የነበረ ማን ያርዳ የቀበረ
- ማን ይስጥ ወላጅ ማን ይንሣ ፈራጅ
- ማፈር ከሌለ ክብርም የለ። ማግኘት በእድል ሥራ በግድል
- ማየ ሰሊሆም ዕውር ኅበ ዘወሰድዎ የሐውር
- ማፈር ከብዙ ነገር ይጠብቃል አለ ማፈር በብዙ ነገር ያስጠይቃል። ማየት ከመልአክ መቀበል ከአምላክ
- ምላጭ ምላጭን ይቆርጠው ሰው ሰውን አይበልጠው
- ምላጭ ቢያብጥ በምን ይበጡ ውኃ ቢያንቅ በምን ይውጡ
- ምላጭ አይበጥ ያበጠውን ያፍርጥ
- ምላጭ ለመላጫ ጠፍር ለመለመጫ
- ምሥጢር ከቤት ምክር ከጐረቤት
- ምስክር ከተጠራ መሥዋዕት ከተሠራ (አያድርም)
- ምስክር ቢያድር ይለወጣል ሸንፍላ ቢያድር ይመለጣል
- ምስለኔ ሁን እንደኔ። ምስር ይሰብራል ጓያ ይመረራል
- ምስር መዝራት ሥራ ማጣጥ (አለ ጦጣ)
- ምስክር ተበለጠ ባቄላ ተፈጠጠ
- ምቀኛ ጠላቱን ይተክላል ወዳጁን ይነቅላል
- ምንም ቢለፈልፉ ድካም ነው ትርፉ
- ምን ያመታ ድኃ ምን ያገሣ ውኃ
- ምንም ቢያጠምዱ በዘጠና ቤቱን አይተው ቀጠና
- ምንም ቢነግሡ በእጅ አይካሱ
- ምንም ቢኖሩ ከሞት አይቀሩ
- ምንም ቢያርሱ እንደ ጐመን አይጐርሱ
- ምንም ቢከፉ ዘመድ ምንም ቢጠም መንገድ
- ምንም ቢፋቀሩ አብረው አይቀበሩ
- ምንም ቢዋደዱ ባዕድን አይረዱ
- ምንም ሴት ብታውቅ በወንድ ያልቅ
- ምንም ብወድህ በወንድሜ ግንባር ደም አልይብህ
- ምንም ቢሆን ጉፋያ ሥጋ ሥጋ ነው ብያ

- ምንም ብቀጥን ጠጅ ነኝ ምንም ብደኽይ ጨዋ ነኝ
- ምን ይዞ ይሄዷል ጉዞ። ምድር ለገበረ ጦር ለወረወረ
- ምን ይሰማ ጀሮ ምን ይውጥ ጉረሮ
- ምን በእግሩ እየመጣ በእጁ እንዳይመጣ (አለ ዳኛ)
- ምከረው ምከረው እምቢ ቢል መከራ ይምከረው
- ምክር ለሚሰማ ውሃ ለተጠማ (ለሚጠጣ)
- ምክንያት እንደ ሴት ግርማ እንደ ሌት (ይስጥህ)
- ምክር ተቀባይ ሲያጣ ተመልሶ ወደ ባለቤቱ ይመጣ
- ምድር ሲደላደል ማሳ ሲታደል (ተወልደኹ አለ ጦጣ)
- ምድር በአለቃ ከማይ በጨራቃ
- ምጡን እርሽው ልጁን አንሽው
- ሞተ በለኝ ከንፈኔን አለ በለኝ ቀለቤን
- ሞት ላይቀርለት ምክንያቱ በይሁዳ ሆነለት
- ሞት ላይቀር ፍራት አመል ላይቀር ቅጣት
- ሞት ሲደርስ ቄስ ጦር ሲደርስ ፈረስ
- ሞት በአቤል ተዝካር በሮቤል (ተጀመረ)
- ሞት በጥር በነሐሴ መቃብር የማይመስል ነገር
- ሞትህ እንደ ሕይወትህ ሕይወትህ እንደ ሞትህ (ነው)
- ሞኝ መካሪውን ባለጌ አከባሪውን (አይወድም)
- ሞኝ ባያፍር የሞኝ ዘመድ ያፍር
- ሞኝ ባያገኘው ፈሊጥ ውሻ ያገኘው ሊጥ
- ሞኝ የዕለቱን ብልህ ያመቱን (ያስባል)
- ሞኝ የተከለው ብልህ አይነቅለው
- ሞኝ ካመረረ በግ ከበረረ (መመለሻ የለውም)
- ሞኝ ቢፈርዱለት አያውቅ ቢፈርዱበት አያውቅ
- ሞኝ ካገደደ ልጅ ከለመደ
- ሞኝ የመከሩት ለት ቀንጫ የጠረጉለት ለት
- ሞኝ ቢመክሩት ከልማዱ አህያ ቢያጥቡት ከአመዱ
- ሞኝ እንደ ነገሩት በቅሎ እንዳሰገሩት

## ስድ ምሳሌ።

- መሬት ሲያረጅ መጭ ያበቅላል
- መብረቅ የመታው ወዘት አስተኛው
- መርፌ የራሷን ቀዳዳ ሳታይ የሌላውን ቀዳዳ ትጠቅማለች
- ሚዳቋ ዘላ ዘላ ተመሬት። ማጣትና ማግኘት ጆሮ ለጆሮ
- ማሽላና ነገር ካንገት ካንገቱ። ማሽላ ሲያርር ይስቃል
- ሜዳን መራመድ ሳታውቅ መሰላሉን መውጣት ማን አስተማራት። ምንም ብታውቅ ከዳኛ ጋር አትሟገት
- ምንም ቢቸገሩ ተበድሮ ጋሬዳ። ምጥ ለናቷ አስተማረች
- ሞት ቢዘገይ የቀረ ይመስላል። ሞኝ ሲናገር ብልህ ያዳምጣል
- ሞኝና ውኃ ከወሰዱት ይሄዳል። ምሳሌው ሁሉ አንካሳ ነው
- ሞኝ ዝም ሲል አዋቂ ይመስላል።

## ሠ - ሥ

- ሠርገኞች መጡ ብቅል አስጡ
- ሠርገኞች ደረሱ በርበሬ ቀንጥሱ
- ሥራ ካልሠራችሁ የት ሊገኝ ምሳችሁ
- ሥራ ለሠሪው እሾህ ላጣሪው
- ሥርዓት ያናግራ ዕርቅ ያፋቅራል
- ሥንዴ በጭንቅ ባለጌ በጥብቅ
- ሥንዴ በማዶ ይመስላ በረዶ
- ሥንዴ ለመቀኍረብ ዋስ ለማቅረብ
- ሥራ ከመፍታት ልጀን ላፋታት
- ሥራ ያጣ ገበሬ ጨው የሌው በርበሬ
- ሥጋ ለአንበሳ ወተት ለእምቦሳ

## ስድ ምሳሌ።

- ሥራ ያጣ መነኵሴ ቆቡን ቀዶ ይሰፋል
- ሥንዴ ካለ ፈታጊ አይታጣም (አይጠፋም)
- ሥጋና ሴት በባለጌ ቤት ይረክሳል
- ሥጋ ቢወድቅ አፈር ይዞ ይነሣል
- ሥጋ ቍጠር ቢሉት ጣፊያ አንድ አለ

- ሥጋ ያማረው መረቅ የሸተተው ከበጎች ማህል ገብቶ ይተኛል። ሥጋ ለጥጋብ አጥንት ለትካዜ

## ሰ - ሲ - ሳ - ሴ - ስ

- ሰማንያ ለማገጃ ስለት ለማረጃ
- ሰማይ ከነ ግሡ ምድር ከነ ልብሱ
- ሰማይ ከነደመናው ምድር ከነ ጐተናው
- ሰማይ ያለ ደመና ብረት ቤት ያለ ሴት መሠረት
- ሰማይ ቢያኩ ጤፍ ቢሰኩ አይደረስም ልኩ
- ሰማይ አለ ደመና ብረት ነገር አለ ዳኛ ተረት
- ሰማይ ሲጠና ምድር ሲቀና። ሰሳ የናቷን አትረሳ
- ሰምቶ ዝም አይቶ ዝም በሆድ ያለ አይነቅዝም
- ሰምቶ መቻል ለእግዜር ይመቻል
- ሰርቆ ከማሰብ እጅን መሰብሰብ
- ሰርቀህ የጉም ሌባ ጉም ሲለቅ የታባትህ ትገባ
- ሰባኪ መፈለጉ ለሰሚ መርፌ መፈለጉ ለጠቃሚ
- ሰባ እንረደው ጐፈየ እንስደደው
- ሰባት ዓመት እንዳይማሩ ፸ ዓመት ይደንቍሩ
- ሰነፍን ከመውለድ ይሻላል ማስወረድ
- ሰንፍ ሴት ያገባ በሰኔ ገደል የገባ
- ሰነፍ ሰው ናቂ ሞኝ ሰው ሳቂ። ሰኔ ነገ በኔ
- ሰማይ አይላጥ የ፫ ፍርድ አይለወጥ
- ሰንበሌጥ ለቤት ቀሚስ ለሴት
- ሰው መጣ ነገር መጣ ነገር ከመጣ አለ ጣጣ
- ሰው የሠራው መሬት አወራው
- ሰውን አትመኑ መሬት አወራው
- ሰውን አትመኑ አብዱል ዘመኑ
- ሰውና አመሉ ሳይተዋወቁ ይኖራሉ
- ሰው በዋለበት ውኃ በወረደበት
- ሰው ይጥራል ዕድል ይሠራል
- ሰው እዳነጋገሩ በቅሎ እንደሰጋሩ
- ሰው ሆኖ አይስት የለ እንጨት ሆኖ አይጤስ የለ።
- ሰው ጊዜውን ዕቃ ቦታውን ምንጊዜም አያጣውም
- ሰውየውን ካልናቁ አጥሩን አይነቀንቁ
- ሰውን ሰው አማው የራሱን ባይሰማው
- ሰው ለወዳጁ መኰንን ለጠጁ
- ሰው ሠራሽ በአምላክ ሥራ ፈራሽ
- ሰው ያመነ ጉም በአምላክ ሥራ ፈራሽ
- ሰው ያመነ ጉም የዘገነ አንድ ሆነ
- ሰውነቱ ከንጽሕና ልቡ ከትሕትና ያልተለየ ደህና
- ሰው ተዘመዱ አህያ ታመዱ። ሰው ካላገሩ ምነው መናገሩ
- ሰው ከተከተተ ጅብ ካኰተኰተ
- ሰው ይጨነቃል የሚሆነውን እግዜር ያውቃል
- ሰው እንደ ዓቅሙ እህል እንደ ቀርሙ
- ሰው ይኖራል እንጂ እንደቤቱ አይኖርም እንደ ጐረቤቱ
- ሰውን ከነ አመሉ ድሪቶን ከነ ቅማሉ ወዷያ በሉ
- ሰው ያላገር መሬት ያለ ዘር። ሰው ባፉ አሞራ በክንፉ
- ሰው አይወድም በደል በሬ አይወድም ገደል
- ሰው በዝና ዝናም በደመና (ይታወቃል)
- ሰው በዘመድ አህያ በገመድ
- ሰው በየወንዙ ብዙ ነው መዘዙ
- ሰው ያስባል እግዚአብሔር ይፈጽማል
- ሰውነቱን ቢንቁ ልብሱን ይጠይቁ
- ሰውን ከመለመን ፈጣሪን ማመን
- ሰው ሰን የሚበልጠው ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ነው
- ሰውን አትናቀው እህልን አትራቀው
- ሰውን የሚያስረጅ ሐሳብ ልብስን የሚያስረጅ ስብሳብ
- ሰው በከንቱ አይጐነበስም ወይም ዕቃ ሊያነሣ ወይም ሊፈሳ። ሰውን ውደደው እንጂ አትመነው
- ሰይጣን ለአመሉ መጽሐፍ ቅዱስ ይጠቅሳል አሉ
- ሰዶ ማሳደድ የያዙትን አለመሰደድ
- ሰው ማመን ገደለኝ የኔን እየመሰለኝ
- ሰጥቶ በእጅ መለመን ከሰው ደጅ
- ሰው ተዛመዱ ቀበሮ ተጕድጓዱ
- ሰው ባላወቀው ይፈርዳል እግዚአብሔር ባወቀው ይቀጣል

- ሲሄዱ አገር ሲተኙ ነገር አወይ የዓለም ነገር
- ሲሞቱ ገመድ ሲገዙ ገመድ (አይጠፋም)
- ሲሠሩ ሎሌን መስሎ ሲበሉ ጌታን አህሎ
- ሲሰርቀኝ ያየሁት ሲሰጠኝ ጠላሁት
- ሲሰበር ይሰንጠር ሲረዝም ይጠር
- ሲስሚት እምቢ ብላ ሲሰቡዋት
- ሲበላ ለሚከሳሲ ነገሩን ለሚረሳ ለዚያ እህልን ንሳ ለዚያ ምክርን ንሳ። ሲበሉ በሰዓት ሲናገሩ በሥርዓት
- ሲርበኝ ታነቅሁ ሲጨንቀኝ ታረቅሁ
- ሲቀላውጡ ዓይንን አፍጦ ሲቆፍሩ እግርን አንፈራጦ
- ሲቀመጡ አውቃለሁ ሲነሡ አፍራለሁ
- ሲናገሩት ያልሰማ ሲሙቱት ያልደማ
- ሲተኙ አገር ያገኙ ሲነሱ ነገር ይረሱ
- ሲታጠቡ ከክንድ ሲታረቁ ከሆድ
- ሲከሱ ይከሱ ሲሄዱ ይመለሱ
- ሲኖሩ ለጠቅ ሲሄዱ መንጠቅ
- ሲያጌጡ ይመላለጡ ሲገዙ ይገዙ
- ሲያምኑ መከዳት ሲወዱ መጥላት
- ሲያዩት ያምራል ሲይዙት ያደናግራል
- ሲነግሩት የሚዘነጋ ሲያምኑት የሚሰጋ የለውም ዋጋ
- ሲያረጁ አምባር ይዋጁ። ሲያምኑት የከዳ አለበት ዕዳ
- ሲያዩት የማያምር ሲበሉት ያቅር
- ሲጠሩህ ዝም በል ሳይጠሩህ አቤት በል ነገሩ እንዲዘናበል። ሲጠሩህ አቤት ሲልኩህ ወዴት
- ሲያጥቡት ያድፋል እጅ ሴምክሩት ያጠፋል ልጅ
- ሲፈሩ አይከሱ በጉጣ አያርሱ (ጉጣ ያለቀ ማረሻ)
- ሳለው የማያበድር ገዳይ ተበድሮ የማይመልስ አበይ
- ሰላይ ሙዙ አየሁ መዘዙ
- ሳማና አብላሊት ውሽማና ሚስት
- ሳለቅስ ሳነባ ውል ለሳማ የሰጠኸኝ ሽማ በደጅህ ተቀማ
- ሳል ያለበት ጉልማሳ ዘንጋዳ ያለበት ዳጉሳ
- ሳል ተይዞ ስርቆት ቂም ይዞ ጸሎት (ቆሎ መዝራት)
- ሳትበጡ እገሙኝ ሳትመከሩ አርሙኝ
- ሳያገቡ ማርገዝ ሳያረጁ መፍዘዝ
- ሳያተርፍ ያበደረ ሳይቀበል ተቀበረ
- ሳይቸገር የተበደረ ሳይከፍለው ተቀበረ
- ሳይማሩ መተርጐም ሳይበጡ ማገም
- ሳይሠሩ ማግኘት ሳይጸድቁ ገነት
- ሳይቀቡ አይነግሡ ሳይመነኩሱ አይጸጽሱ
- ሳይባርክ ያረዳ ሳይታየው የፈረደ
- ሳይጠሩት አማካሪ ሳይሾሙት ፊታውራሪ
- ሳይቀስሱ አይናዘዙ ሳይሸሙ አያዝዙ
- ሳይርቅ በቅርቡ ሳይደርቅ በርጥቡ
- ሳይቀድስ ያርዳል ሳይታየው ይፈርዳል
- ሳይቀሱ መምሬ ሳይጠምዱ ገበሬ
- ሳይቀሱ መናዘዝ ሳይዞሙ ማዘዝ
- ሳይረቱ አይበረቱ። ሳይከካ ተቦካ
- ሳይታደሉ አይገዙ ሳይበሉ አይወዙ
- ሳይነገር ይፈርዱታል ሳይጻፍ ያነቡታል
- ሳይውሉ ይዋዋሉ ሳይተማመኑ ይማማሉ
- ሳይዘራ ያመተረ ሳያውቅ የተረተ
- ሳይገድሉ ጐፈሬ ሳያረጋግጡ ወሬ
- ሳይጠሩህ መጣህ ሳትጠግብ ወጣህ
- ሳይጣሉት የተጣላ ሲርብ ያበላ (አይረሱም)
- ሳይጠሩት አቤት ባይ ሳይሰጡት ተቀባይ
- ሳይጠሩት የመጣ ሳይጠግብ ወጣ
- ሳይፈታ ሚስቱ ሳይረታ ርስቱ። ሳይያዙ ገና ዘር ልመና
- ሴት አግብተው ሴት ቢወልዱ የታለ ግንዱ?
- ሴቶች ሲበዙ ጉመን አጠነዙ
- ሴት አማት የመረዘው ኮሶ ያነዘዘው (አንድ ነው)
- ሴትና ፈረስ ያቀረቡለትን ይቀምስ
- ሴትና ቄስ ቀስ በቀስ። ሴትን ያመነ ጉምን የዘገነ
- ስለ ትዕግሥቱ ይጾሙ ስለ ሥራቱ ይቆሙ
- ስለ ፍቅር በስመ አብ ይቅር። ስለ ልብስ ይኰራል ነፍስ
- ስለት ድጉሱን ዳባ ራሱን። ስለ ከለሱ አይፈወሱ
- ስልቻና አቍማዳ ቁራጣና ጐማዳ
- ስላ ጐረስሁ እጄን ተነከስሁ። ስም የመራል ጥዋፍ ያበራል

- ስም ይወጣል ከቤት ይቀበላል ጐረቤት
- ስም እኩል ሥራው ስንኩል። ስሙን ጠርቶ ራሱን ቆርቶ
- ስሞታ የውርርድ እኩሌታ። ስሙን ለሰው አወረሰው
- ስሱ መጓጓተቱን ቆዳ መንጋጋቱን (አይተውም)
- ስስታም ሲበላ ይታነቃል ሐሰተኛ ሲናገር ይታወቃል
- ስታበጅ ውላ አበላሸችው ባተላ
- ስትፈጭ የነበረች ሲፈጩላት ደከመች
- ስለ ጤስ አይነድም ስለ ዳመነ አይዘንብም
- ስትሄድ ቀንጣ ቀንጣ ስትበላ እንደ አንበጣ
- ስንቅህ ባህያ አመልህን በጉያ
- ስንቅ ያለው ጦም አያድርም ዋስ ያለው አይታሠርም
- ስትግደረደር ጦምህን አትደር። ስታበይው በልተሽ ታይው
- ስንቁን የተቀማ ነጋዴ ዋግ የመታው ስንዴ
- ስደት ከሹም ልጅ መንገድ ከሀገር ልጅ
- ስድብሽና ስድቤ አንድ ነው ትርፉ ሰው መስማቱ ነው

## ስድ ምሳሌ።

- ሰነፍ ኢጋራ ራሱን ሲነቀንቅ ይኖራል
- ሰነፍ ጸሐፊ ከሙሴ ይገድፋል
- ሰው ያለው አርፍዶ ይሞታል
- ሰው ምን ይመስላል? ቢሉ ኑሮውን
- ሰው መስሎኝ ደንጊያን ቆነጣጠሁ (አለ የሰለቸው)
- ሰው ማነን ያህል? ቢሉት የተናገረውን ያህል አለ
- ሰዶ ማሳደድ ቢያምር ዶሮህን ለቆቅ ለውጥ
- ሲሮጡ የታጠቁት ሲሮጡ ይፈታል
- ሲሰርቀኝ ያየሁት ሲሰጠኝም አላመንሁት
- ሲበዛ ሲበዛ ይገፍላል። ሲሰማ የሞተውን ሲያይ ቅበረው
- ሲያብል የተኛ ቢጠሩትም አይሰማ
- ሲያጌጡ ይመላለጡ ሲምሩ ያስተምሩ
- ሳይሆን ለብም ሳይሰበር ጠግን
- ሳትዋጋ ንጉሥ ቢሉት ግንድ ተዋግቼ
- ሳር ያልሰጧት ላም ወተት አምጪ ቢሉዋት አትሰጥም
- ሴት የላከችው ጅብ አይፈራም
- ሴትዮው በገዛ አረሟ እባባ ይዛ ታስፈራራ
- ሴት ያመጣችው ጠብ ቆሎ አይበርድም
- ሴት ያመጣችው ጠብ ቶሎ አይበርድም
- ሴት ካልወለደች ቋንጣ አትጠብስም
- ስንቅና ውሸት እያደር ይቀላል
- ስንኳን ከጦርነት ከወሬም አልፈራም
- ስንኳን ረኃብ ጥጋብንም እችላለሁ

## ሸ - ሹ - ሻ - ሽ - ሾ

- ሸማ ለብሶ ስልቻ በቅሎ ጭኖ ለብቻ
- ሸማ ማዋስ ባላገር በቅሎ ማዋስ ለወታደር
- ሸማን በውሃ ሰውነት በንስሓ
- ሹመትና ቁመት አይገኝም በምኞት
- ሹመት ላወቀው ይከብደዋል ላላወቀው ያሳብደዋል
- ሹመት በተርታ ሥጋ በገበታ
- ሹም ለሹም ይጐራረሳል ድኻ ለድኻ ይለቃቀሳል
- ሹም ቢሞት አምሳ የሹም ልጅ ቢሞት መቶ ታምሳ
- ሹም ያዝዛል ቄስ ይናዝዛል። ሺ ቢመከር አንድ በወረር
- ሺ ሙት ሺ ሞት። ሺ አውል ኪሞት ሺ ይሙት
- ሻሽ ይደምቃል ማቅ ይሞቃል። የሚበጀውን ባለቤቱ ያውቃል። ሺ ቢያጩሽ አንድ ያገባሽ
- ሽማግሌ ካሞተ ሥንዴ ካልሸተ
- ሽል ከሆነ ይገፋል ቂጣ ከሆነ ይጠፋል

## ስድ ምሳሌ።

- ሸኒና ጥላ ቤት አይገባም
- ሹመትና ቁመት ከልኩ አያልፍም
- ሹምና ጥጥ እያደር ይከዳል
- ሺ ቢታለቡ ከገሌ አላልፍም (አለች ድመት)
- ሺ ይሙቱ ሺ አውል አይሙት
- ሽማግሌና ስልቻ ሳይሞላ አይቆሙም
- ሽበት እኖር ብዬ መጥቻለሁ አለ

- ሾላ በድፍን። (ሳግላ ብላዕ አይትቅላዕ)

## ረ- ሩ - ራ - ሬ

- ረዝም ባይፈራ አጭር ባይኰራ
- ረዝም ጦር ባይወጉት ያስፈራሩበት
- ረዝሙን ባላማ አጭሩን በጫማ
- ራስ ሳይጠና ጉተና። ራስን ተከናንቦ ሙ... ገልቦ
- ራስን ተላጭቶ ወለባ ልባልባ ታጥቆ ዓዛባ
- ራብን ያማርራል ሰው ቊንጣኑን ባይቀምሰው
- ራብ ይከላል ባቄላ ከእጥፍ ያደርሳል ነጠላ
- ራዛ ትሄዳለህ? ካንተ ጋራ ስንቅህሳ አንተሳ
- ርስት በሺ ዓመቱ ይመለሳል ወደ ባለቤቱ (ይባላል)

### ስድ ምሳሌ።

- ራስ ካለበት እግር ይሰበሰባል
- ሩቅ አገር ለውሸት ይመቻል። ሩቅ አሳቢ ከቅርብ አዳሪ
- ራሴን መትቶ እግሬን ቢያከኝ አይገኝም
- ራስ ይሸብታል እንጂ ልብ አይሸብትም።
- ሬሳ በምን ከበደ? ሐሳቡን በሰው ላይ ጥሎ
- ሮቃ (መርሆ) የዝሆን አለቃ ለምሳር አይበቃ

## ቀ - ቁ - ቂ - ቄ - ቅ

- ቀለም ሲበጠበጥ ብርዕ ሲቀረጥ
- ቀባሪ በፈጣሪ። ቀስ በመቀስ
- ቀና ቢታጣ ይመለመላል ጉባጣ
- ቀን ቢረዝም ልብ ይደክም። ቀን ባጀብ ሌት በዘብ
- ቀን አይጥለው የቀለም ሠረገላ አያሰናክለው
- ቀን አይጥለው ጠጅ አያሰክረው (የለም)
- ቀን እስኪያልፍ ያባትሽ ሎሌ ያግባሽ
- ቀን ሳይቆጥሩ ውሻ ሳይጠሩ ደረሰ በእግሩ
- ቀን በበቅሎ ማታ ቆሎ። ቀን ሲጥለው ሁሉ ይጥላው
- ቀን እንደተረዳ ሌት እንደ ግድግዳ
- ቀስ በቀስ እንቁላል በእግሩ ይሄዳል
- ቀን ይነዳ እንደ ፍሪዳ። ቀን ሲደርስ አምባ ይፈርስ
- ቀን የሰጠው ቅል ደንጊያ ይሰብራል
- ቀንና ጨርቅ እንደምንም ያልቅ
- ቀን ካልለቀሙ ሌት አይቅሙ
- ቀኝም ሠረሩ ግራም ሠረሩ መገናኛው ኰሩ
- ቀጥኜ ቢያዩኝ ጅማት ለመኑኝ
- ቀድሞ ያሸተውን ወፍ ይበላዋል ቀድሞ የሚናገረውን ሰው ይጠላዋል። ቀዳዳ ያፈሳል ግቢ ያፈርሳል
- ቀድሞ ነበር እንጂ ተራምዶ ማለፍ አሁን ምን ይሆናል ተይዞ መለፍለፍ። ቁም እንደ ዓላማ ጥበቅ እንደ ጫማ
- ቁመቷ ቢያጥር እንደ ድምብላል ውዷ ክፉ ነው ይደበላል። ቁም ነገር ይዞ ተረት ቂም ይዞ ጸሎት
- ቁራ ስሙን ይጠራ። ቁጭትና መጠጥ ለጊዜው ይጣፍጥ
- ቂል ያገኘው ፈሊጥ ውሻ ያየው ሊጥ
- ቂል አይሙት እንዲያጭውት። ቄስ ለኑዛዜ ፍቅር ለሚዜ
- ቂም ቂም ያሰኘሽ እንደ ዶሮ ለካስ ለመከራሽ ላሣርሽ ኖሮ
- ቂም ይዞ ጸሎት ሳል ይዞ ስርቆት
- ቂም ይዞ ጸሎት ጭድ ይዞ ወዘት
- ቄስ ምን ይሻል? ጠላ ነገር ምን ይሻል? ችላ
- ቄስ ያዘዘህን አድርግ ቄስ ያደረገውን አታድርግ
- ቄስ ኤረክሶን መምህሩ እናት አያስቀብሩ
- ቅን በቅን ከማገልገል ፊት ለፊት ማውደልደል
- ቅልና ደንጊያ ተማትቶ ጌታና ሎሌ ተማጉቶ የማይሆነው ከቶ። ቅርንጫፉ እንደዛፉ
- ቅናት ጥናት አያገናኝ ካባት ከናት
- ቅቤና ቅልጥም ወዴት ግጥምጥም
- ቆላና ደጋ እመቤትና አልጋ
- ቆዳ ማንጓጓቱን ስሱ መንጓጓቱን (አይተውም)
- ቆጥሮ የማይሰጥ ሌባ ቆጥሮ የማይቀበል ሌባ
- ቊርጥ ያጠግባል ተስፋ ያታልላል

## ስድ ምሳሌ።

- ቀብሮ የሚመለስ የሚመለስ አይመስለውም
- ቀንድ ካላት ይልቅ ጐዳ ትከፋለች
- ቀንድ ውስጥ ገብቶ ኧራቱ አይቀርም
- ቂል ሲረግሙት የመረቁት ይመስለዋል
- ቂልን ለብቻው ስደበው ራሱ ባደባባይ እንዲሰድብ
- ቂጡ የተወጋ ውሻ እንደ ልቡ አይጮኽም
- ቁስና ንብ እያየ እሳት ይገባል
- ቅል ባገሩ ደንጊያ ይሰብራል
- ቅቤ ይፍሰስ ከገንፎ አይለፍ
- ቅዠት ተፈርቶ ሳይተኛ አይታደርም

## በ - ቢ - ባ - ቤ - ብ

- በሁለት ብትር አማይቱ በሁለት ዳኛ አማይጐቱ
- በልቶ የማይመርቅ ገበያ ወጥቶ የማይጠይቅ (ከብት)
- በልቶ እንደ አንበሳ ተኝቶ እንደ ሬሳ
- በልጅ አመካኝቶ ይበሏል አንጕቶ
- በል በል ይላሉ ሲፈርዱ ጣል ጣል ይላሉ ሲያርዱ
- በለፈለፉ ባፍ ይጠፉ። በልብ አምኖ በአፍ መንኖ
- በልቶ መጠጥ ያጣ ተበድሎ ፍርድ ያጣ
- በልቶ የከሳ የነገሩት የረሳ በማር አጠገብ ውኃን ጥገብ
- በሐምሌ ወጨፎ በሰኔ አርከፍክፎ
- በኋላ የመጣ ዓይን ወጣ በኋላ የመጣ እጅ ይዞ አስወጣ
- በመቃቀም የተቋመ ፍቅር አይውል አያድር
- በሚያዝያ ጐመን የዘራ ክረምቱን ሁሉ በላ
- በሞኝ ክምር ዝንጀሮ ልጅዋን ትድር
- በሰኔ ካልዘሩ በጥቅምት ካልለቀሙ እህል የት ይገኛል
- በድንበር ቢቆሙ። በምን በላህ በሳማ ባያፈጅህማ
- በማያድሩበት ቤት አያመሻሹበት
- በሰም የተጣበቃ ጥርስ ቢስቁበት እንደምቅ ቡበሉበት አይደቅ። በሰማንያ አይቀጥሉ በእርጥብ አያቃጥሉ
- በሰማንያ ያለቀ በፀሐይ የደረቀ
- በሰማንያ የተረታ ማኸል አገደው የተመታ
- በሰማይ የለም ጠጠት ባባት የለም ቅጣት
- በሰማይ የለ ዱር በቁስ የለ ግብር
- በሰው ምድር ልጅዋን ትድር። በሰበቡ መምሬም ተሳቡ
- በሰፈሩበት ላንዳ በመዘኑበት ሚዛን
- በሬ ተሸካሽኮ ቀንበር ገብሬ ተቸካሽኮ ድምበር
- በሬና በሬ መከሩ ቀንበርን ሊሰብሩ
- በሬ ያርሳል አህያ ምርቱን ያፍሳል
- በርበሬ አይሆን ዕጣን ነገር አይሆን ሥልጣን
- በርበሬ ታፈጀ ጠበቃ ታፈጀ
- በባዳ ቢቆጡ በጨለማ ቢያፈጡ ምን ያመጡ
- በሮች ተረት ለመዱ ዝም ብለው እንዳይጠመዱ
- በስለ እንብላ ደረሰ እንዝራ። በሰው ቂማ እጅዋን ትቃማ
- በሰፌድ ያሰጣ በእንቅብም ያሰጣ እኩል ለኩል ወጣ
- በሰጡበት አገር አምኖ ማደር የማይመች ነገር
- በስለት የተመተረ ባጤ ይሙቱ የተከተረ
- በሸማግሌ የታረቀ በፀሐይ የደረቀ አለቀ ደቀቀ
- በቃል ያለ ይረሣል በመጽሐፍ ያለ ይወረሳል።
- በቅሎ እንዳሠገሩት ሎሌ እንደ ነገሩት
- በቅሎ ግዙ ግዙ አንድ ጨው ላያግዙ
- በቅሎ እንደ አሰጋገሩ ሎሌ እንዳስተዳደሩ
- በቅሎ ከሸጠ የሸመጠጠ በለጠ
- በሸሮ ላይ ቅቤ ተጨምሮ አማረ በእሑድ ላይ በዓል ተጨምሮ ከበረ። በበትሩ አይመታ በዘመዱ አይረታ
- በበጋ እሞኝ ቤት ተንጋጋ በክረምት እንደ ጭልፊት እየቤትህ ግባ። በበባላህ ገብር በሰማህ መስክር
- በተሳለ ያርዷል በታየ ይፈርዷል
- በተተከለው ግንድ በተፈተለው ገመድ
- በተለሙ ያርሷል በጀመሩ ይጨርሷል
- በትር ለገና ነገር ለዋና። በትኩስ ሥጋ በርጥብ ፍለጋ
- በትንሽ ማረሻ ትልቅ እርሻ
- በንጉሥ ሞት አይዘበት በዝሆን ሐሞት አይፈተፈት
- በአፉ ያመነ ከሥሩ የመነመነ

- በአፍ ስሕተት በእግር መንሻተት
- በዓይን ጥቅሻ በከንፈር ንክሻ
- በዕውር ይጠቃቀሱበታል በደንቆሮ ይንሾካሾኩበታል
- በዓል ሽሮ የከባረ ጦም ገድሮ የወፈረ (የለም)
- በከብቱ የለገሰ በወደሉ የገሰገሰ ካሰበው የደረሰ
- በካሣ የከበረ በአኅት የሰከረ (የለም)
- በክረምት ካረሰ እናቱን ያስመነኰሰ
- በወሬ አትጥላኝ በስመ ጅብ አትውጋኝ
- በወሬ አይነግሡ በእጅ አይካሱ (በቊንጫ አያርሱ)
- በወር ልቅ ባመት ቀሚስ ጥልቅ
- በዋስ ያለ ከብት በጣት ያለ ቀለበት
- በውል ከሄደች በቅሎዬ ያለ ውል የሂደች ቆሎዬ
- በውርርድ ላይ ውርርድ ከነብር ላይ ስማርድ
- በዘጠና የለም ጤና። በዘመኔ ይድላው ለወገኔ
- በየዕለቱ ይወርዳል ዓመቱ። በየወንዙ ብዙ ነው መዘዙ
- በደግነቱ ተቄረጠ አንገቱ
- በደንባራ በቅሎ ቃጭል ተጨምሮ
- በገዛ ጌታ እግሩን ይመታ። በገና ጨዋታ አይቆጡም ጌታ። በገና በሰው እጅ ያምር ሲይዙት ያደናግር
- በጊዜ የገባ እንግዳ እራቱ ፍሪዳ። በጊደር ጥገት በጥሬ ዱጨት። በጋለሞታ ቤት ሁሉ ይጣላበት
- በግዜሄር ቢቆጡ በጨለማ ቢያፈጡ ምን ያመጡ
- በጎውን አማጭ መጦር ክፉውን አማጭ በጦር
- በጠራ ተሻገር በተሳለም ምተር። በጥንስሱ የተቀዳ በጨርቋው የተጐዳ። በጣይ በጉባይ (በፀሐይ በጉባኤ)
- በጦም ቆሎ በዳገት በቅሎ በቅሎው ይነካል ቆሎው ይከካል። በጥቂት በጥቂት ይሞላል ልቃቂት
- በጨው ደንደስ በርበሬ ይወደስ። በጥር ሠርግ በግንቦት በልግ። ቢሰጡኝ እንዳ ቢነሡኝ ኣረዳ
- ቢተኙ ነገር ያገኙ። ቢነሡ ነገር ይረሱ
- ቢያዩኝ እስቃለሁ ባያዩኝ እሰርቃለሁ። (ይላል ሌባ)
- ቢያብዱም ቢጨምቱም ያንዱን ነገር ላንዱ ኣያጫውቱም
- ቢያዝኑለት ያለቅስ ቢስሙት ይነክስ
- ቢጠረጥሩ ጠጠር ይጥሉ። ቢጨንቀን ሾጤ ሆነን
- ቢፈሩት አይቀር ሞትና ነገር። ቢከማች ዕዳው ላንች
- ባህያ ቆዳ የተሠራ ቤት ሲፈርስ ያድራል ጅብ የጮኸ ለት
- ባለጌ ካወራው የጭዋ ልጅ ያሰበው
- ባለጌ ኣያዝንም ለገበረ ያዝናል ባልጀራው ለቀረ
- ባለጌና የቆቅ አውራ በራሱ ያወራ።
- ባለቤት ከቤት ጠበቃ ከችሎት
- ባለጌ ያለበት ሸንጎ ዝምብ የገባበት እርጎ
- ባላዋቂ ቤት እንግዳ ናኘበት። ባላደራ ጮኸ ከተራራ
- ባልነቃ ሰንጥቆ ባልደመነ በርቆ
- ባለጠጋ በድሎ ይቆጣል ድኻ ተበድሎ ይለማመጣል
- ባልንጀራህ ሲታማ ለኔም ብለህ ስማ
- ባልዋጁበት ጣት የዘንዶ ጉድጓድ ይለኩበት
- ባለቤት ሲተዋወቅ የሠርገኛ ልብስ ይደርቅ
- ባልፈሸሽ በኖብሽ ባልነበርሽ በቆብሽ
- ባልና ሚስት ፍትሕና መንግሥት
- ባበደሩበት አገር ተበድሮ በሰጡበት ተቀባጥሮ
- ባልንጀራህ ከሚበልጥህ ቊንጣን ይግደልህ
- ባሕር ዛፍ ለማገር ጉራጌ ለነገር። ባረገዘች ክታቡን ያዘች
- ባቄላ ላይሰበር መነኮሴ ሳይቀበር
- ባርያ ቅቤ ለምዶ እንግዲህ ማን ሊሸከም ነዶ
- ባንድ ከፈጩ የለም እመቤት። ባንድ ከበሉ የለም ዳረጐት። ባስተጋባ ባሕር ሆዴ ገባ
- ባርያና ውላጅ ሽራቢና ገማጅ። ባርሃ ሲኰራ በዱላ
- ባርያ ባንደበቱ ውሻ በዥራቱ። ባንድ ወናፍ ሁለት አፍ
- ባርያ ካልሰረቀ ሰማይ ካልፈለቀ
- ባርያ ሲጠግብ ሸንጎ ኣህያ ሲጠግብ አምቦ
- ባሮች አግዙ ላህዮች ኣህዮች አግዙ ለባሮች
- ባተ - መልካም ሲሆን ለመሮጥ ባይሆን ለጌጥ
- ባንድ ራስ ሁለት ምላስ። ባንድ አጕራ ሁለት አውራ
- ባንዱ ታዘብ ተለዘብ። ባንድ ፪ት በጥሬ ዱጨት
- ባንዱ ቀን ስተቱ ዘላለም ይጸጸቱ።

- ባንድ ዙፋን ፪ት ንጉሥ ባንድ አፍ ሁለት ምላስ
- ባወጡት ዳኛ ቢረቱ በቁረጡት ቸንገር ቢመቱ የግዚሄር ግቡ ከብቱ። ባወጣኸው ዳኛ ትሆን አሣረኛ
- ባይኔ ኣልቅሼ በእጄ አብሼ
- ባልሞገትከብት ተፈረድ ባልወጣህበት ውረድ
- ባጭር ታጠቆ ጋሻ ነጥቆ ዘገር እንቅንቆ ይዋጋዋል አጥብቆ
- ባገባቡ በደጃፉ ይገቡ። ቤት ያለ ኣጥር ሬሳ ያለ መቃብር
- ባጉራ ጠናኝ የተረታ ማኽል አገዳውን የተመታ
- ባፈሳ ይታፈሳል በነጠረ ይመለሳል
- ባፈሳ ይወረሳል በንጥጥር ይመለሳል። ቤት ያለመውጫ ፊት ያለ አፍንጫ ያ መንፈጫ ያ ሙገጫ
- ቤተ ክርስቲያን ለማላጅ ገበያ ላርፋጅ
- ቤት ያለ ቊልፍ አልጋ ያለ ምንጣፍ
- ቤተ ክርስቲያን ተኳሽ ዕርቅ አፍራሽ። ቤት ያለ ሴት ከብት ያለ በረት አይሆን ለንብረት
- ቤት ያለ አጥር ቤተ ክርስቲያን ያለ ቅጥር
- ቤት ከነ ጒልላቱ አጥር ከነ ማዕዘንቱ
- ቤት የሌለው ቤቱ ይስጠ ችግሩን እንዲያውቀው
- ብላ ያለው ቀርቦ ተሸከም ያለ ተሰብስቦ (ይቆየዋል)
- ብላ የበሰለ ተናገር የመሰለ። ብርሌ ከነቃ አይሆንም ዕቃ
- ብልጥና ምስጥ ውስጥ ለውስጥ
- ብረት ሲግል ቀጥቅጠው ንፋግ ሲወድ መጥምጠው
- ብላ ለከርሥህ ፍረድ ለነፍስህ
- ብልህ ያመቱን ሞኝ የዕለቱን (ያስባል)
- ብርቅና ድንቅ አለ ፩ ጊዜ አይደምቅ
- ብርድ ቆላ ወረደ ልጅ አባቱን ወደደ። ብዙ ገንዘብ ያለው ይደፈራል ብዙ ወንድም ያለ ይታፈራል
- ብዙ ቢወልዱ ሙያውን ግብሩን አይተው ፩ዱን ይወዱ
- ብዙ ቢያወጉ ይዘነጉ። ብዙ ቢተቹ ይሰለቹ
- ብዙዎች ለብዙ ሲያውቁ የራሳቸውን አይጠነቅቁ
- ብዙዎች ይስጡህ ብዙዎች አይጥሉህ (አይቆጡህ)
- ብነጨው ፊቴን ብመታው ደረቴን

## ስድ ምሳሌ

- በለምለም ምሳሌ ኲሸሽላን በላሁበት (አለች አህያ)
- በሰላም ጊዜ ያልመከሩት በመከራው ጊዜ ልምከርህ ቢሉት አይሆንም። በሰው ቊስል እንጨት ቀርቅርበት
- በሰላም ጊዜ አለሁልህ ያላሉት በመከራ ጊዜ ቢጠብቁት አይገኝም። በሬ ባንጀቱ እንጂ ባንገቱ አይስብም
- በመሸታ ቤት የተገዛ ጦር ቢወረውሩት ከድፍድፍ
- በራቸውን ከፍተው ሰውን ሌባ ይላሉ
- በቂል ከምር ዝንጀሮ ይማታበታል
- በቅሎ ማሰሪያዋን በጠሰች በራሷ አባሰች (አሳጠረች)
- በቅሎ ማን አባትህ ቢሉት ፈረስ አጐቴ አለ
- በቆሎ እየሳቀ ያርራል (እያረረ ይስቃል)
- በትንባሆ የተገዛ ጦር ቢወርውሩት ጋያን ይወጋል
- በእርሻ ጊዜ ያልዘራ በመከር ጊዜ አይሰበስብም
- በእጅ የያዙት ወርቅ ከብረት እኩል ነው
- በአይጥ ሽንት የተሠራ ቤት ድመት ሲጮህ ይፈርሳል
- በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ። በደል ዋና አጥታ ትኖራለች
- ቢወዱኝ ብሎ የሞተ ቢጠሉትስ ምን የምጣበት ነበር?
- በዕውር ቤት አንድ ዓይና ብርቅ ነው
- በዝሆን ጆሮ ትንኝ። በዝሆን አፍ ቅርፍት።
- በደቦ የተሠራ በደቦ ይፈርሳል (ደቦ ወበራ)
- በጥባጭ ስላእ ማ ጥሩ ይጠጣል?
- በጫማ የሚሄድና በቃርያ የሚበላ ሰውን አይጠበቅም።
- በግ ባልበላሽ ትበይኝ!! እላ ጅብ
- በገዛ ዳቦዬ ልብ ልቡን አጣሁት
- በፊት የወጣን ጆሮ በኋላ የወጣ ቀንድ በለጠው
- በፋሲካ የተገዛ ባሪያ ሁልጊዜ ፋሲካ ይመስለዋል
- ባለጌን ከሳደገ የገደለ ይሻላል
- ባለቤቱን ከፊቱ ማመስገን ከሐሜት እኩሉ ይቆጠራል
- ባለቤቱ ያከበረው አህያ በቅሎ ያላውጣል

- ባለቤቱን ካልናቁ ውሻውን አይመቱም
- ባለቤቱን ካልጮኸ ጎረቤት አይረዳም
- ባለቤቱ ያቀለለውን አሞሌ ባለ ዕዳ አይቀበለውም
- ባሌን ጎዳሁ ብላ ዓይኗን በእንጨት ወጋች
- ቧልትና ቅዘን ቤት ያስፈታል። ባዋቂ ፊት መናገር መታገም
- ባልና ሚስት ካንድ ባሕር ይቀዳሉ።
- ባርያ ረዳት ቢያመጡላት መጇዋን ደበቀች
- ባባትህ አገር አትቀማ በናትህ አገር ጦም አትደር
- ባባቱ ፊት የሚናገር አፉ ለምጣም
- ብቻውን የሚበላ ብቻውን ይሞታል
- ብቻውን የሚሮጥ የሚቀድመው ብቻውን የሚሚገት የሚረታው የለም። ብልጥ ዓይን አስቀድሞ ያለቅሳል።
- ብዙ ከማዳመጥ ጥቂት መናገር ብዙ ከመናገር ጥቂት ማሰብ ይበልጣል። መናገር ምላስን ያላሻል።

## ተ - ታ - ት -

- ተለማማጭ አልማጭ ተለጣጭ የጎረቤቷን ድልህ ሚጣች። ተልባ ቢንጫጫ በአንድ ሙገጫ
- ተላም የዋለ በሬ ከጋለሞታ የዋለ ገበሬ
- ተልባ በቅባ ኑግ ለሰሚው ግራ ለበይው መልካም ነው
- ተመሞት ይሻላል መሰንበት
- ተመመልከት ዓላማህን ተከተል አለቃህን
- ተመመራመር ይገኛል ቁም ነገር
- ተመሮጥ ይሻላል ማንጋጠጥ
- ተመከሮ ልብ ተሸምቶ ድልብ አይሆንም
- ተማሪና ዶሮ በሞቱ ክቡር ነው በቁመናው እራቱ ጥሬ ነው
- ተምሮ የማይጽፍ አከፍሎ የማይገድፍ
- ተምሮ ያላስተማረ ዘርቶ ያላጠረ
- ተሰው ጋር አለሁ ብዬ ተጅብ ተዳብዬ
- ተሰብሮ ቢጠገን እንደ ድሮው አይሆን
- ተስፋ መስጠት እያዩ ዕዳ መግባት
- ተስፋ ቆርጦ ፩ ላይ ከመቆም ይሻላል በተስፋ ሲጓዙ መከረም። ተቀዳዳ ይሻላል ጨምዳዳ
- ተሺ ምስክር የታቦት እግር። ተመምሩ ደቀ መዝሙሩ
- ተቀማጭ የሌለው ተሚጋች ስልቻ የሌለው አንጓች
- ተቀመጥ በወንበሬ ተንገር በከንፈሬ
- ተቁም ዶሮ ተሸከላ ማሰሮ
- ተቁመትህ ማጠሩ ሆድህ መጠጠሩ
- ተረት ለነገርህ ይሆናል መሠረት
- ተረታን እንዳይሉ ይግባኝ ይላሉ
- ተራራ ለጥናት ውኃ ለጥማት
- ተባቂላ አይጠፋም ዲቃላ ተጠላ አይታጣም አተላ
- ተናዝዞ ይሞቷል አስይዞ ይሚገታል
- ተናግሮ አናገረኝ ይወስደኝ ይመስል ሄዶ ተናገረ የላከሁት ይመስል። ተናካሽ ውሻህን ተዋጊ በሬህን
- ተናግሮ አናግሮ የሆድን ጨርሶ ጠላት ይሆናል ወዳጅ ተመልሶ። ተናግሮ ከማሰብ ከንፈርን መሰብሰብ
- ተንጋሎ የተፋ ለራሱ ከፋ
- ተኛ ወዲያ ጎራሽ እህል አበላሽ
- ተዝካር ያየ ተማሪ ሽቀጥ ያየ አጣሪ
- ተወፈሩ ፈጣሪን አይፈሩ ሰውን አያፍሩ
- ተዋሰኝ ግዝት ይሆነኝ አበድረኝ አይማረኝ
- ተው ፈረሴን ለጉም ሊጋላና ለጉም አይዘነጉም
- ተድረው ቢመለሱ የውኃን መንገድ ረሱ
- ተዳኛ ተሚግቶ ታድያማ ተዋግቶ!!
- ተገናኝተው ሳሉ ምን ጊዜ እንገናኝ ይላሉ
- ተግደርዳሪ ጦም አዳሪ ቀላዋጭ ቀባጣሪ
- ተጠንቀቅ ወደል እንዳትገባ ገደል
- ተጥዶ የማይፈላ ተሹሞ የማይበላ (የላም)
- ታላቁን ነገር እየተመኘሁ ቢከፍቱት ተልባ ሁኜ ቀረሁ
- ታልቸኰል ቀስ በቀስ ይገኛል ሁሉ
- ታሞ የተነሣ እግዚሄርን ረሳ
- ታርቄ ተመርቄ ታጥቤ መጠንቀቅ
- ታስሮ ከመማቀቅ ይሻላል መጠንቀቅ

- ታጥቀህ ታገል እንዳትንገላታ አስተውለህ ተሟገት እንዳትረታ። ታላቅ ጦር ባይወጉበት ያስፈራሩበት
- ታዝበው ኪጠሉህ ታዝበው ይውደዱህ
- ትለብሰው የላት ትከናነበው አማራት
- ትምህርት የማያልቅ ሀብት (ምርት)
- ትምህርት በልጅነት አበባ በጥቅምት
- ትንሽ ሥጋ እንደ መርፌ ትወጋ
- ትንቢት ይመራል ልጓም ይገራል
- ትንሽ ምላጭ አገር ትላጭ። ተሞኝ ደጅ ሞፈር ይቆረጣል
- ትንኝ ለሆዱ ዝሆን ለሆዱ ተያይዘው ወንዝ ወረዱ
- ትኩሱ ሬሳ ደረቁን አስነሣ። ቶፋ መቀበሪያው ፈፋ
- ተልባ መስሎሽ ሰናፍጭ ትቀምሽ

## ስድ ምሳሌ

- ተመረቅሁ ብለህ ከተረገመ ጋር አትዋል
- ተቀምጠው የሰቀሉት ቁሞ ማውረዱ ያስቸግራል
- ተኚ ብለሽ አትነሺ አልኩሽን?
- ተከናንቦ የሚበላውን ተጐንብሰህ ግባበት
- ታላቅ ወንድም እንደ አባት ይቆጠራል
- ትንሽ ቆሎ ያደርሳል ካሻሮ

## ነ - ኑ - ን

- ነቢያት በመደመዱ ሐዋርያት ገደገዱ
- ነገር በምሳሌ ጠጅ በብርሌ መዝሙር በሃሌ
- ነገር በዋና ዘፈን በበገና። ነገር በዋስ እህል በነፋስ
- ነገር ቢሳሳት ከጧቱ ጥጃ ቢሳሳት ከናቱ
- ነገርን አዳምጦ እህልን አላምጦ። ነገር ከሥሩ ውኃ ከጥሩ
- ነገር ከዋስ ምላስ ከጥርስ። ነገር በዕርቅ መንገድ በደረቅ
- ነገር በመልከኛ ጠላ በመከደኛ። ነገር ከግቡ ጋሻ ከንግቡ
- ነገር ካንሺው ሥጋ ከጠባሺው
- ነገር ያለ ዳኛ ተረት ሰማይ ያለ ደመና ብረት
- ነገር በዋናው ንብ በአውራው። ነገር ባዋቂ ብረት በጠራዊ
- ነገር ሲጀመር እህል ሲከመር
- ነገር ነገርን ያነሣዋል ጥጋብ ሞትን ያስረሳል
- ነገር ከመፈለግ ይሻላል ነግ ፈረግ
- ነገር አንሺውን እሾህ አጣሪውን (ይወጋል)
- ነገር እንዳገቡት ሙከት እንዳሰቡት
- ነገር ነገርን ያመጣል ድግር አፈርን ያወጣል
- ነገር በነገር ይወቀሳል እሾህ በእሾህ ይነቀሳል
- ነገር ከምጩ ውኃ ከምንጩ። ነገር ለሰሚ ውኃ ለተጠሚ
- ነገር በወቀሳ በደል በካሣ። ነገር ለበለጥ ውድማ ለመለጥ
- ነገር ለጀማሪው እሳት ለጫሪው
- ነገር የዋለበት ዳኛ ያውቃል ከብት የዋለበት እረኛ ያውቃል። ነገር ካጀማመሩ እህል ካከማመሩ
- ነገር ከመጀመሪያው እህል ከመከመሪያው
- ነገር እንደ አፉ ዛፍ እንደ ቅርንጫፉ
- ነገር ያለ ዳኛ ትብትብ ያለ መጫኛ
- ነገር ወዴት ትሄዳለህ? ወዳገር
- ነገር ስንት ነው? ሁለት ምን ያበዛዋል ውሸት
- ነገር በዋና ሚዶ በእረኛ። ነገር ከፊቱ ዱቄት ከወንፊቱ
- ነገር ከመጀሪያ ፍሊጋ ከመሻገሪያ
- ነገር የሻ ዳኛ አምጡ ይላል የዶሮ ሻኛ
- ነገር ሳያውቁ ሙግት ዓቅም ሳይኖር ትዕቢት
- ነገር ሲያመልጥ ራስ ሲመለጥ (አይታወቅም)
- ነገረኛ ናቸው አጥልቃችሁ ቅበሩዋቸው የተንሡ እንደሆን ብዙ ነው ጣጣቸው። ነገሬ በከንፈሬ
- ነገሬ በሆዴ መንገዴ ባመዴ። ንጉሥ ለብያኔ አቡን ለኵነኔ
- ነገርኩት መስዬ እንዲመስለው ብዬ
- ነጭ እንደ ሽማ ትክል እንደ ትርሽማ
- ነፃነት ያኰራል ሥራ ያስከብራል
- ነፍጥ ቢያጓር የጌታውን ጐን ይሰብር

- ኑሮ ያናኑራል ሕግ ያከባብራል
- ኑሮ በጸጋ መቀመጥ በአልጋ ታላቅ ጸጋ
- ኑሮ ኑሮ ከመሬት ዙሮ ዙሮ ከቤት (አይቀርም)
- ንብ ቢሂድ ካጥር ሰው ቢሰደድ ካገር
- ንጉሥ ሲሞት ግምቡን ብልህ ሲሞት ልቡን
- ንብ በአውራው ገበሬ ባዝመራው
- ንጉሥ የፈረደበት መርከብ የተሰበረበት (አንድ ነው)
- ንጉሥ አንጋሹን ቤተ ክርስቲያን ቀዳሹን
- ንጉሥ ከሾመው ማረሻ ይሾመው
- ንጉሥ ይተከላል ንጉሥ ይነቀላል
- ንጉሥ በመንግሥቱ ጕልማሳ በሚስቱ አምላክ ባምላክነቱ ገበሬ በርስቱ ቢገቡአቸው ቀናተኞች ናቸው
- ንጉሥ በዘውዱ ድኻ ባመዱ
- ንጉሥ የሰቀለው አንበሳ የሰበረው
- ንጉሥ አይከሰስ ሰማይ አይታረስ አባት አይወቀስ
- ንጉሥ ያላቸው ንቦች ማር ይበላሉ ንጉሥ የሌላቸው ዝምቦች ጥብም ይልሳሉ። ንጉሡ ቢሞቱ ከማን ይሚገቱ
- ንጉሡ ሲቆጡ ቀስ ብላችሁ ውጡ
- ንጉሥ ከተነፈስ ውኃ ከፈሰሰ
- ንጉሥ የወደደው ዘመን የወሰደው
- ንጉሥ ይሞግትልህ ንጉሥ አይሞትህ
- ንግግር ሲበዛ ያጠፋል ማር ሲበዛ ያስተፋል

## ስድ ምሳሌ

- ነበረ እንጂ ይኖራል የሚባል ፍጡር የለም
- ነገር ቢበዛ በአህያ አይጫንም
- ነፋስ ሲነሣ እሳት አይጫርም
- ነገር እንዲጠፋ ዳኛውን ግደል
- ኑሮ ካሉት መቃብርም ይሞቃል
- ንብ ሲሠማራ አጥሩን ተመልከት
- ንጉሡ በድንኳናቸው እኔ በጎጆዬ (ንጉሥ ነን እለ ድኻ)

## አ - ኧ

- አህያ ሰባ ካልተበላ ምን ረባ?
- አህያ ሲግጥ ደብተራ ሲያላግጥ (ይሞታል)
- አህያና ጓያ በአምሳያ። አህያ ለሰርዶ ድኻ ለመርዶ
- አህያው በፈሩ መደላደሉን ሰበሩ
- አህያና ፋንድያ አራዳና ገበያ
- አህያ ታመዱ ሰው ተዘመዱ
- አህያ ሲጭኑ ፫ት ሆኖ መንገድ ሲሄዱ ፪ት ሆኖ
- አለ ፩ድ የላት ጥርስ በዘነዘና ትነቀስ
- አለ አባት ጐመን ባጓት። አለቃ ለራሱም አልበቃ
- አለ እኩያ ጋብቻ ቆይ ብቻ ቆይ ብቻ
- አለ ዋንጫ አይስማት አለ ቀንጠፋ አይስባት
- አለ አሽከር በቅሎ አለ ወንድ አምባጓሮ
- አለቅትና ድኻ ውኃ ለውኃ። አለ ባለቤቱ አይነድም እሳቱ። አለቃ ያውቃል ድኻ ይጠይቃል
- አለባብሰው ቢያርሱ ባረም ይመለሱ
- አለት ለረገጠ ፍለጋ የለው ውኃ ለጠጣ ሽታ የለው
- አለ ድኻ ዘውድ አለ ገበሬ ማእድ (አይገኝም)
- አለ ራቱ አያቀርስ አለ ረጅቱ አይወርስ
- አለ ባል ሴት ወይዘሮ አለ ማንገቻ ከበሮ
- አለ ወንድም ጋሻ አለ ድግር ማረሻ
- አለ ዳኛ ቀጠሮ አለ ቅቤ ዶሮ
- አለ ጨልማ ፍራት አለ ዘመድ ኩራት
- አለኝ ብሎ ከማፈር የለኝም ብሎ መድፈር
- አለፈ በዋዛ ልብን ሳልገዛ
- አሉ ብሎ የተረታ ማኸል አገዳውን የተመታ
- አላርፍ ያለች ጣት እር ጠንቁላ ወጣች
- አላውቅም አስገድሎ አያውቅም
- አላጋጭ ገበሬ ይሞታል በሰኔ
- አመል ያወጣል ከማኸል አመል በጥፊ ይበልህ
- አመልህን በጉያ ስንቅህን ባህያ
- አመል ሳይቀር ቅጣት ሞት ላይቀር ፍራት
- አመስጋኝ አማሳኝ። ዓመት የሚያበላ ዓመት ያጣላ

- አማቻችን አፈኛ ቢመስለ ወደኛ
- አማትና ምራት ሳይስማሙ መሬት (እሳትና እራት)
- አምሳ ዳቦ ከመላስ አንዱን መቅመስ
- አምባ ያለው ፈሳሽ ወንዝ ያለው መላሽ
- አሞራን ሲበሉ ስሙን ዥግራ ይሉ
- አሞራ በዛፍ ውርርድ በጫፍ
- አሣምር ያሉት አያከፋ ጠብቅ ያሉት አያጥፋ
- አሳማ በበላ ጉፍጠራን በዱላ
- አስፍቶ ከማረስ ከበላተኛው መቀነስ
- አሥራው ካሉ አፅውቅ ይገዳሉ
- አሮጌ ማሳ ደረሰ ለንጀራ ልጅ ያጐረሰ
- አበ ልጄ አትቁም ከደጄ። አበባ እያገርህ ግባ
- አበድረኝ አይማረኝ ተዋሰኝ ግዝት ይሁነኝ
- አባት ሳለ አጊጥ ጀምበር ሳለ ሩጥ
- አባት አይክሰስ ሰማይ አይታረስ ውኃ አይጠበስ
- አባት በነውሩ ይከሰሳል ሰማይ በመብረቅ ይታረሳል
- ውሃ በእሳት ይጠበሳል። አባት ያበጀው ለልጅ ይበጀው
- አባቱን ርስቶ ላማቱ ይነጭ አማቱን ጋርዶ እናቱን ያስፈጭ
- አባት ጨርቋን በጐረሰ የልጁ ጥርስ አጠረሰ
- አባቱ ዳኛ ልጁ ቀማኛ። አባት ሲታማ ልጅ አይስማ
- አባያ ቢቀና ቤት ያቀና። አባትና ጋሻ ምስክርም አያሻ
- አባት የሌለው ልጅ መዝጊያ የሌለው ደጅ
- አባት የያዘውን ልጅ ይወርሳል እጅ የያዘውን አፍ ይጐርሳል። አባቱን ያላወቀ አያቱን ናፈቀ
- አብረው የተጠመዱ አብረው ይፈቱ አብረው የበሉ አብረው ይሞቱ። አብ ሲነካ ወልድ ይነካ
- አብሮ መኖር ያናንቃል አብሮ ማደግ ያሳስቃል
- አተርፍ ባይ አጉዳይ አልሞት ባይ ተጋዳይ
- አተኳኰስ እንደ አሞጋች አኰራኰር እድነ ጋሎች
- አታላይ ለጊዜው ያመጣል በኋላ ይሰምጣል
- አታላይ ጉድባ ዘላይ። አታላይ ወደታች ሲሉት ወደላይ
- አትኩራ ገብስ ጐመን ባወጣው ነፍስ
- አትዋልባቸው ይዋሉብህ አትምከርባቸው ይምከሩብህ እንዲያው ያወጣሃል ቅን ከሆነ ልብህ
- አትግደርደሪ ጦምሽን እንዳታድሪ
- አትጥላኝ በወሬ ሳታጣራ ነገሬ
- አንበሳ ምን ይበላል? ተበድሮ ማን ይከፍላል? ማን ተናግሮ። አነጋገራችን እንደየ ጠባያችን
- አንተ ሌባ እኔም ሌባ ምን ያጣልናል ብሰው ገለባ
- አንተ ግፋኝ እሥጋ ላይ እኔም እወድቃለሁ ከላይ
- አንተ አብጀው አስቤም አልፈጀው
- አንካሳ ያለው ደብር አዞ ያለው ባሕር ሳይበጠበጥም አያድር። አንድ ቀን ቢስቱ ዘላለም ይጸጸቱ
- አንደበቱ ከጸሎት እጁ ከምጽዋት (ያልተለየ)
- አንደበቱ ሰውን ከመበደል እጁ ሰውን ከመግደል
- አንድ ዓመት ከርተት አንድ ዓመት ሰርተት
- አንድ ወናፍ ሁለት አፍ። አንድ በሬ ስቦ አንድ ሰው አስቦ። አንድም ምረጥ አንድም ቍረጥ
- አንድ ምስክር አያስደነግጥ አንድ ዓይን አያስረግጥ
- አንድ ዓመት በወዝ አንድ ዓመት በደመወዝ
- አንድ ዕንጨት አይነድ አንድ ሰው አይፈርድ
- አንዱ ባንዱ ሲስቅ ጀምበር ጥልቅ
- አንድ ዓመት እንዳይማሩ ፯ ዓመት ያፍሩ (ይደነቍሩ)
- አንድ ዓመት ወር ድንጋይ ጠጠር (አይሆንም)
- አንድ ወሬኛ አገር ይፈታል አንድ ቅማል ሱሪ ያስፈታል
- አንገቷን ደግፈው ቢያዘፍኗት ያለች መሰላት
- አከፋፈል ለዕለት አሳሳብ ለጥንት
- አዋቂ ይረደኝ ሸንነ ይፍረደኝ። አንድነት ያገባል ገነት
- አዋጅ ቢያስነግሩ ልዩ ነው ምክሩ
- አውራ የሌለው ንብ አለቃ የሌለው ሕዝብ
- አውቆ የሚያጠፋ ኑሮው ምን ይከፋ
- አውቆ መተው ነገሬን ከተተው። (ለእግዜር ይመቸው)
- አዎን ማለት መረታት አለ መመከት መመታት
- አዎን ባይ ዕዳ ከፋይ አሉ ባይ ሞት ተቀባይ
- አዎን ብለህ ተሟገት አሉ ባይ ሞት ተቀባይ
- አዎን ያለች ምላስ እናት የሌላት አራስ

- አዎ ያለን አያሚግቱ እሺ ያለን አይሙቱ
- አውቀው በድፍረት ሳያውቁ በስሕተት
- አዘኑ ላይለቅህ ድግሡ አይራቅህ
- አዘዞ አንድም ተናዝዞ አንድም ስንቅን ይዞ
- አየሁ ያለ ጣጣ ያመጣል አላየሁም ያለ ከጣጣ ያመጣል
- አያተርፍ አይነግድ አይተች አይፈርድ
- አያጥብ ለባሽ አይረታ ከሳሽ አያርም አራሽ
- አያስገሳ ኮሶ የታባቱ ደርሶ። አይጥ በበላ ዳዋን በዱላ
- አያገባት ገብታ አያወዛት ተቀብታ
- አይቡ ዳኛ ቅቤው መልከኛ
- አይቡን ሲያዩት አጓቱን ጠገቡት
- አይሆንም እንጂ ከሆነማ ከመጋዞ ይሻላል ጉልማ
- አለ ጉልበት ሰኰና አለ ራስ ጐተና
- አይጥም ጠላ ባልና ሚስት ያጣላ (ከጐረቤት ያጣላ)
- አይጧ ጣረሞት ተይዛለች ድመቲቷ ትጫወታለች
- አይጥ በድመት አፍንጫ ወርዶ አህያ ታሥሮ ከሰርዶ
- አይጥ ለሞቷ የድመት አፍንጫን ማሽተቷ
- አይጽፍ ደብተራ ክንፍ የሌለው አሞራ
- አይፈስ ውኃ አይሰደድ ድኃ (የለም)
- አደራ ቢሉዋቸው ይብሳሉ እሳቸው
- አደንጓሬ የእህል አውሬ። አደን ያስረሳል ኃዘን
- አድረው ሊለያዩ አመልን ያሳዩ
- አድራሽ ተመላሽ ቀበኛ ደንጊያ ላሽ
- አገር ያደረገው ዘንዶ የወረው
- አገር የሌለው ለጌታ አዳሪ ማጭድ የሌለው ወራሪ
- አገር ያጣ ስሜን ምግብ ያጣ ጐመን
- አገርህን ወዴት ነው? ማርያም ውኃ ወንድሜ ነሃ?
- አጉል ፍቅር ያመናቅር አጉል ንግግር ያደናግር
- አጉል መጋባት መጋማት። አጋጨው እንደ ነጋዴ ጨው
- እጉሊንጥ ባልንጀራ እንብላ ሲሉት እንራ
- አጤ ከሞቱ በማን ይሚገቱ። አጤን መደብ እቴጌን ገደብ
- አጥብቀህ ጉረስ (ጉርስ) ወደ ዘመዶችህ ተመለስ (ምልስ)
- አጥልቆ የሚያርስ ጀምሮ የማይጨርስ
- አጥንት ፈጭ ዝርዝር ቀጭ። አፈኛ ባፉ ኃይለኛ በመዳፉ
- አፉ ከኛ ልቡ ከነኛ (ልቡ ከወሬኛ)
- አፍ ያለው ጤፍ ይቆላል ራሱ ተናግሮ ሰውን ያናግራል
- አፍ ሲድጥ ከዕዳ እግር ሲድጥ ከአንጋዳ
- አፍና እጅ እግርና ፍንጅ። አፈ ምላጭ በደረቅ ላይጭ
- እህል ላበደረ አፈር ወርቅ ላበደረ ጠጠር
- እህል ከበዩ ሰው ከገዳዩ። እህል ኪያጡ የናት ልጅ ይጡ
- እህል ካልተዋጠ ነገር ካልተደመጠ
- እልፍ ሲሉ እልፍ ይገኛል ደኻ ሞኝ ነው ሞቱን ይመኛል
- እህል ላራሽ ርስት ለወራሽ። እማኝ ሲገዙ ነገር አያበዙ
- እማን ላይ ቆመሽ እግዜርን ታሚያለሽ
- እኔን አይተህ ተቀጣ በጉድህ እንዳትወጣ (አለ ሌባ)
- እኔ የምሞተው ዛሬ ማታ ገብሱ የሚደርሰው ለፍስለታ
- እኔ ያለሁ እዚህ አንተ ያለኸው ሽሬ በምን አወቅህ? በወሬ። እኔም አለኝ ቍስል ያንተን የሚመስል
- እንኳን ዘንቦብሽ እንዲያውም ጤዛ ነሽ
- እንኳን ለቤቱ ይተርፋል ለጐረቤቱ
- እንደ አገሩ ይኖሩ እንደ ወንዙ ይሻገሩ
- እንደ እሸት ፈልፍዬ እንደ ዘንግ መልምዬ
- እንደ እንግዳ ጥልቅ እንደ ውሃ ፍልቅ
- እንደ መረብ ሸፍኖ እንደ እንቅላል ደፍኖ
- እንደ ፀሐይ የሞቀ እንደ ጨረቃ የደመቀ እንደ እባባ ያሸበረቀ። እንደ ሸመላ በሁለት ይበላ
- እንደ ሰው ትመጪ እንደ አውሬ ትሮጪ
- እንደ ገና ይመታል በገና። እንደ ንጉሡ አጐንብሱ
- እንደ ሣር ነጭቶ እንደ ውሃ ተጐንጭቶ
- እንደ ፈረስ ጆሮ እንደ ሰላጢን ጉሮሮ
- እንደ ካህን ናዝዞ እንደ ንጉሥ አዝዞ

- እንደ ወርቅ አንከብሎ እንደ ሸማ ጠቅሎ
- እንደ ተተከለ ትርሽማ እንደ ተሰጣ ሸማ
- እንደ ቆጫት ተነሥታ የሰውን ልቅሶ አጥፍታ
- እንደ እንግዳ ደራሽ እንደ ውኃ ፈሳሽ
- እንደባት ስቆ እንደ ንጉሥ አውቆ
- እንድትሄድ ቀይዳት እንዳትበላ ለጐማት
- እንዳየን ጤፍ አጋየን። እንደ እንቍላል ድፍን እንደ መረብ ሽፍን። እንዳልበላ በአፌ እንዳልበር በክንፌ
- እንዳያማህ ጥራው እንዳይበላ ግፋው
- እንዳልተወው ወለድኩ እናልሰው ነደድኩ (አለች ላም)
- እንደ ልብ የለም ነዳጅ እንደ ልብ የለም በራጅ
- እንደ የቤቱ ብዙ ነው ብልሃቱ
- እንደ ጴጥሮስ በጵላሎተ ርእስ እንደ ጳውሎስ በዘፈረ ልብስ
- እንዲያው ብትመለሺ የገንፎ ዕንጨት ላሺ
- እንደ ርግብ የዋህነት እንደ እባብ ብልህነት
- እስር በፍንጅ ጣል በድጀ። እሳት ታየው ምን ለየው
- እሳት ለፈጀው ምን ይበጀው። እሺ ይበልጣል ከሺ
- እሳት ቢቀርቡት ያሳክካል። መነኵሴ ቢቀርቡት ይልካል
- እሳትና ጥል የቀረበው ያቃጥል
- እስበሱ ሥጋን በኩበት ጠበሱ
- እስላም ካረገደ ቅማንት ከነገደ። እበላ ባይ ቃል አቀባይ
- እሺ ባይ አክባሪ እምቢ ባይ አሳፋሪ
- እሾኽ በእሾኽ ይነቀሳል ገንዘብ በገንዘብ ይመለሳል
- እሾኽ ላጣሪው ሥራ ለሠሪው። እባብን ያየ በልጥ በረየ
- እሾኽ አጣሪውን ነገር ፈጣሪውን (ይጐዳል)
- እሾኽ በእሾኽ ይወጣል ሰው በሰው ይመጣል
- እሾኽ ለረጋጪው ነገር ላምጪው
- እራትን ቢንቁ አንድ እጅን ይለቃለቁ
- እራት የሌለው ቄስ እንደ ልቡ አይቀድስ
- እራትና መብራት አማትና ምራት (አይጣጣሙም)
- እራት የሌላት ደግም ምሳ አማራት
- እራት ሲበሉ የመጣ እንግዳ እራቱ ፍሪዳ
- እራት ሲበሉ የመጣ ይቆጠራል ፍሪዳ እንዳመጣ
- እርጉዝ ላም ያለው ሰው ደረቅም አያንቀው
- እርሱ ራሱ ጊዜ መሆኑን ባያውቀው ጊዜ ጊዜ ይላል ሞኝ ሰው። እርጥቡን ሬሳ ደረቁን አስነሣ
- እርጎውን ለውሻ እርሱን ለውርሻ
- እርሟን ዛሬ ብታፈላ አንድ ቁና አተላ
- እርሟን ዛሬ ጠምቃ ፈጀችው ጠልቃ ጠልቃ
- እርሶው ቢያምር ዳቦውም ያምር (ነበር) (ያምራል)
- እርሻ ለባለ ከብት ርስት ለባለ ርስት
- እርሻ ላጥማጅ መሬት ለተወላጅ
- እርሷ ወልዳው አልመለሰም እርሷም ጋግራ አልበሰለም
- እርሱ ካለው ሳያልፍ በሽተኛው ባይለፈልፍ
- እበላ ያለ ዳኛ እገድል ያለ ደምኛ
- እባብ ግደል ከነበትሩ ገደል። እባብ ለባብ ይተያያሉ ከካብ
- እባብ በመርዙ መሬት በወንዙ
- እባብ ከእግርህ ብትር ከእጅህ (አለች ቀበሮ)
- እባብ የሚገድለው በምላሱ እኮ ነው
- እባብ!! እንደ መለስለሱ መታጠቂያ በሆን እሱ
- እባብ ስለ ሆዱ ይሄዳል በሆዱ
- እናንቱን ሳይ ሴት ማግባቴ ቤቴን ሳይ ትምባሆ መጠጣቴ
- እኔ የምበላው ሳጣ ልጄ ጥርስ አወጣ
- እናያለን ሲሉ ይታያሉ እናማለን ሲሉ ይታማሉ
- እንዳይወልዱ ይመነኵሱ እንዳይጸድቁ ይልከስከሱ
- እንደ ወይን መልምዬ እንደ እንጨት ተክዬ
- እንደ ፈታሒነቱ ሁላችን እንኰናለን እንደ መሐሪነቱ ሁላችን እንማራለን። እንደ ውሌ ደጃዝማች ባሌ
- እንደ ወንድማማች ተበዳደሩ እንደ ባዕዶች ተቆጣጠሩ
- እኖር ባይ ተጋዳይ እድን ባይ ተከላካይ
- እንግዳ ፊት ወርቅ ኋላ ብር ኋላ ጨርቅ
- እንጀራ ያለው ክቡድ እንጀራ የሌለው ዕብድ
- እንጀራ ከባዕድ መከራ ከዘመድ
- እንጀራ በሰፌድ አሞሌ ከገመድ
- እንግዳ ሆነህ ብትመጣ ሳይሰለቹህ ውጣ

- እንዴት ዘገዬ ይሉናል ግድ የለም ስንገባ ያምኑናል
- እየ ቤትህ ግባ እራስህ ተቀባ
- እየተፈጨ እየተቦካ እየሞተ እየተተካ
- እንጃ በሰማያት በምድርስ የለም ምክንያት
- እካስ ያለ ታግሥ እጸድቅ ያለ መንኵሶ
- እንከን ይመጣ ጥፍርም አላሳጣ
- እውነትና ሐቅ እያደር ይጠራል እንደወርቅ
- እኩሉን ተላጭታ እኩሉን ተቀብታ
- እውነት የተናገረ በመርከብ የተሻገረ
- እውነት ይመስላል ልብን ያቆስላል
- እወዳለሁ እያለ የሚጠላ እጾማለሁ እያለ የሚበላ
- እያየህ ተናገር እየዋሽህ ተሻገር
- እያደፈ በእንዶድ እየጐለፈ በሞረድ
- እያወቁ ቢስቱ ምንድር ነው መድኃኒቱ
- እደ ልቡና ለጸሎት እደ ሰብእና ለመሥዋዕት
- እዳ አለብኝ ብለህ አትቸገር ዕዳ የለብኝም ብለህ አትከበር አይታወቅም የአምላክ ነገር
- እጅ እያጠቡት ያድፋል ልጅ እየነገሩት ያጠፋል
- እጅና ጭራ አፍና እንጀራ ሥጋና ሞራ
- እጅግ ስለት ይቀዳል እፎት እጅግ ብልሃት ያደርሳል ከሞት
- እጅ ለነገር ያግዛል ልብ እንደ ንጉሥ ያዛል
- እጅህን ከባሕር አግባ ብታገኝ ዓሣን ታወጣለህ ባታገኝ
- ታጥበህ ትወጣለህ። እግሩ ለጠጠር ግምባሩ ለጦር
- እገሌ የዋለበት ሸንጎ አይጥ የገባበት እርጎ
- እኖራለሁ ብለህ እጅግ አትበርታ እሞታለሁ ብለህ ሥራ አትፍታ። እርጎውን ለውሻ እርሱን ለውርሻ
- እግዜር ያመነውን ማን ይችለዋል ንጉሥ የተከለውን ማን ይነቅለዋል። እጇ ከብትር አፌ ከነገር
- እግዚአብሔር ለፍጥረቱ ሰው ለሰውነቱ (ያስባል)
- እግዚአብሔር የተናገረውን አያስቀር የሚያደርገውን አይናገር። የእግዚአብሔርን ያህል ጌታ ገነትን ያህል ቦታ
- እግረ መንገዳቸውን ይሸታሉ በሬአቸው
- እጭን ያለ ኮርቻውን እለምን ያለ ስልቻውን

## ስድ ምሳሌ

- አህያ ላህያ ቢራገጥ ጥርስ አይሳበር
- አህያ በሞተች ባመቷ ኵርኵር። አህያ ከሞሞቷ መጐተቷ
- አህያ እንደምትታለብ ከላሞች ፊት ለፊት ትቅለብለብ
- አህያን ሥጋ ችነህ ጅብን ንዳ ብለህ እንጃ ይሆንን ብለህ?
- አለ ንጉሥ ሰላም አለ ደመና ዝናም} የለም
- አለ ንጉሥ ዘውድ አለ ምሳር ግንድ
- አለ መባ ቤተ ክርቲያን አትግባ
- አለ አቡን ክህነት አለ ንጉሥ ሹመት
- አለ ዳኛ አይከሱ አለ ጥርስ አይነክሱ
- አለ ዓቅማቸው እንዋጋ ቢሉ ጀግኖችን አስገደሉ
- አሉ ባለ ዕዳ አዎን ባለ ሜዳ
- አልበላ አልጠጣ ጐንደር ሂዶ ቀረ እንደወጣ
- አምኖ ለሚሚገት ረቺ የለው ብቻውን ለሚሮጥ ቀዳሚ የለው። አመልህ በጉያ ስንቅህ ባህያ
- አምነህ የሞገቱት አያስረታ ዝግ ብለው የታጠቁት አይፈታ። አመል ያስወጣል ከማኸል
- አባይና ስንቅ እያደር ይቀላል። አያድን አገሬ (ታላቅ ጋሻ) ጐድን ያሰብራል
- አይጥ በበላ ዳዋ ተመታ። እህል ወዳጁን ይጐዳል

## ዐ - ዓ - ዕ

- ዐሣ ዓሣን ይበላዋል ወንድም ወንድምን ይጠላዋል
- ዐሣ ጐርጓሪ ዘንዶ ያወጣል የሰው ፈላጊ የራሱን ያጣል
- ዐሣ በወንዙ ይታረዳል የጨዋ ልጅ በቤቱ ይፈረዳል
- ዐሣ ለወጋሪ ነገር ለጀማሪ። ዓመት አስቦ ለልደት
- ዐሣው እንዳይሞት ውኃው እንዳይደርቅ አድርጎ ነው ዕርቅ
- ዓሣን በልቶ ውሃ መጠጣት መልሶ ከነበረበት ማግባት
- ዓለም አታላይ እንደ በቅሎ ኮብላይ

- ዓመት የማይበላ ዓመት ያጣላ
- ዓይን ሁልጊዜ ከታለቅስ ፩ድ ቀን ብቻ ታልቅስ
- ዓይን የማያየው ልብ የማይስተው (እውነት አለ)
- ዓይን አይፈስ ዕርቅ አይፈርስ
- ዓይን አፋር ልጃ ገረድ ከወንድሟ ትውልድ
- ዓይቡን ሲያዩት አጓቱን ጠገቡት
- ዕልልታ ለደስታ እሪታ ለርዳታ። ዕርቅ ከወርቅ ከምርቅ
- ዕርቅ ቢፈርስ ካስታራቂ ድረስ
- ዕርቅ አፍራሽ ቤተ ክርስቲያን ተኳሽ
- ዕርቅ ደም ያደርቅ። ዕብድ ለዕብድ አብሮ ይነጉድ
- ዕብድና ብርድ ያስቃል በግድ
- ዕብድና ገር የታየውን ይናገር
- ዕንጨት ቢጠርቡት ይቀጥናል ሰው ቢበልጡት ይቀናል
- ዕውቀት ያኰራል ሥራ ያስከብራል
- ዕውር ከመሪው ሞኝ ከመካሪው (ይጣላል)
- ዕውር አያፍር ፈሪ አይደፍር
- ዕውር ምን ይሻል? ብርሃን ነጋዴ ምን ይሻል መዳን
- ዕውር ሲወበራ በሸማ ላይ አራ
- ዕውር ቢፈርዱ ዕውር ይወልዱ
- ዕውር ዕውርን ቢከተል ተያይዞ ገደል
- ዕዳ ከፋይ አሉ ባይ ሞት ተቀባይ አዎን ባይ
- ዕዳ ለቤት ምሥጢር ለጎረቤት
- ዕዳውን ከፍሎ የከተተ ጌታውን የተሰናበተ
- ዕድሜ ያልመከረው ሽማግሌ ከውኃ የገባ አሞሌ
- ዕድሜና ጨርቅ በደኅና አያልቅ
- ዕድል ተርታውን ዕጣ ፈንታውን
- ዕጣ ያስታርቃል ሙግት ያዳርቃል
- ዕፁብኬ ዕፁብ ውእቱ ለዕፁብሰ ትርጓሜ አልቦቱ

## ስድ ምሳሌ

- ዓሣ መብላት በብልሃት ነው። ዓባይን ያላየ ምንጭ አይቶ ይንደንቃል። ዓይን ካላዩበት ግንባር ነው
- ዓባይ ማደሪያውን ሳያውቅ ግንድ ተሸክሞ ይዞራል
- ዓይንህና አገርህ አይጠግቡም። ዓይን አይቶ ልብ ይፈርዳል
- ዓይን ከጥርኝ አፈር በቀር የሚያጠግባት የለም
- ዕርቅና ስንቅ ከቤትህ ሳለህ ይጠላል
- ዕሬትን ያልቀመሰ የማር ጣዕምን አያውቅም
- ዕብድ የያዘው መልከ አይበረክትም
- ዕብድ ቢጨምት እኩለ ቀን ድረስ ነው
- ዕብድና ዘመናይ የልቡን ይናገራል
- ዕንጨት ካልነሡት እሳት አይጠፋም
- ዕንቊራሪት በሬን እኽል ብላ ተሰንጥቃ ሞተች
- ዕውር ሲቀናጣ ዘንጉን ወርውሮ ፍለጋ ይገባል
- ዕድሜና ቆረንጮ ተበጣጥሶ ያልቃል
- ዕድሜና መስተዋት አይጠገቡም
- ዕጣ ያስታርቃል እንጂ አይፈርድም

## ከ - ካ - ክ - ኮ

- ከሁለት ዛፍ ያረፈች ዎፍ ሁለት ክንፏን ትነደፍ
- ከሆዱ የሚማከር ባባት አገር አይቀብር
- ከለ ከርሞ ዶሮ እንቊላል ለዘንድሮ
- ከልጂ ሆዴ ከባዕድ ዘመዴ
- ከለማኝ ለማኝ ቆረንጮዬን ቀማኝ
- ከልጅ ልጅ ቢለዩ ዓምትም አይቆዩ
- ከልጅ ጋር አትጫወት ይወጋሃል በእንጨት
- ከል የገባ አይነጣ ክልል የገባ አይወጣ
- ከመናፍቅ ትርጓሜ ከትምባሆ ልምላሜ
- ከመነኮሰች ባሰች ከተተኮሰች አነከሰች
- ከሙቶ ሃምሳ ዳዊት የልብ ቅንነት (ይጠቅማል)
- ከመጠምጠም መማር ይቅደም።
- ከመልካም ጠላ ክፉ ጠጅ። ከመልካም ወዳጅ ክፉ ልጅ
- ከመሞት ይሻላል መሰንበት። ከመታገል መታደል
- ከመደባደብ ይሻላል ማደብ። ከመጋደም መጋደል
- ከመወለድ መዛመድ ከመዛመድ መላመድ

- ከመሠረት አትጣላ ለጥንት የሚሆንህ ተግድግዳ አትፋቀር ተንዶ እንዳይጫንህ
- ከመነቃቀፍ ይሻላል መተቃቀፍ። ከባቄላ አይጠፋም ዲቃላ
- ከመናገሩ ይሻላል ጦም ማደሩ። ከቀዳዳ ይሻላል ጨምዳዳ
- ከመናገር ማዳመጥ ከመዋጥ ማላመጥ
- ከማሽላ ገንጠል ከአገዳ ጠልጠል
- ከማይራገጥ ወተቱን ከማይናገር ከብቱን
- ከምሳ የለዩን ደብተራ ውቅር ይሠራ
- ከምድር አደላድሎ ላህያ ከቡላድ አደላድሎ ከቋያ
- ከመውለድ ሰነፍ ይሻላል መጨንገፍ
- ከማይሰማህ ደብር አትማል ከአቅምህ በላይ አትዝለል
- ከማጠቢያ ሁሉ ሳሙና ከሥራ ሁሉ ትሕትና
- ከሞተ አቴቴ ምን አለኝ ካማቴ።
- ከሞተ ወዲያ ማልቀስ ደንጋይን መንከስ
- ከሞኝ ጋር ከመናገር ከብልህ ጋር መቸገር
- ከስጡህ አትስነፍ ካልሰጡህ አትለፍ
- ከሣልስትና ይሻላል ትናንትና
- ከሰው ክፉ ደብተራ ከአውሬ ክፉ ዳሞተራ
- ከሰው መርጦ ለሹመት ከእንጨት መርጦ ለታቦት
- ከሰጭ አሰጭ። ከሰቀላ ወደ ጥላ
- ከሰው ክፉ ደባል። ከጭንቅ ክፉ አላል።
- ከሰው ቀለብላባ ከመሬት ገብጋባ
- ከሰው ስሕተት ከብረት ዝገት (አይጠፋም) ከሰማ የነበረ ካለቀሰ የቀበረ
- ከሴት ነገር ከበቅሎ መደምበር
- ከሰው እንደረአይት ከዛፍ እንደ በቀልት
- ከሹም አይጣሉም ከምግብ አይታገሉም
- ከሺ በቅሎኛ የቄስ ደንካራ። ከሺ ዋቢ እራሱ ቀራቢ
- ከሽማኔ ቤት ቍቲት ከመነኵሴ ቤት ስስት (አይጠፋም)
- ከሺ ወርዋሪ አንድ መካሪ። ከሳሽ ከእሳት ጠባሽ
- ከሺ ምስከር ዋና በከናፍር። ከሩቅ ዘመድ ቅርብ ጐረቤት
- ከሮጠ ያንጋጠጠ በለጠ። ከራሳቸው ይጠፋል መዳነታቸው
- ከሽማግሌ ምክር ከገዢም ውረር
- ከቅዱሳን አፍ ምስጋና ከሰማይ ደመና
- ከቃጫ ወድያ ገመድ ከናት ወድያ ዘመድ
- ከቍንጫ ያወጣሉ መላላጫ
- ከበቀለ ያልተነቀለ ከተነቀለ ያልተተከለ
- ከበሮ በሰው እጅ ያምር ሲይዙት ያደናግር
- ከባለ ቀትር አትቀታተር ከነገረኛ አትነጋገር
- ከሳቱ ወድያ ይገኛል ምክር ያ ካመለጠ ይሰበስባል እግር
- ከባለጌ ጡጫ ከዳገት ሩጫ። ከዕውር ግልምጫ (ያድን)
- ከባዕድ ለስላሳ የራስ ከርካሳ። ከባርያ ጥቁር ከነገር ከጭሩ
- ከባለጌ መጋባት የጭዋ ልጅ መፋታት
- ከብት አይወድም ገደል ሰው አይወድም በደል
- ከተዘጋ ቤቱ ከተዳፈነ እሳቱ። ከብት ሰማይ ይከፍት
- ከብዙ ሐሰት አንድ እውነት ይበልጣል
- ከብዙ ጉልበት ጥቂት ብልሃት
- ከብዙ አህዮች ፩ድ ፈረስ ከብዙ ራስ አንድ ራስ
- ከብዙ ሺ ይበልጣል አንድ እዲ
- ከተማረ የተመራመረ ከወረወረ ያማከረ
- ከተመቱ ማንጠራጠር ጅብ ከሄድ አጥር ማጠር
- ከተጋደሉ ደመኛ ከተማማሉ ማለኛ
- ከታዘለ የማይወርድ ከሞቀ የማይበርድ
- ከታዳጊ ጌታ ሰግደድ ያለ ቦታ
- ከተናጋሪው ደጋሚው ከተርጓሚው ደርጋሚው
- ከነገር ክፉ ቍጭት ከአውሬ ክፉ ድርጭት
- ከነገር ማን ይቅድም? የደም
- ከነገሩ ጦም ይደሩ። ከአጉል ጥንቆላ የጨዋ ልጅ መላ
- ከነገረ ቀደሙ ይሻላል አፈ-ገራሙ
- ከናቷ ልጅዋ ትብስ ባቄላ አሮባት እጅዋን ትልስ
- ከኑግ የተገኘህ ሰሊጥ አብረህ ተወቀጥ

- ከንጉሥ በላይ አይፈርዱ ከባሕር በላይ እሳት አያነዱ
- ከአፍ የወጣ ቃል ከእጅ የወደቀ እንቊላል
- ከአንበሳ መንጋጋ ማን ያወጣል ሥጋ
- ከአዋቲ ጠያቂ ከጠያቂ አጥባቂ ከአጣቢ አድራቂ
- ከአጭር ምክር ከኃይለኛ ውረር
- ከእውነት የተሻለ ሐሰት ከመውጋት የተሻለ መሳት
- ከእግዚአብሔር ወድያ ፈጣሪ ከአባት ወድያ መካሪ
- ከአጋም የተጠጋ ቊልቋል ሲያለቅስ ይኖራል
- ከሀል መጥፎ አጃ ከነገር ክፉ አንጃ ከሣር መጥፎ ሙጃ
- ከዓይን የራቀ ከልብም ራቀ። ከወንድ ደረቅ ከወጥ መረቅ
- ከኵተት እስከ ሽበት ከልጅነት እስከ ዕውቀት
- ከክፉ ባለ ዕዳ ተልባም አይጐዳ
- ከክፉ ጐረቤት አይሠሩም ደህና ቤት
- ከወረወረ የመከረ ከመከረ የሰነዘረ
- ከወገብ በላይ ታቦት ከወገብ በታች ጣዖት
- ከወገኑ የተለየ አንበጣ ይባላል ፌንጣ
- ከሥሩ የተነቀለ ወይራ አሉ ብሎ የተረታ ባለጋራ
- ከወዳጅ የቀደመ ከጠጅ የከረመ
- ከወደቁ ወድያ መንፈራገጥ ወገብን መምለጥ
- ከዘር የሚሰጡት አለ ከዓውድማ የሚነፍጉት አለ
- ከዚህ የወደቀን ሬሳ ማን ያንሳ? ። ከዲዳ ላም ንዳ ከዝምታ ያለ ደስታ ከፍቅር ያለ ጨዋታ
- ከደብረ ታቦር ወድያ ክረምት ከደሮ ጩኸት ወድያ ሌት የለም። ከዳቦ ወጥ ጨምረህ ግመጥ
- ከስድት አፍላል ከቅመም ድምብላል
- ከደጃዝማች ማን ተሚጋች። ከጐሽ እበት ከዕንጨት ሽበት
- ከደህና ቢደርሱ ያደርጋል እንደሱ
- ከጀመሩ መጨረስ ካደረጉ ማልቀስ
- ከዳኛ ፊት አይናገሩም ዋዛ ከልጅ ፊት አይቆርሱም አሚዛ
- ከገንዘብ ዋና ርስት ከከብት ዋና እንስት
- ከጌታህ ጋር አትከራከር ከልጅ ጋር አትማከር
- ከሰው ቤት ዛር ከተሚጋች ቤት ነገር (አይጠፋም)
- ከጠጅ ወድያ አስካሪ ከባለ ቤት ወድያ መስካሪ
- ከጨርቅ ነጬ ከቦሃ ልጩ። ከጤፍ የደቀቀ ከመርፌ የረቀቀ
- ከጠላቱ የሚዋደድ እያደረ ይናደድ
- ከፈጣሪ የወረደ ለመሬትም አልከበደ
- ከፍትፍቱ ፊቱ ከፊቱ ፍትፍቱ
- ካሀያ ጋር ያረፈደ ያሀያን አመል ለመደ
- ካልታረደ አይታይ ስባቱ ካልተናገረ አይገኝ ብልሃቱ
- ካልጠገቡ አይዘሉ ካልዘለሉ አይሰበሩ
- ካላበበ አያፈራ ካልሰማ አያወራ
- ከልፈላ አይገነፍል ካልተጣደ አይበስል
- ካላየ አይቆጭ ካልሰማ አይበሳጭ
- ካልተማሩ አያውቁ ካልመጸወቱ አይጸድቁ
- ካለቀ መቆጠብ ከመሸ መንጠብጠብ
- ካልቀመሰ የደገመ ባሰ። ከለሥራዎ ምን አገባዎ
- ካለ ጓደኛ መጋፋት ከንቱ ልፋት
- ካሚጋች አስታራቂ ካጣቢ አድራቂ
- ካረጁ አምባር ይዋጁ። ካጃጁ አማራቸው ሊቆነጁ
- ካረገዘች ክታብ ያዘች። ካባቱ የተረፈ ተከሸፈ
- ካረጁ ወዲያ ጐፈሬ አዝመራ የሳተው ገበሬ።
- ካነጋገር ይፈረዳል ካያያዝ ይቀደዳል
- ካይን የፈጠነ ከውሃ የቀጠነ (የለም)
- ካይጥ ቤት ብቅል ከውሻ ቤት ጠፍር (አይጠፋም)
- ካገር ደጋ ከምኝታ አልጋ ታላቅ ጺጋ
- ካገር ንጉሥ የጐንደር ባላምባራስ
- ካገሩ የወጣ እስኪመለስ ቢጭኑት አህያ ቢለጉሙት ፈረስ
- ካገለገለ ያወደለደለ ካማከረ ያገለለ
- ካንገት በላይ ፍቅር እያደረ ያቃቅር
- ካድራጊ አስደራጊ ካስደራጊ አደራራጊ
- ካፍ የወጣ ከልብ የመጣ። ካፍ የወጣ አፋፍ
- ካፋፍ ላይ ነፋስ ካፍ ላይ እስትንፋስ (አያቋርጥም)
- ካጤ ቃል በላይ እውቅ አታላይ

- ክረምቱን ያፈጀ በጋ ዕዳውን የፈጀ ዜጋ
- ክረምት እንደ ግድግዳ በጋ እንደ ተራዳ
- ከባድ ላም ያለው ጠረሾ አያንቀው
- ክብረት ከሥምረት ነፃነት ከአንድነት ነው
- ከንፍ የሌለው አሞራ ቀንድ የሌለው አውራ
- ከዶ ከመሚገት አምኖ መረታት
- ክፉ አውሬ አይልመድ ከለመደም አይውለድ
- ክፉ እንደ አፉ ዛፍ እንደ ቅርንጫፉ። ክፉ ይነካል በክንፉ
- ክፉ አሽከር ከመንደር ሲደርስ ይቀራል ክፉ ጌታ ከዳገት ያሰግራል። ክፉ ነገር ለከርሥ ክፉ ሥጋ ለጥርስ
- ክፉ ሰው ከፍቶ ያከፋል አተላ ያስተፋል
- ክፉ ከማድረጋቸው ክፉን ማስለመዳቸው
- ኰለንታሁ በጽርሐ አርያም ኰለንታሁ በከርሠ ማርያም
- ኰራት እራት። ኰራትና ሃብት አይገኙም አንድነት
- ኮሶ ለአፍ ይመራል ጠላ (ወተት) ሲጠጡ ሸምጠጥ
- ኮሶ ያነዘዘው ሴት አማት የመረዘው

## ስድ ምሳሌ

- ከሆድ የገባው የናት ልጅ እንኳ አያገኘውም
- ከላይ ከደፈረሰ ከታች አይጠራም
- ካለመናገር ደጃዝማችነት (ይቀራል)
- ከሞት ውድያ ሐኪም አይጠየቅም
- ከመሃይምን ጐረምሳ የተማረ ሽማግሌ ይሻላል
- ከሩቅ ዘመድ ቅርብ ጐረቤት። ከቅርብ የወደቀ ከቍስል ዳነ
- ከባል በፊት ልጅ ይስጥሽ። ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው
- ከባለ ቤቱ እጅ የዋለ እንቍላል አይሰበርም
- ከቤተ ቀሊል ቤተ ቆማጣ ይሻላል
- ከቤት ዶሮ ካለ ከበረኻ ቆቅ ይያዛል
- ከብልህ ያለ ሞኝነት ተራራን ያህላል
- ከክፉ በቅሎ የተባረከ አህያ ይሻላል
- ከአንበሳ ቤት አጥንት አይጠፋም። ከወረሩ ሰውን አይፈሩ
- ከጠላት አሳሳም የጠላት መግመስ ይሻላል
- ከዝንጀሮ ቆንጆ ምን ይመራርጧል
- ከጠላት ምክር ፊተኛውን ትተህ ኋለኛውን ያዝ

## ወ - ዋ- ዉ - ዎ

- ወሀ ሲያለቅስ ዓሣ ያልቅ። ወሀ ለቀደመ ግዳይ ለፈለመ
- ውኃ እድፍን ያጠራል ትምህርት ልብን ያበራል
- ውኃ ሲጠራ ተሻገር ዳኛ ሲገኝ ተናገር
- ውኃ ከነቁ አበባ ከአጽቁ። ውኃ ኣያንቅ ነገር አያልቅ
- ውኃ ምን ያገሣ ድኻ ምን ያነሣል (ያወሳ)
- ውኃ የጥቅምት ነበርህ ታድያ ማን ይጠጣህ
- ውኃ ሲደርቅ ይሸታል ሰው ሲከዳ ይወሸክታል
- ወልደው ሳያበቁ በሰው ልጅ አይስቁ
- ወልዶ አይስም ዘርቶ አይቅም (የለም)
- ወልዶ የማይስምለት ተናግሮ የማይሳምለት
- ወልጄ አልላከሁ መንኰሼ አልጸደቅሁ
- ወረቱን የተቀማ ነጋዴ ዋግ የመታው ሥንዴ (አንድ ነው)
- ወራሽ የሌለው ባለ ጸጋ ፍራሽ የሌለው አጋል
- ወራት ይገፉል ባቄላ ጠላት ያጠፉል ዲቃል
- ወሬ ለጠያቂ ገበጣ ላዋቂ። ወሬኛ ሚስት ዘርዛራ ወንፊት
- ወሬ ታሽቶ አይቆረጠም ነገር ተዘግኖ አይቃም
- ወርቅ ያለው ቀበዝባዛ እህል ያለው ፈርዛዛ
- ወርቅና ሰም ፈትልና ቀሰም። ወስፌና ቢለግም ቅቤ አይወጋም
- ወርቅ ቢጠፋ የወርቅ ሚዛን አይጠፋ
- ወርቁ ከዳኛ ፊት ይቅረብ መጻፉ ከቄስ ፊት ይነበብ
- ወተት ለእምቦሳ ሥጋ ለአንበሳ
- ወተት ተበድሮ ለእንግዳ ፈረስ ተውሶ ለሜዳ
- ወተት ጠጥቶ ጠላ እግዜሄር ሲጣላ ጠላ ጠጥቶ ወተት የእግዜር ስጦት። ወንድ ለግርግርታ ጋሻ ለመከታ
- ወንድ ልጅ ፩ ቀን እንዳባቱ አንድ ቀን እንደናቱ
- ወንድ ልጅ ለፈረስ ሴት ልጅ ለበርኖስ

- ወንድም ወንድሙን አይበልጠው ምላጭ ምላጭን አይቆርጠው። ወንድ ባለ በዕለት ሴት ባለች ባመት
- ወንድምን አስቀይሞ ከመጾም ይሻላል ሥጋን መኮምከም
- ወንድ ተወልዶ ካልሆነ እንዳባቱ አመልማሎን ይስጡት ይፍልተል እንደናቱ። ወይኖ አረሰው ወይኖ ጐረሰው
- ወይ አገርሽ መራቁ ልቤን አለማወቁ!!
- ወይ ጋሻ ቅድም ቀረሻ። ወዳጅህ ሲታማ ለኔም ብለህ ስማ ወይ ባልዘፈንሽ ከዘፈንሽም ባላሳፈርሽ
- ወይፈን ለገራፊ ዓሣ ለገፋፊ (ለጠላፊ)
- ወይም አጥፍቶ ይርቋል ወይም አንድዶ ይሞቋል
- ወይፈን ካረሰው አባት በሬ የዳሰሰው (ያበላሸው)
- ወደሽ ከተደፋሽ ቢረግጡሽ አይከፋሽ
- ወዳጅ ይመጣል ከራያ ጠላት ይመጣል ከጉያ
- ወደው የዋጡት ቅልጥም ከብርንዶ ይጥም
- ወዳጄ ስለው በለጠኝ ስለቴ ለሰው ቆረጠኝ
- ወድቆ ይነሷል በእጅ ዘግይቶ ይከብሯል በልጅ
- ወዳጅና ጠላት አንድነት ይሰሙሃል አንድነት ይጠይቁሃል። ወጠጤ ለወጠጤ ቢፈርዱ እንዳይታረዱ
- ወጥ ያጣ ዱባ ልብስ ያጣ ዳባ። ወጮ ቢገለብጡት ወጮ
- ወጥ ያጣ ጐመን አገር ያጣ ስሜን። ወገነ ብዙ ኃዘነ ብዙ
- ወፍ ዛፍ አይቶ ወታደር ቤት አይቶ አይራመድም ከቶ
- ወዶ ገባ ልብሱ ዳባ። ዋስ አይሞግት ቈማጣ አይፈትፍት
- ዋስ ያለው ያመጣል ዋስ የሌለው ይስምጣል
- ዋሱን የማያመጣ ጢም አያወጣ
- ዋሽ ቢሉኝ እዋሻለሁ ነፋስን በወጥመድ ይዠለሁ
- ዋቢ ያለው ይወጣል ዋቢ የሌለው ይቀጣል
- ዋጪው ብላት ትጐርስበት ተዪው ብላት ትጨምርበት
- ዋና ከቤት ጠበቃ ከዱለት
- ውል አይፈርስ ዓይን አይፈስ
- ውል ያውላል ታንኳ ያሻግራል አቧራ ያስላል
- ውል አያናግር የተከዜ ምላት አያሻግር
- ውል ያዋለ ሰንበትን ያከበረ
- ውሸት መልካም ነገር ጣጣው ባልነበረ
- ውሻ ቢጠሩ ቀን ቢቀጥሩ ደረሰ በእግሩ
- ውሻ በቀደደው ጅብ ገብቶ ለመደው
- ውሻ ከሸሹለት ልጅ ከሳቁለት ያ አይመለስ ያ አይታገስ
- ውሻ በጅራቱ ባርያ ባንደበቱ። ውሻ ከሊጥ ጦጣ ከጥጥ
- ውሻን በእግር መምታት እንካ ብሎ ሥጋን መስጠት
- ውሾችም ምን ጊዜ ነው የሚናከሱ? ጅብ አባረው ሲመለሱ
- ውሃው እንዳይደርቅ ዓሣው እንዳያልቅ አድርጎ ዕርቅ
- ውረድ ከማማ ውጣ ከጫማ
- ውርርድ ቁም ነገር ይጋርድ
- ውርርድ ከጫፉ አሞራ ከክንፉ (ከዛፉ)
- ውትር ውትር ያነሣል ብትር
- ውጦ ውጦ ጨረሰው አይመረው አይተኰሰው
- ዎፍ ከድንጊያ ላይ አርፉ ፍሊጋዋ ጠፉ
- ዎፍ ጠባቂ ቢያደኳት ደንጊያ ለቃሚ ቀጠረች
- ወንድ የሞተበት ወንድ አይሻገርበት

## ስድ ምሳሌ

- ወግ አድራሽ ገበሬ ይሞታል በሰኔ።
- ወሬ ሲነግሩህ መላ ጨምር
- ውሸት ተናግረህ እውነት አግኝ
- ውሻ የሚበላውን እንጂ የተቃጣበትን ዱላ አያይም
- ውሻ በቀደደው ጅብ ይገባል
- ወንዝ ለወንዝ ርዋጭ የሰው በግ አራጅ
- ወጥን ማን ያውቃል? ቀላዋጭ
- ውዝፍ ለሹም ጥምብ ለጅብ
- ዎፍ እንደ አገርዋ ትጮኸለች

## ዘ - ዛ - ዝ - ዞ

- ዘመን የወለደው ንጉሥ የወደደው
- ዘመን እንደ ንጉሡ ዓውድማ እንደነፋሱ
- ዘመነ ግርምቢጥ ውሻ ወደ ሰርሶ አይሃ ወደ ሊጥ

- ዘመድ ቢረዳዳ ችግርም ባልኈዳ
- ዘመን የሚወልደውን ንጉሥ የሚፈርደውን (የሚያውቅ የለም) ። ዘመዱን ያማ ለራሱ ገማ
- ዘመድ በዘመዱ አይጨክንም ሆዱ።
- ዘመድና ዋንጫ እያለቅሰ ይምጣ
- ዘመድና መድኃኒት ለተቸገሩ ዕለት
- ዘመድ ከዘምዱ አህያ ካመዱ። ዘሩ የጣቴ ምድሩ ያባቴ
- ዘንዶ የዳገት በረዶ። ዘንግ ከተተከለ ልብ ተከፈለ
- ዘፈን በበገና ነገር በዋና
- ዘፈን አለ በገና ነገር አለ ዋና
- ዘንጋዳ ወታደር በመከር ጊዜ ይታይ ነበር
- ዛፍ ሲወድቅ ከግንዱ ሰው ሲቸገር ከዘመዱ
- ዛብ የሌለው ፈረሰኛ ምሳ የሌለው ኮሶኛ
- ዛፎች ቢጠፉ ቊጥቋቶች ተሰለፉ። (ዛፎች ነን አሉ)
- ዝምብ ሩቅ አይበር የሜዳ ልጅ (ሜዳ አደግ) ዱር አይደፍር። ዝሆን እንሆት ፍለጋው ወዴት
- ዝም ያለ ተንኰለኛ ይመስላል እንብላ ያለ ስስታም ይመስላል። ዝናም ለዘር ጠል ለመከር
- ዝናም ከደመና ነገር ከዋና
- ዝናም ካልጣለ ሁሉ ቤት እንግዳ ካልመጣ ሁሉ ሴት
- ዝንጀሮ ሰው ነበር ይላሉ ድሮ
- ዝናም ሳይመጣ ገና የውሃ መንገድ መጥረግ ደኅና
- ዝንጀሮ እንሳሳቅ ካልሺ ነዶዬን መልሺ
- ዝምበር ሳለ ሩጥ አባት ሳለ አጊጥ
- ዥብ እንደ አባቱ ይዘርጥጥ አህያ እንደ አባቱ ያፈርጥጥ
- ዥብን ሊወጉ ከአያህ ይጠጉ
- ዥብ እስኪነክስ ያነክስ። ዥራቷ ታደርሰኝ ከናቷ
- ዥብ ታኰተኰተ ሰው ከተከተተ

## ስድ ምሳሌ

- ዘመድን የሚወጉበት ጦር ጀንፎው አይለቀቅም
- ዘመን ያነሣው ቅል ደንጊያ ይሰብርቅል
- ዘመደ ብዙ ጠላው ቀጭን። ዘር ከልጓም ይጠቅሳል
- ዘመድና መድኃኒት በቸገረ ቀን ይፈለጋል
- ዘር ልትበደር ሄዳ እህል ሲሸት መጣች
- ዛፍ በሌለበት እምባጮ አድባር ይሆናል
- ዝሆን የዋለበትን ትመስላለች
- ዝሆን ቂጡን ተማምኖ ግንድ ይውጣል
- ዝምብ ቢሰበሰብ መግላሊት አይከፍትም
- ዝም ባለ አፍ ዝምብ አይገባበትም
- ዝምታ ወርቅ ነው መናገር ብር ነው
- ዝባድን ከውሻ እምነት ከባለጌ አትሻ
- ዝናም ሲያባራ ከዋሻ ምን ያሻ?
- ዝናብና ልጅ ሲጠሉት ያከብር
- ዝናር የሌለው ነፍጠኛ አለንጋን የሌለው ፈረሰኛ
- ዝንጅብል ማን? ቢሉህ ማነኝ ትል
- ዝንጀሮ የራሷን ጠባሳ አይታ በባልጀራዋ ሳቀች
- ዝንጀሮ ቢሰበሰብ ውሻን አይመክትም
- ዝንጀሮ የመቀመጫዬን ይቅደምልኝ አለች
- ዠርባ ለባለ ቤቱ ባዕድ ነው። ዥብ ከሄድ ውሻ ጮኸ
- ዥብ ከማያውቁት አገር ሄዶ አጐዛ አንጥፉልኝ አለ
- ዥብ ምን ይመስላ? እግሩ ያነክሳል አፉ ይነክሳል
- ዥብ ኪበላህ ዥብ በልተህ ተቀደስ

## የ - ያ - ይ

- የሁለት ሴቶች ባል ይሞታል ይበላል ሲባል
- የሆነ አይመለስ እሳት አይኈረስ
- የሆድ ብልሃት የጋን መብራት
- የሆድ ማበድ ያስቃል በግድ። የሐምሌ ብራ የሴት ውብራ
- የኃጥኡ ዳፋ ጻድቁን ያዳፋ። የለመደ መደመደ
- የለመደ ፈረሰኛ ዛብ አይጨብጥ እርካብ አይረግጥ
- የለመደች ጦጣ ሁልጊዜ ሽምጠጣ
- የለመደ ልማድ ያሰርቃል ከማድ (ያስረዳል)
- የለመኑትን የማይነሣ የነገሩትን የማይረሳ
- የለበሰ የማነንም ኈረሰ። የተላከ አፉን ለከከ
- የላሜ ልጅ ያውራዬ ውላጅ። የላም ወተቱን የጌታ ከብቱን

- የላጭን ልጅ ቅማል በላው ያናጢን ልጅ ጅብ በላው
- የላም መንጃ የሽማ መከንጃ የማር መቅጃ
- የሌለው ልብም። የሌባ ሞኝ ከጐተራ ሥር ይገኝ
- የሌባ ዓይነ ደረቅ ተመልሶ ልብን ያደርቅ
- የሌባ ምኝታው አመድ መታሠሪያው ገመድ
- የሌባ እጁን የፍየል ልጁን።
- የሌባን ጠበቃ አደባልቀህ (ደርበህ) ውቃ
- የሌላት እራት ደግሞ ምሳ አማራት
- የሎሌ አልቃሽ የሴት ቀዳሽ የቄስ አውደሽዳሽ
- የሌሊት ግስገሣ የቀን ዘለሳ
- የልጅ ሞት የእግር እሳት። የልጅ ቀላቢ ያህያ ጋላቢ
- የልጅ ነገር ሁለት ግሬ አንዱ ብስል አንዱ ጥሬ
- የልጅ ፍቅር የሴት ከንፈር እናትን አያስቀብር
- የልጅ ብልጥ የሰጡትን ይውጥ (እየቀደመ)
- የልብህን ቢያናግሩህ አለ ዕዳ ቢለቁህ (ቢሰዱህ)
- የሕልም ሩጫ የጨለማ ፍጥጫ
- የመስከረም ውስጡ በጋ ያረመኔ ልቡ ቀጋ
- የመነነ ከዱር የሞተ ከመቃብር (አይወጣም)
- የመነኵሴ ሎሌ የክረምት አሞሌ
- የመንታ እናት ተንጋላታ ትሞት
- የመታሰር ምልክት መያዝ የመሻር ምልክት መጋዝ
- የኰንን ልጅ በከተማ የድኻ ልጅ ባውድማ
- የመዝሙር መጀመሪያ ሃሌታ የዘፈርን መጀመሪያ እስክስታ
- የመኰንን ልጅ አዘን ቢነግሩት አደን
- የመተሩበት እጅ ይወዛል የተማከሩት ዳኛ ያግዛል
- የመከሩበት ሞተ የወረወሩበት ተሳተ
- የሙት አልቃአሹ የቁም ወራሹ። የሙት አልቃሽ የቁም ወራሽ። የሚሰርቀውን ያጣ ሌባ ሰላማዊ መስሎ ይገባ
- የሚዘን አባይ ለእሳት የዳኛ አባይ ለሰንሰለት
- የሚሉሽን በሰማሽ ገበያም ባልወጣሽ
- የሚፈታ ከተማ አዋጅ ቢነግሩበት አይሰማ
- የሚያልፍ ውሃ አደረገኝ ደኃ (አለች ልጅዋን ጐርፍ የወሰደባት)
- የሚያልቅ እህል ከማያልቅ ዘመድ ያጣላል
- የሚሮጡበት ሜዳ የሚወጡበት ቀዳዳ
- የሚወጡበት ገደል የሚንጠለጠሉበት ቅጠል
- የሚያልፍ ዝናም አይምታህ የሚሞት ሽማግሌ አይርገምህ
- የሚመክተው ጋሻ የሚጠጋበት ዋሻ (የለውም)
- የሚወዱትን አቅፎ የሚጠሉትን ነቅፎ
- የሚያጠግብ ቂጣ ከምጣዱ የሚወጣ ጥጃ ከገመዱ (ያስታውቃል)። የሚሠራ ምንም አያወራ
- የሚያመጣውን እንድታወቅ ያለፈውን እወቅ
- የሚያድግ ልጅ አትበድል የሚሞት ሽማግሌን አታቃልል
- የሚበላው ካጣ የሚበላለት ያጣ
- የማሽላ ዘር ከነ አገዳው ቸር
- የማትሄድ መበለት ዞራ ዞራ ትሰናበት
- የማን እርሻ ብለህ እረስ የማን ሚስት ብለህ ውረስ
- የማታ ማታ ጭምት ይረታ። የማያውቅ ምን ያውቅ
- የማተች አይፈርድ የማያተርፍ አይነግድ
- የማይጣሉ መላእክት የማይታረቁ አጋንንት
- የማይጽፍ ደብተራ ክንፍ የሌለው አሞራ
- የማያመሽ ባል ቅንድብ ይስማል
- የማይመስል ነገር ለሚስትህ አትንገር (ለሴት አትንገር)
- የማይድን ባሕታዊ ወተት አምጡ የማይድን ፋቅራ ጠላ ስጡ። የማይሠራ አይብላ የማይረዳ አይጥላ
- የሚያበድር ደመኛ የማይመስል ቀማኛ
- የማያበድር ገዳይ የማይመስል አባይ
- የማይፈወስ ድዉይ የማይመስል ጉጉይ
- የማታድግ ፍየል ፫ ትወልዳለች ልጆቿም ያልቃሉ እሷም ትሞታለች። የማያግዙ በከፈር ያግዛሉ በከንፈር
- የማይስማሙ ዝምቦች ጥምብ ይልሳሉ የሚስማሙ ንቦች ማር ይጐርሳሉ። የማይጠረጥር ቤቱን አያጥር
- የማታ ምግብ ለእንግዳ የጧት ምግብ ለአገዳ የጧት መጠጥ ለዕዳ። የሜዳ ንስንሱን የቤት ጉስጉሱን
- የሚያምኑበት ተዘግሮ ይተዉታል ተከፍቶ

- የማይቀና ባይወልድ የማያስብ ባይነግድ (ይሻላል)
- የምትታጠቀው የሌላት የምትከናነበው አማራት
- የምድሩን በአፍ የሰማዩን በመጻፍ
- የምትበላው እኽል ከማታየው መሬት ይበቅላል
- የምሕረት ጐደሎ የባርያ ወይዘሮ። የሰው አገሩ ምግባሩ
- የሞተን አትርሳ የወደቀን አንሣ
- የሞተ ቢሞት ያለን እንጫወት። የሰው ነገር አለ መናገር
- የሞተ ያልነበረ ይመስላል ያለ የማይሞት ይመስላል።
- የሞኝ ልቅሶ መልሶ መልሶ። የሰው በልቶ አያድሩም ተኝቶ
- የሰው እጅ የግዜሄር ደጅ። የሰው ብርድ አይቀርም በምድር
- የሰው ታናሽ ይገዛል በግማሽ። የሰው ክፉ ጠማማ ነው አፉ
- የሰው ልጅ በምን ይታፈራል በወንበር አይደለም በወንበር በከንፈር። የሰው እንግዳ ያገር ባዳ
- የሰው ፈላጊ የራሱን ያጣል ዓሣ ጐርጓሪ ዘንዶ ያወጣል
- የሰው አትበዪ ምግባር የለሽ የራስሽን አትበዪ ገንዘብ የለሽ
- የሰው ቤት ሲቃጠል ቋያ ይመስላል
- የሰው ሆዱ የዎፍ መንገዱ የሚያውቅ የለም
- የሰው ቀላል ለራሱ ይቀላል የልብስ ቀላል ባለ ቤቱን ያቀላል። የሥጋ ትል የዘመድ ጥል
- የሥጋ መጨረሻ አጥንት የነፍስ መጨረሻ ግብት
- የሥንዴ አራራ የቆንጆ መራራ
- የሰው ፊት አይቆረስ የሰው የገንዘብ አይወረስ
- የሰው ብልሃቱ ለፈጣሪ መንገር ነው መዳኒቱ
- የሰውን አባት የሚሰድብ አባቱን ያሰድብ
- የሰይጣን ገንዘብ የተበደረ ሳይበላው ተቀበረ
- የሰጡህን ተቀበል ያደረጉህን ቻል አትበል
- የሰው ልጅ ካለህ አገሩ ጐራዴ ካለ ሰፈሩ
- የሰነፍ አበባል ይብረድልኝ የሰነፍ ምስክር ይማልልኝ
- የሰማዩ ንጉሥ እስኪረዳ የመሬቱ ንጉሥ ይጐዳ
- የሰባን አርዶ የጸራን አውርዶ። የሰጠ ቢነሳ የለበት ወቀሳ
- የሰከረ ይተፋል የገደለ ይደነፋል
- የሰጋ ቤቱን ዘጋ የዘነጋ ተወጋ
- የሳተ ይምከርህ የዋለ ይንገርህ
- የሴት አገሯ ባልዋ ማደሪያዋ አመልዋ
- የሴት አመዳም የአሮጌ ሆዳም
- የሴት በራ የበቅሎ ደምባራ (በራ ገላጣ)
- የሴት አጭር ወይዘሮ የወንድ አጭር አውራ ዶሮ
- የሴት ጠጪ የግመል ፈንጪ። የሴት ዘንገኛ የናት ምቀኛ
- የሴት ረገርም የማቅ ሙዥምዥም አያስጐጅም
- የሴት ከርፋፋ ዕቃውን በዕቃ ደጋግፋ ፩ዱን ስታነሣ ሁሉም ይደፋ። የሴት ልባም ያህያ ቀንዳም
- የሴት መልኳ ምንድር ነው? እጅዋን ታጥባ ሰነፍ እንኩ ስትል ነው
- የሸማ ጥቅል የወርቅ እንክብል። የሹም ሰነፍ ባይለፈልፍ
- የሹም ገፋፋ አገር ያጠፋ ያህያ ጀላፍ መስክ ያጠፋ
- የሺ ፍልጥ ማሰሪያው ልጥ
- የሺ ሞት ሥርግ ነው ያ፩ ሞት ጐዳት ነው
- የሺ ገንዘብ ተቀበል የሺ ወንድም አትግደል
- የሺ አካላት መሰብሰቢያው አናት
- የሺ ቃል ንቁፍ የዋና ቃል ጽሑፍ
- የሺ ገንዘብ ብላ ከሺ ወንድም አትጣላ
- የሽሮ ፋከራ ከምጣዱ እስኪወጣ እንጀራ
- የረጋ ወተት ቅቤ ይወጣል የረጋ ሰው ከሁሉ ይበልጣል
- የርሷ ጊዜ ተንሰቀሰቀች የሰው ጊዜ ሳቀች
- የረዘመውን በጠፍር ያጠረውን በድግር
- የራሷን አበሳ በሰው ላይ አብሳ። የቀበረ ተቀበረ
- የራሱን የሚበላ ዕዳ የለው የመሰለውን የሚናገር በደል የለው። የሮጠ በለጠኝ የበላ አመለጠኝ
- የቀበጡ ዕለት አይገኝም ሞት። የቀን ጨዋታ አይገኝም ማታ። የሴት ምክር የእሾህ አጥር

- የቂል ብትር ሆድ ይቀትር። የቂስ ነጋዴ ይመስላል ወንበዴ። የቀና ቢታጣ ይመለመላል ጉበጣ
- የቂጣ እንዲሁ ይጠፋል የማርገዝ እንዲሁ ይገፋል
- የቂስ ሞገደኛ የሴት ብትረኛ አያድርስ ከኛ
- የቅማል ድስት ከራስ ወርዶ ካንገት
- የቆመ ሌባ የተቀመጠውን ይቀባ
- የቆቅ ለማዳ የካይላ እንግዳ ወደ ቤት ሲሉት ወደ ሜዳ
- የቆጡን አውርድ ብላ የብብቷን (ጥላ)
- የበላችው ያገሳታል በላይ በላዩ ያጐርሣታል
- የበቅሎ ከበድ የሐር ገመድ (አለኝ ይላል አማጭ ለልማዱ)
- የበደለ ይካስ የወለደ ይላስ። የበረታ ከራሱ የሰነፈ ከዋሱ
- የበሶ አቁማዳ ተፈትቶ የተሸካሚው አፍ ነጥቶ
- የበላ ዳኛ የወጋ መጋኛ። የበላው አብላላው
- የበላን ሆድ ያውቃል የወጋን ክንድ ያውቃል
- የበሬ ዳተኛ በማኽል ይተኛ። የበሬ ቀንዱ የወይራ ግንዱ
- የበሬ ዶሰኛ የሴት ምላሰኛ አያድርስ ወደኛ
- የበሬ ሆዳም ቢታረድም (ቢሞትም) አይጐዳም
- የበረደውን አሙቆ ይረጠበውን አድርቆ
- የበቅሎ ዕቃ እየራሱ አለቃ። የቡና ቀዝቃዝዛ የሹም ፈዛዛ
- የባለጌ ኃይለ ቃል እንደ ሽመል ይወቃል
- የባለጌ ኵራት እንዲያው ነው በከንቱ
- የባለጌ ኵራት እንዲያው ነው በከንቱ
- የባለጌ ልጅ ከመብል ይደፍር ከነገር ይጃጃል
- የባለጌ ልጅ እያደረ ይጋጃል የጨዋ ልጅ እያደረ ይበጃል
- የባልቴት ወብራ የከረምት ብራ (ወብራ መቀናጣት)
- የባለ ሥር ምላሱ አሥር። የባል ደግነቱ ባትናገር ሚስቱ
- የባርያ ንጉሥ ደህና ሥር ቢያሳዩት ዓይኑ ወደ ፈርስ
- የባዕድ ሞኝ ከዘመድህ እኩል አርገኝ የዘመድ ሞኝ ከልጅ እኩል አርገኝ። የቤት ቀጋ የውጭ አልጋ
- የብረት ቆሎ የደንጊያ ንፍሮ
- የተማረ ከብሩን መርመረ። የተከፋ ተደፋ
- የመሰከረ ይፈረዳል የሰባ ይታረዳል
- የተፈተለ ከሁለት የተታታ ከሦስት
- የተኛውን አንበሳ አስነሳችው ላም ላሳ ልሳ
- የተናካሽ ውሻ የጅብ መቋደሻ። የተቀማጭ ምላሱ ምላጭ
- የተጠማ ከፈሳሽ የተጠቃ ከነጋሽ
- የተላጠ እንጨት ዳግም አይላጥም ሰው አለ አንድ ጊዜ አይበለጥም። የተጣፈ ይወርሳል ያልተጻፈ ይረሳል
- የተፈጠመ ያርፋል የተኛ ያኰርፋል
- የተጠረጠሩበት ደንጊያ ይጥሉበት
- የተናገሩት ከሚጠፋ የወለዱት ይጥፋ
- የተረገዘ በሆድ የታዘለ በለምድ
- የተሳለ ብረት አንገትን ከደረት ሥጋን ከጅማት (ይለያል)
- የተራበ ከባቄላ የተበደለ ከሰቀላ
- የተታታ ገመዴ የተቆፈረ ጉድጓዴ
- የተቆለፈ ወርቅ ያልተቆለፈ ጨርቅ
- የተመረጠ እንጨት ለታቦት የተመረጠ ሰው ለሹመት
- የተመኘነው አገኘውነው። የተዘጋ ተጠበቀ ያልተዘጋ ተሰረቀ
- የተፈጠመ አይናገር አንካሳ አይሻር
- የተሾመ ወደ ግምጃ የተሻረ ወደ ሙጃ
- የተገዘተች ነፍስ የተለጐመች ፈረስ
- የታናሽ ልጅ አሳናሽ የዘንጋዳ ወጥ እህል አለባሽ
- የትሕትና ብትር ያስመታ የትሕትና ሙግት ያስረታል
- የትም ፍጭው ዱቄቱን አምጭው
- የነብር ልጅ አይታቀፍ የጨዋ ልጅ አይነቀፍ
- የነብር ዓይን ወደ ፍየል የፍየል ዓይን ወደ ቅጠል
- የንብር ጅራቱ አይዙም ከያዙም አይለቁም
- የነገሩ ሁነኛ የጦር አርበኛ። የነገር ወጡ መደመጡ
- የነገር ጣዕሙ ዝግታ ያዋቂ ጣዕሙ ዝምታ

- የነገሩትን የማይረሳ የለመኑትን የማይነሣ እግዜርን አትርሣ። የነፍሰ ገዳይ ምልክቱ ደም በጣቱ
- የናት ልመና ፊት አያስመልስ አንገት አያስቀልስ ስሂን በውድ አለዚያ በግድ
- የናት ሆድ ዥንጉርጉር እንደ ነብር ጠጉር
- የናት ልጅ የሌለው አይስላ ጆሮ የሌለው ምንቸት አይፍላ
- የኔ ነው የማይል የሞት የራሱን የማይተው የሞተ
- የኔ ነህ በለኝ ደስ እንዲለኝ የንጉሥ ቃል ፩ድ ይበቃል
- የንጉሥ ግምቡን የብልህ ልቡን
- የንጉሥ እድር እናት አያስቀብር። የንጉሥ ቃል አጠረ ብለው አያስረዝሙት ረዘመ ብለው አያሳጥሩ
- የንጉሥ ሞት የፀሐይ ፅርበት። የንጉግ ገንዘብ በለጋስ እጅ ይናኛል የጠላት ገንዘብ በወዳጅ እጅ ይገኛል
- የንጉሥ አሽከር ስሙ ወርቅ ልብሱ ጨርቅ
- የንጉሥ እንግዳ አያድርም ምድረ በዳ
- የእንጀራ እናት ምን አጠናሽ እንደ ዥማት?
- የአሽከኮ ዳባ ለመስበኪያ ቀጭን ሸማ ለማረግረጊያ
- የአርበኛ ልጅ ይወጋል የኣሮጌ ልጅ ያወጋል
- የአውሬ ሥጋ ለወሬ። የአልኮል ፍቅር እስከ መቃብር
- አቡነ ዘበሰማያት ጦር ሲወጋ እንጂ አይታይም ሲወረወር። የዞረ ያመጣ ፌራና ፈንባጣ
- የአገው ልብ ፱ኝ ፰ቱን አኑሮ ፩ዱን ሰጠኝ
- የአይጥ ጣረሞትዋ የድመት ጨዋታዋ
- የአህያ ፍሪዳ የእባብ ለማዳ (የለም)
- የአፍ ብልሃት ጌትነ የእጅ ብልሃት ባርነት
- የአፍ ዘመድ ከገበያም አይገድ። የአተር ክምር የጢሰኛ ክብር። የአይጥ እርጉዟ የድመት ወዟ
- የአንበሳ ገራም ይውላል ከላም
- የእንጦጦ መምር አይናገር ቢናገር ባመት ያውም እሬት
- የከፉ ሰው ፈስ ዓይን ያፈስ። ያአህያ ባል ከጅብ አያስጥል
- የዕብድ ገላጋይ ጐራዴ አቀባይ
- የኣረፋውን ሲሏት የጀጀባውን
- የእህል ጌታ ፈርዛዛ የወርቅ ጌታ ቀበዝባዛ
- የእንጨት ክፉ አባሎ የዳኛ ክፉ መድሎ
- የእህል ጣዕም በጕሮሮ የነገር ጣዕም በጆሮ
- የእህት ጅል ባይወልዱትም ልጅ። የእረኛ ፈሱ መርዘኛ
- የዕውር አስተናባሪ የድውይ አጋፋሪ
- የዕብድ አሞራ ሲላ ደንገጡራ
- የዕቡይ ልጅ ወዳቂ የዘማ ልጅ ሳቂ
- የዕብድ ቅል ማንጠልጠያው ክር (ፈትል)
- የከተማ ወንበዴ የበረኻ ወንበዴ
- የከረረ ይበጠሳል የተበደለ ይካሳል (የበደለ ይወቀሳል)
- የካህን አፋር ያህያ ዕውር የሴት ደፋር (አይረቡም)
- የወለደ ይልሳል (ይላስ) የበደለ ይክሳል (ይካስ)
- የወለደውን ቢስሙለት ያቀረበውን ቢበሉለት (ደስ ይለዋል። የወንድ አጭር ዝንጀሮ የሴት አጭር ወይዘሮ የወታደር ፈዛዛ የናት ነዝናዛ የሴት ቀበዝባዛ) አይረቡም
- የወንዝ ዘለላ ጋን ይመላ የሥንዴ ዛላ እፍኝ ይመላ
- የወደድኸው ቂጣ ሰተት ብሎ ወጣ
- የወደዱትን ቢያጡ የጠሉትን ይቀላውጡ
- የወጋ ቢረሳ የተወጋ አይረሳ (ሳም)
- የወደቀን አንሣ የሞተን አትርሳ
- የወላጅ ሆድ ቀጥቀጥ የልጅ ሆድ ቀጥ
- የወንፌድ ስልቻ ጤፍ ይቋጠራል ባቄላን ያፈሳል
- የወጣ ሰው አንዱን ጥሎ አንዱን አንጠልጥሎ
- የወጋ መጋኛ መቅቡጥ የለመደ ዳኛ (መቅቡጥ ጉቦ)
- የዋርካ ልጅ ሳንቃ ያለቃ ልጅ አለቃ
- የዋስ ተሟጋች የድውይ ፈትፋች። የዋጋ ብልጥ ልብ ይግጥ የልጅ ብልጥ እየቀደም ይውጥ
- የዋስ ወንድም አይታገት የአባይ ወንድም አይጐተት
- የውሻ ትሕትና የካህን ዕብድና መቼ ይጋጠምና
- የዎፍ ወንዱ የሰው ሆዱን የሚያውቅ የለም
- የዘመድ ጥል የጐመን (የሥጋ) ትል
- የዘመድ ቁስ እየፈታ ያለቅስ (የዘመኑ ወሬ ይቀዳል ባቦሬ)
- የዘመኑ ሰው ምላሱ መንታ ፩ዱ ለፍቅር ፩ዱ ለሐሜታ
- የዘነጋ ተወጋ ያወቀ ተጠነቀቀ

- የዘፋኝ እጅ ከመሰንቆ የሰካራም እጅ ከብርጭቆ
- የዝሆን ክሳት የባለ ጸጋ ድህነት (አይታወቅም)
- የዝምብ ተባቱ የ- ጭምቱ ሳይታወቁ ሞቱ
- የዝንጀሮ ንጉሥ እሱው ይከምር እሱው ያፈርስ
- የደገመ ተረገመ። የደንቆሮ ልቅሶ መልሶ መልሶ
- የደፋት ሬሳ የጠበሱት ዓሣ።
- የደንጊያ መቀመጥና የባዕድ ፍቅር እያደር ይቆረቊር
- የዳጉሳ እንጌራ በትኩስ የባዕድ ፍቅር በአዲሱ
- የዲንጋይ ልብ የኩበት ግምብ (የለም)
- የዳኛ ጅል ያማታል አባይ ምስክር ያስረታል
- የድመት ማንቀላፋት አይጦችን ለማጥፋት
- የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሳል ያይጥ ችኩል የድመትን አፍ ይልሳል። የገንዘብ አሮጌ ያባት ባለጌ (የለውም)
- የጅብ ገበሬ የዝንጀሮ ጐግኋይ ሁሉም በየበኩሉ እበላ እበላ ባይ። የገዛ ጌታ እግርን ይዞ የመታ
- የጋራ እርሻ የፍቅር መጨረሻ
- የጋላ ወዳጅ የማጭድ ቀዳጅ። የጋራ ወንጋራ
- የጌታውን አመካከት ሎሌው ይመልከት
- የግፍ ግፍ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ
- የጐበዝ ልቡ ከደረቱ የፈሪ ልቡ ከፊቱ
- የጐበዝ ድዳ ባመቱ ምድረ በዳ
- የጐበዝ ሹም የጎንደር ጉም አገር ይደረግም
- የጐረቤት ሌባ ቢያውቁት ይስቃል ባያውቁት ያሰጋል
- የጠረጠረ ቤቱን አጠረ። የጠሩትን እንግዳ እራቱ ፍሪዳ
- የጠገበ ዕውር ዘንጉን ይወረውር
- የጠላ ከፋት አለመገኘቱ የልጅ ከፋቱ አለመስማቱ
- የጠጅ ቤት አዛዥ አተላ አጋዥ
- የጧት መጠጥ ለዕዳ የጧት ምግብ ለአገዳ የማታ ምግብ ለእንግዳ። የጣመው ቀለጠመው። የጦም ቆሎ የባል ደሮ
- የጦጣ ብልጣ ብልጥ የዝንጀሮ ቅልጣ - ቅልጥ
- የጦጣ ዘር አቀባይ የዝንጀሮ ጐልኋይ
- የጦጣ ልጅ በዛፍ የመናፍቅ ልጅ በመጻፍ (አይቻሉም)
- የጥር በልግ የብር ዘንግ። የጥቅምት እርሻ ያባት ውርሻ
- የጨው ገደል ሲናድ ብልህ ያለቅሳል ሞኝ ይልሳል
- የጨረቃ ሃያጅ የምስክር ፈራጅ
- የጨነቀው ይዋጋል ያልደረሰበት ያወጋል
- የጨለማ አፍጣጭ የዕውር ገልማጭ
- የፈረሰኛ ጥለት ለባሽ የሴት ትምባሆ ቀማሽ
- የፈሩት ይደርሳል የጠሉት ይወርሳል
- የፈቷት ሚስት ያጠቡት ወጭት የወጡበት ቤት (፩ ናቸው) ። የፈሰሰ አይታፈስ የሞት አይመለስ
- የፊት ከብት የእጅ ወረት። ያለ ባለ ቤቱ አይነድም እሳቱ
- የፋቂ ልጅ ሰነፍ አንዱን ሳይፍቅ አንዱን ይዘፍቅ
- የፍየል ጅራቱ ከብርድ አያድን አፍረትን አይከድን
- ያህያ ሥጋ ውርደተኛ አልጋ ላይ ቢያኖሩት እመሬት ይተኛ
- ያህያ ልጅ ጥሎ ይመረጣል የፈረስ ልጅ ጥሎ ይደነግጣል
- ያህያ ጅላፋ መስከ ያጠፋ የሹም ዘፋፋ አገር ያጠፋ
- ያለ ሥራ ሙብል ያለ ዳኛ ውል (አይቻልም)
- ያለ ዘመድ ነግሦ ያለ አቡን ቀስሶ
- ያለው ይምዘዝ ያሌለው ይፍዘዝ
- ያለ ስፍራው የተሰበረ ሲጠግኑት አስቸገረ
- ያለ ሥራ አይበላ እንጀራ። አለ ባላ ቆጥ አይሠራ
- ያለ መከራ አይገኝም እንጀራ
- ያለ ፊቱ አይቆርስ ያለ ቤቱ አይወርስ
- ያለ አቻ ጋብቻ ቆይ ብቻ ቆይ ብቻ
- ያላባቱ ቢዛቊን አባክኖ ያባክን
- ያልተረታ አይረታ ያልጠገበ አይማታ
- ያልወለዱ ሁሉ ጊደሮች ይባላሉ
- ያልተገራ ፈረስ ይጥላል በደንደስ
- ያልበላ ዳኛ አያሚግት ያልጠጣ እንግዳ አያጫውት
- ያል በሉት ዕዳ ያልጠሩት እንግዳ
- ያልተሾመ አያዝ ያልቀሰሰ አይናዘዝ
- ያልሰጡት ተቀባይ ያልጠሩት እቤት ባይ

- ያልተቀጣ ልጅ ያልታጠበ እጅ። ያልወለደ አጋድሞ አረደ
- ያልዘራሁት በቀብኝ ዱባ ያልኩት ቅል ሆነብኝ
- ያልወለድኩት ልጅ አባ አባ ቢለኝ አፌን አለኝ ዳባ ዳባ አለኝ
- ያልገደለ ዘማች ያልወለደ አማች
- ያልጠረጠረ ተመነጠረ። የዘገነ አዘነ ያልዘገነም አዘነ
- ያልተማረ አይጸድቅ ያልተወቀረ አያደቅ
- ያመንኩት ፈረስ ጣለኝ ከደንደስ
- ያሳደግሁት ውሻ ነከሰኝ ያነደድኩት እሳት ጠበሰኝ
- ያማከሩት ዳኛ ያግዛል የመተሩበት እጅ ይወዛል
- ያምራል ብሎ ይሸልሟል ያውቃል ብሎ ይሾሟል
- ያምናውን ዘንድሮ የአዋጁን በጆሮ
- ያምራል ብለው ከተናገሩት ይከፋል ብለው ያስቀሩት
- ያሰረ ይፈታል የሰጠ ይረታል
- ያረጀን ሹም ገባር ይከሰዋል ያረጀን ጅብ አህያ ይልሰዋል
- ያበደች ጋለሞት እናቷን ትመታ
- ያበደ ኑሮው የፈረደ ለጉረሮው
- ያባት ሞቱን አይወዱ ረጀቱን አይሰዱት
- ያባ ሆይ መቋሚያ ላይ በላ ታቹ ዱላ
- ያባት ያኖራል የባዕድ ያናግራል
- ያባቱን ያገኘ ሕይወቱ ያባቱን ያጣ ሞቱ
- ያንበሳ ማላጅ ጋማ ይዞ ጅብን መውጋት አህያን ተጉዝጉዞ። ያብዬን እስከ ወደ እምዬ ለከከ
- ያንተን የሚመስል የኔም አለኝ ቍስል
- ያንጐርጓሪ ጉልበት የተራጋጭ ወተት
- ያንድ እርሻ እሸት ያንድ ላም ወተት
- ያወቀ ተጠነቀቀ ያላወቀ ተነጠቀ
- ያንድ ቀን ስሕተት ለዘላልም ዕውቀት (ነው)
- ያውሬ ሥጋ ለወሬ። ያዩትን ሲሠሩ ዓይናቸው ታውሩ
- ያየ በሄደ የሰማ ይመጣል የወጣ ቢገባ የገባ ይወጣል
- ያይጦች ዝላይ ለነአቶ ውሮ ሲሳይ
- ያደረገችውን ታስታውቅ ከደረቷ ትታጠቅ
- ያደረፈውን በእንዶድ የጐለደፈውን በሞረድ
- ያዳኘ ውሻ ጠጉር ባፉ ብትር ትርፉ
- ያገርህ ልጅ ብታገባህ ሚስትህ ብታፈታት እትህ
- ያገር እድር ለንጉሥ ያስቸግር። ያገር እድር ጦም ያሳድር። ያገር ልጅ የማር እጅ
- ያገኘ ከራሱ ያጣ ከዋሱ። ያጥንት ፍላጭ የሥጋ ቍራጭ
- ያገር ልጅ በምን ይማታል? በኩበት ያ እንዳይሄድ ያ እንዳይሞት። ያፍ አማኝ አደረገኝ ለማኝ
- ይሆናል ብዬ ጎሽ ጠመድኩ የማይሆን ቢሆን ፈትቼ ሰደድኩ። ይህ ሁሉ ጠበሳ ባንቺ የተነሣ
- ይሉኝታ የራስ ዓሊን ቤት የፈታ
- ይቅር ስለ እግዜሄር ወድቆ አይሰበር ሞቶ አይቀበር
- ይሰጡኛል ብሎ ከሰተ ቆጥቦ የበላ በለጠ
- ይወዷል ከሆድ ይታጠቧል ከክንድ
- ይብራና ይብራ ተጣሉ በሰው ሽምብራ
- ይደንቃል ይገርማል ያህያ ከጅብ ጋር ይከርማል?
- ይጥሉህ አትጥላቸው ይበድሉህ አትበድላቸው
- ይጠላኝ ይመስላ ይመታኛል ይወደኝ ይመስል ይስመኛል
- ይወደዋል ካሱ ይመከሯል ይወልደዋል ካሉ ይመስሏል

## ስድ ምሳሌ

- የሆድ ነገር ሆድ ይቆርጣል። የሆድ ምቀኛው አፍ ነው
- የልመና እንጀራ ምን ጊዜም ከልመና አያወጣም
- የልጅ ነገር ጥሬ በገል። የልቡን አድራጊ አይናደድም
- የላከ እንደ አፉ ያከከ እንደ እጁ አይሆንለትም
- የመኰንን ልጅ ኃዘን ቢነግሩት አደን
- የመከራ ልጅ ሁለ ጊዜ መከራ መስሎ ይታያል
- የሙት ቀናተኛ ሚስቴን አደራ ይላል
- የሚያልፍ ቀን የሚያልፈውን ስም ያወርሳል
- የሚያድግ ዛፍ በቍጥቋጦው ያስታውቃል
- የሚሸሹበት አምባ ሲሸሽ ተገኘ
- የሚያስፈራውን ለሚነግርህ የሚያስቀዝነውን ንገረው

- የሚከርምም የማይከርምም አንድነት ዝናም ይለምናል
- የሚዳቋ ብዛት ለነ አቶ ውሻ ሥርግ ነው
- የምትነቃቃ ግንድና የምትሰቅ ሴት ሴት ልብ ሩቅ ነው
- የማይተማመኑ ባልንጀሮች እየወንዙ ይማማላሉ
- የማይቻል ጠላት ስለ ወዳጅ ይቆጠሯል
- የማያፍር እንግዳ ባለቤቱን ይጋብዛል
- የማያስተኛ ነገረውህ ተኝተው ያድራሉ
- የማይድን በሽተኛ የበጋ እሸት ያድራሉ
- የማይመለስ ማር ሹመኛ ይበደረዋል
- የማይበላ የለም የማይጠግብ ባሰ
- የማትሰማው ስድብ ከቀረርቶ ይቆጠራል
- የማታርፍ ጣት አር ጠንቍላ ወጣች
- የማይመቱት ልጅ ሲቈጡት ያለቅሳል
- የምትኰነን ነፍስ ጐረቤት ያውቃታል
- የምጣዱ እያለ የእንቅቡ ተንጣጣ
- የምትጠላውን የምትወደውን ሰጥተህ ሸኘው
- የምትጠላው ሰው ፈሱ እሆዱ ውስጥ ሳለ ይሸታል
- የምትጠባ ጥጃ አትጮኽም። የማይደርሱበትን አያኩም
- የሞተ ልጅ አንገቱ ረዢም። የሞኝን ጥርስ ብርድ ፈጀው
- የሰው ቤት ሲቃጠል ቋያ ይመስላል
- የሰው እረኛ ጥቁር ነው የሸንጎ ዓይን ጉልበትን ይሰብራል
- የሰይጣን አመጣጥ የማያውቅ አይመንኰስ
- የሰው ፊት የማያፍር በቅሎ አይቀመጥ
- የሰው ልጅ ከማሳደግ የውሻ ልጅ ማሳደግ
- የሰው አገር ዝናምና የንጀራ አባት አይምታህ
- የሴት ቀበጥ የበቅሎ መድን ለመሆን ገበያ ወጣች
- የቀባጣሪ አፉ ጠማማ ነው። የተናቀ ሰፈር ባህያ ይወረራል
- የቀበሮ ባሕታዊ ከበጎች ማኸል ገብቶ ይጸልያል
- የቆጡን አወርድ ብላ የብብቷን ጣለች
- የብልጥ ዓይን ቶሎ ያለቅሳል። የታመመውን ሙት ጠየቀው
- የተላጠ እንጨት ሁለተኛ አይላጥም
- የተነቃነቀ ጥርስ ሳይወልቅ አይቀርም
- የባለጌ ሃይማኖት ከጅማት ይከራል
- የተጠገነ አፍስሶ ለቀመ። የቸገረ ዱጨት ከነፋስ ይጠጋል
- የታመነ ዳነ ደም የተፈናጠቀበት ሞት
- የታለህ ያላሉት እዚህ አለሁ ይላል
- የተቀመጡ ማዕርግና ልጃገረድ የሚሆኑት አያጡም
- የታነቀ የልቡ ይናገራል ግን የሚያምነው የለም
- የናት ልጅ ሲጣላ እውነት ይመስላል
- የናት ሞትና የደንጊያ መቀመጥ እያደር የቈረቍራል
- የአሥር እናት ጅብ በላት። የክፉ ሰው ተዝካር ያቅራል
- የአዳኝ ውሻ መነጽሩ የአፍንጫው ነው
- የአጭር ኵራት የሴት ስካር አይታይም
- የአንበሳ ልጅ ሲሞት አንበሳ ሲሞት እቤትህ ዋል
- የእንሽኰሽኵታ ግቢ ለፍች ያስቸግራል
- የእከክ መድኃኒቱ አለመቅረብ አለመቀራረብ ነው
- የእውነት ዘንግ ትመነምናለች እንጂ አትሰበርም
- የዕንጨት ምንቸት ራሱ አይድን ሌላውን አይድን
- የዕሬትን ምሬት ያልቀመሰ የማርን ጣዕም አያውቅም
- የክረምት ጥማትና የመከር ጊዜ ራብ አለባለቤቱ የሚያውቀው የለም። የደላው ውሻ ማር ይቀላውጣል
- የደንቆሮ ዘፈኑ ያው አንድ ብቻ ነው
- የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሳል
- የገማ ሰው ከሰው አይሸሽም ሰው ከሱ ይሸሻል እንጂ
- የገበያ ግርግር ለቀጣፊ ይመቻል
- የጒበዝ ልብ ከደረቱ ነው። የጉልበት ግማሹ አፍ ነው
- የጓጉንቸር ልጅ መሄድ ሳታውቅ መዝለል
- የጠገበ ሰው የተራብ ያለ አይመስለውም
- የጠገበ እንግዳ ሳይተች አይወጣም
- የጠገበች ዶሮ ከነጭልፊት ማኅበር ትገባ
- የጢስና የልጅ መውጫ አይታወቅም
- የጨዋ ልጅና ቅል ተሰባሪ ነው

- የጫማ ጠጠርና የእንጀራ ልጅ እያደረ መቆርቆሩ አይቀርም። የፉክክር ቤት ሳይዘጋ ያድራል
- የፊት ምስጋና ለኋላ ሐሜት ያስቸግራል
- ያልተገላበጠ ያርራል። ያለ ይበዛል አለ ወፍጮ
- ያለ የሚኖር ይመስላል የሞተ ያልነበረ ይመስላል
- ያላዩት አገር አይናፍቅም ያላዩት ነገር ክፉ አይደለም መልካምም አይደለም። ያኖሩት እንቅርት ያገለግላል
- ያልታደለ ከንፈር ሳይሳም ያረጃል
- ያልተነካ ግልግል ያውቃል (ያልደረሰበት)
- ያልታየ እንጂ ያልተሰማ ያልተደረገ እንጂ ያልተባለ ነገር የለም። ያልወለደ አንጀት ጨካኝ ነው
- ያልሰማ ጆሮ ከጐረቤት ያጣላል
- ያልዘራውን ያሚበላ ዝንጀሮ ነው
- ያልሞተና ያልተኛ ብዙ ይሰማል
- ያብሮ አደግ ልብ በቁና ይሰፈራል
- ያላሰብከው አግኝ መርገምም ምርቃም አይደል
- ያባትህና የናትህ ወገኖች ሲጣሉ ጥግህን ያዝ
- ያንዱ ቤት ካልጠፋ ያንዱ ቤት አይለማም
- ያናጢ ልጅ ጅብ በላው የላጭ ልጅ ቅማል ፈጀው
- ያኮራፊ ምሳው የነበረ እራት ይሆነዋል
- ያዛቆነ ሰይጣን ሳያቀስ አይቀርም
- ያየ ላውራ ቢል ያልሰማ አወራ
- ያገባሽ ይፈታሻል ወዮለት ለወለደሽ
- ያገርን ሰርዶ ያገር በሬ ያወጣዋል
- ያገርህ ዱር ፍራትን ያስወግዳል እንጂ ከሞት አያድንም
- ያጓኑት ደንጊያ ተመልሶ ራስን ይመታል
- ይሉኝ አይል ጸሐፊ ከሙሴ ይገድፋል
- ይሉኝታና መጠቀም አንድነት አይገኙም
- ይሉኝ አይል ውሽማ ዶሮ ሲጮህ ይማለላል
- ይመታሉ የሚጠሉ ይመስል ይስማሉ የሚወዱ ይመስል
- ይማሩኝ እያልክ ከምትታማበት አትገኝ
- ይሰበረኝ ይሰንጥረኝ የሚሉ የሰውን ልብ ሊሰብሩ
- ደልድል ዕድልህ እንዳይጐድል

## <u>ደ - ዱ - ዲ- ዳ - ዴ - ድ - ዶ</u>

- ደኃና ሹም ተሟግቶ ደንጊያና ቅል ተማትቶ የማይሆን ነው ከቶ። በአመዱ ንጉሥ በዘውዱ
- ደኃ ካልዞረ ዶሮ ካልጫረ (ማን ያበላው ነበረ)
- ደኃን ካስለቀሱ በሥላሴ ዘንድ ይወቀሱ
- ደሃ ተበድሎ ማሩኝ ይላል ቶሎ
- ደመናን የጨበጠ ሰማይ የቧጠጠ (የለም)
- ደሞዙ ሥንዴ ሥራው የምን ግዴ
- ደመወዝ ያጣ ሎሌ ሥራው የምን ግዴ
- ደመወዝ ያጣ ሎሌ ይኮበልላል በሐምሌ
- ይርስሁ ልጄ ፈላሁ ጠጅ
- ደረቴን ሲያመኝ እግሬን አገመኝ
- ዶሮ በልቶ ከስብና ጐመን በልቶ በጤና
- ደስታና መከራ ቀኛን ግራ (ናቸው)
- ደብተራ የዘኬ ጐተራ ዘኬውን ሲቁጥር አነቀው ነብር
- ደንጊያን ለረገጠ ፍሊጋ የለው ውኃን ለጠጣ ሽታ የለው
- ደወል ላንበሳ ባማረላት ታድያ ማን ይሰርለት
- ደግ ነገር ሳያልቅ ክፉ መናገር
- ዱባና ቅል አብሮ ይበቅል አበላሉ እየቅል
- ዱባ ባገሩ ጋር ያህላል አሉ
- ዲንጋይ ላይ ተቀማጭ የባለጌ ተለጣጭ
- ዲያቆን ከዘፈነ ፍየል ከቀዘነ (መዳኛም የለው)
- ዳባ ራሱ ስለት ድጉሱ። ዳቦ በገና ቡና በጀበና
- ዳቦ ሲበሉ ልብ ልቡን ዳገት ሲወጡ ጥግ - ጥጉን
- ዳቦ ያለ ቅርፊት ጠላ ያለ ምርጊት
- ዳኛ ሳለ ተናገር ውሃ ሲጠራ ተሻገር
- ዳኛ ይመረምራል ጣዝማ ይሰረስራል
- ዳኛ ቢያገድል በዳኛ አህያ ቢያጋድል በመጫኛ
- ዳኛ ምን ያደላ ከተረታው ሊበላ
- ዳኛን ቢንቁ የተያዘ እህልን ይወቁ
- ዳገት እርሚ ሜዳ ወንድሚ
- ዳኞች ከመረመሩ ይናገራል ምድሩ (ይገኛል ነገሩ)

- ዳኛ የወል ምሰሶ የማኸል። ዳኛ ያደላበት እሳት የበላበት
- ዳኛ ያፈሰሱለት ፈረስ የከሰከሱለት
- ዳኛ የፈረደው ስለት የቀደደው
- ድኃ ሲቆጣ ከንፈሩ ያብጣል መንገዱ ያሠልጣል
- ድኃና እመቤት እልፍኝና ማድ ቤት
- ድል በመታደል ሙያ በመጋደል
- ድመት መንኰሳ አመሏን አትረሳ
- ድሪቶ ከነ ቅማሉ መጥፎ ሰው ከነ አመሉ ወድያ በሉ
- ድኻ ያልፍልኛል ይላል ጌታ ቀኑን ይቁጥራል
- ድኻ ውኃውን ጠጥቶ እሳቱን ይሞቃል ሃብታም ስለገንዘቡ ይጨነቃል። ድንኳን ገልጦ ዙፋንን ረግጦ
- ድኻ ተበድሎ ራሱ ይታረቃል ሃብታም በድሎ ተመልሶ ይስቃል። ድር ቢያብር አንበሳ ያስር
- ዶር ከጋጥ በሬ ከቆጥ። ዶሮና ቀበሮ ተገናኝተው ከጓሮ
- ዶሮ ከጮኸ የለም ሌት ከቡሄ ወድያ የለም ክረምት
- ዶሮ ከጮኸ ሌት የለም ከደብረ ታቦር ወድያ ክረምት የለም። ዶሮ ሲሉ ሰምታ ሞተች እጢስ ገብታ
- ዶሮን ሲደልሏት በመጫኛ ጣሏት።
- ዶሮ ጭራጭራ አወጣች ማረጃዋን ካራ

## ስድ ምሳሌ

- ደም ተበከለህ ዝምብን አትጥላ። ደወል እንደጧቱ ትጮሃለች። ደጃቸውን ከፍተው ሰውን ሌባ ይላሉ
- ዱጨት ባመድ ይስቃል። ዱላ ይዞ ሌባን መጠየቅ
- ደፋርና ጭስ መውጫ አያጣም
- ድሃ በሕልሙ ቅቤ ባይጠጣ እስከ በፈጀው
- ድምቢጥ እንደ አቅሟ በብዕር ትታገማለች
- ድምፅና ቍንጫ ባዶ ቤት ይወዳል
- ድምፅና ቍንጫ ባዶ ቤት ይወዳል
- ዶሮ ብትታመም በግ አረዱላት
- ድሮ በልጅዋ አንጀት ትጫወታለች። ዶሮ በጋን
- ዶሮ እቤት ውላ ዝናም ትመታለች

## ጀ - ጅ

- ጀምሮ የማይፈጽም ፈጭቶ የማያልም
- ጀግና የሚታሰው ወይም ከሞተ ወይም ከተለየ በኋላ ነው። ጀማሪ ይጥፉ ሰካራም ይትፉ
- ጅራቷ ታደርሰኝ ከናቷ። ጅብን ሊወጉ ከአህያ ይጠጉ
- ጅብ እንዳገሩ ይጮሃል የደላው ሙቅ ያኝሃል
- ጅብ ታኰተኰተ ሰው ከተከተ
- ጅራፍ እርሱው ይገርፍ እርሱው ይለፍልፍ
- ጅራፍ እርሱው ይገርፍ እርሱው ይለፍልፍ
- ጅራፍ መትቶ ያለቅሳል ባለጸጋ በድሎ ተመልሶ ይወቅሳል
- ጅራትና ሐሜት በስተ ኋላ ነው። ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ
- ጅብ እንደ ጉልበቱ ልብ የለውም
- ጅብና እህል ሳይታዋወቁ ይኖራሉ
- ጅብ ኪበላህ ጅቡን በልተህ ተቀደስ
- ጀሮ በላ ሆድ ጦሙን አደረ
- ጀሮ የቀደሞዎቹ እኩያ ነው።

## ገ - ጉ - ጊ - ጋ - ጌ - ግ - ጎ - ጓ

- ገበሬ አከባሪውን፥ ባለጌ መካሪውን (ይጠላል)
- ገበሬ አቆጣጥረኝ ወታደር አወራውረኝ
- ገበጣ ላዋቂ ወሬ ለጠያቂ ዋዛ ፈዛዛ ለሳቂ
- ገባር ያህያ ግምባር። ገባ - ወጣ ነገር ያመጣ
- ገብሱ የሚደርሰው ለፍልሰታ እኔ የምሞተው ዛሬ ማታ
- ገርና ልል ሙዳይና አገልግል። ገበሬ በንጉሥ መበለት በቁስ። ገንዘብ ካለ በሰማይ መንገድ አለ
- ገንዘብ ከእጅ ከወጣ ይመጣል ይዞ ጣጣ
- ገንዘብ ያልያዘ መንገደኛ አይፈራም ቀማኛ
- ገንዘብ የጠፋበት ብዙ ኃጢአት አለበት
- ገንዘቤ አትውጪ ከቤቱ ታጣይኛለሽ ከጐረቤቱ
- ገዝቶ የማይቆጣ አጥቦ የማያነጣ
- ገንፎ ለጉንፋን ይበጃል ወዲህም ለሆድ ይበጃል

- ጉም ተራራን ያለብሳል ሹም ለሹም ያወርሳል
- ጉም ሲለቅ የታባትህ ትገባ አንተ ሌባ!!
- ጉድና ድንቅ አለ አንድ ጊዜም አይደምቅ
- ጊዜ የሰጠው ቅል ደንጊያን ይሰበራል
- ጊዜ የሌለው የለም ግን ከዕድሉ የሚያልፍ የለም
- ጋለሞታና ጌታ ደጅ የጠኑ ለታ። ጋሻ ድሮ ቀረሻ
- ጋሻ ተንግቡ ነገር ከግቡ። ጌታ ያዝዛል ውኃ ያነዛል
- ጌታ ለሎሌው ነጋዴ ለአሞሌው (ያስባል)
- ጌታ ሲወድ ማን ይጠላል ጌታ ሲሰጥ ማን ይከለክላል
- ጌታና ሎሌ ተጣልተው ዱባና ቅል ተማተው ኤረ አይ መስልም ተው!! ጌታ ሁን እንዳሻህ ትሆን
- ጌታ ባወቀው ይፈርዳል ሰው ባላወቀው ይጐዳል
- ግመል ምን ተጭነሃል? ሽመል ምን ያወዛውዝሃል? አመል
- ግም ለግም አብረህ አዝግም። ግርግርታ የሌቦች ደስታ
- ግፍ ባገር ሲመላ እርስ በርስ ያበላ
- ግንቦት ቢዳምን የሚመዝን ይመስላል አሮጌ ቢፎክር የሚወጋ ይመስላል። ግንድ ለሺ አይከብድ
- ግፍ ባገር ሲናኝ ኩበት ይጠልቃል ደንጊያ ይዋኛል
- ግፍስ በባሕር ይመላል ዓሣ ዓሣውን ይባላል
- ግዝት ብዝት ዎፈ ገዝት
- ጐመን ባወጣው ነፍስ አትኩራ ገብስ
- ጐመን ጠነዛ ሴት ከበዛ። ጐራዴና ምስጥ ውስጥ ለውስጥ
- ጐልማሳ ሲታጠቅ ከደረቱ ሲሮጥ ከጉልበቱ
- ጐልማሳ ካለበት ከብት አይሰረቅ ሽማግሌ ካለበት ነገር አይነጠቅ። ጐራዴህ ጐመዳም ሚስትህ አመዳም
- ጐረቤት ይሆናል ጠላት ያችን ሴት አትዘጊ ቢሏት
- ጐረምሳ እንደ በላህ አንሣ። ጐኑ የኔ ቀኑ ሰኔ
- ጐራዴ ለወንበዴ ሱቅ ለነጋዴ። ጐርፍ ሲወስድ እያሳሳቀ ተንኰለኛ ሰው ሲጐዳ እየተራራቀ (ነው)
- ጐበዝ ፊት ሰማይ ሰማይ ያያል ኋላ ምድር ምድር ያያል
- ጐባጣን ይቀብሩ እንደ ምግባሩ። ጐሽ ጠመድኩ ይሆናል ብየ ፈትቸ ሰደድኩ አይሆንም ብየ
- ጕንደር ወታ ምን ይዞ መጣ። ጕንደር ወጣህ ምን አመጣህ
- ጐጃም ሲያምጥ በጌምድር በፍልጥ
- ጐድሎ ነበር መላ ሞልቶ ነበር ፈላ
- ጐጆ ወጭ ሙሽራ በገፍ ወጥ ትሠራ
- ጓሳና ድንግል አላንድ ጊዜ አይበቅል
- ጕልበት አለኝ የዝሆን አፍ አለኝ ላንተ የሚሆን
- ጕልበት የሌለው ወንበዴ ትርፍ የሌለው ነጋዴ
- ጕትቻ ለጆሮ እልፍኝ ለወይዘሮ
- ጕጕት ብትጠቃ እርኩም ሆነ ጠበቃ
- ጕትቻ ለጆሮ ትንሽ ትመስላለች ዘፈ ጐበዝ ትቁርጣለች

## ስድ ምሳሌ

- ገላጋይ አጥቼ ግልገሌን በላኋት። ገበያ እንደሰጠህ እንጂ እናንህ እንደላከችህ አይሆንም።
- ገበያ የሚሰጥህ እናት አትሰጥም
- ገዳይ ቢያረፋፍድ ተገዳይ ይገሰግሳል
- ገጣጣ ሲሞት የሳቀ ይመለሳል። ጊዜ ያለው ጊዜ አይጠብቅ
- ጊዜ ወርቅ ነው ግን ኃላፊ ነው። ጉቦና ሌባ በር አይወዱም
- ጉድ ለባለ ቤቱ ያንገት ልብስ ነው
- ጉንፋን የተያዘና የፍየል ይዞ የተደበቀ ሳይገለጥ አይቀርም
- ጋን ሲለቀለቅ ማድጋን ይመስላል
- ጋኖች አለቁና ምንቸቶች ጋን ሆኑ
- ጋን ቢያሚጥጡት ምንቸት ይመላል
- ጌታዋን ያመነች ውሻ ፍሪዳ ሲታረድ ወንዝ ትወርዳለች
- ግዛኝ ብለው ለመሸጥ አሰበኝ
- ጉዳይ አሳልፍ እንድትታማ አሮጌሁን ልትፎክር ሙት ልትመሰንገ። ጕፋያን ሲበሉ ስብ ይቀላውጡ
- ጕሮሮ የሚውጠውን እጅ ይመጥነዋል
- ጕንዳን ቤቱን ይመራል። ጕድጓድ በራሱ አፈር አይሞላም

## ጠ - ጡ - ጣ - ጥ - ጪ - ጬ - ጫ - ጭ - ጮ

- ጠላኝ ማለት ያስጠላ ልግደል ማለት ያስገድላል
- ጠላትን በጦር አባትን መጦር። ጠላት ይቀባል ጥላት
- ጠባ በማቶት እንጀራ በሌማት። ጠላ ካሠር ነገር ካገር
- ጠላ ያለ አተላ ጠጅ ያለ አምቡላ። ጥዋት ሽሮ ማታ ዶሮ
- ጠላት በጥርስ ሲገኛ እባክህ አታስጐምጀኝ
- ጠላትን ለማግኘት ሲጐራጐሩ በወዳጅ ይጀምሩ
- ጠላው ሳይገባ ማቶቱ ቀንዱ ሳይገባ ኸሯቱ
- ጠመንጃ ያለ ጥይት ዱላ ወንድ ያለ ሴት ቀውላላ
- ጠርቦ ለደጁ ፈርዶ ለልጁ። ጠበቃና ቅል ባጠገብ ይውል
- ጠብ ተጀመረ አንበሳ ላምን ሰበረ
- ጠብ ተጀመረ ያ ልጅሽ አለ ልጄ ሲል የነበረ
- ጠባ ለኪዳን መሸ ለቊርባን
- ጠብ ባለበት ቤት ዶሮ ትሞት
- ጠጅ ለዋጭ ልጅ መጫወቻው ለድኻ ልጅ መማቻው
- ጠንቋይ ለራሱ አያውቅ ላዋይ
- ጠጅ ይሻላል በመጠኑ የጭዋ ልጅ ይበልጣል በቀጭኑ
- ጠጅ ለወረት ወዳጅ ለችግር ለት
- ጠገብሁ ያለውን ብላ አትበለው ፈራሁ ያለውን ድፈር አትበለው። ጣል በደጅ እስር በፍንጅ
- ጢም የሌለው መምር ዓፀድ የሌለው ደብር አምሮም ማያምር። ጢምህን እጠላለሁ መሳምህን እወዳለሁ
- ጣዝማ ሰርሳሪ ዳኛ መርማሪ
- ጣዝማ ይሰረስራል ዳኛ ይመረምራል
- ጤና ከሃብት ወፍጮ ከከብት አይቆጠርም
- ጤፍ አይቆላ የጭዋ ልጅ አይጠላ
- ጤፍ ቢሰኩ ሰማይን ቢያከኩ አይገኝም ልኩ
- ጥምድ እንደ በሬ ቅንት እንደ ገበሬ
- ጥርስና ከፍነር ተደጋግፎ ያምር
- ጥቂት ሥጋ እንደ መርፌ ትወጋ
- ጥቂት ያላት ዕረፍት (እንቅልፍ) የላት
- ጥምባሆ ለምን ይበጃል ያስተዋውቃል
- ጥሩ ድህነት ጥሩ ነፃነት ጥሩ ሀብት መልካም ርስት
- ጥበብ ያስከብራል ሃብት ያስጨፍራል
- ጥንቱ የተውሶ ያውም ጠፋ ጨርሶ
- ጥዋት ከበላተኛ ማታ ከጦመኛ እንደ ሽመላ በ፪ ይበላ
- ጥጃ ጠባ ከሆድ ገባ። ጥዋፍ ያበራል ከሳሽ ይመራል
- ጥጃ ቢሳሳት ከናቱ ነገር ቢሳሳት ከጧቱ
- ጥጃ ሣር ይበላል ቤቱ ዕዳ ይሞላል
- ጥጃ ቢሮጥ በሜዳ ውኃ ቢሄድ በጓድጓዳ
- ጥጋብ ቢያምርህ ጠላ መግዛት ቢያምርህ ችላ
- ጥጋብን ወደኛ በል ጥጋብን ወድያ በል
- ጦር ሲመጣ ዛቢያ ቆረጣ ፍርሃት ሲመጣ
- ጦም ከማደር ከዳቦው መቀርቀር
- ጦር ለወረወረ ጐራዴ ለሰነዘረ (መሬት ለገበረ)
- ጦር እንደ ወረወሩት ጐራዴ እንደ ሰነዘሩት
- ጦጣ ባለቤቱን ታስወጣ። ጦጣና ዝንጅሮ ተኮላና ቀበሮ
- ጨው ሲበዛ ያቅራል። በርበሬ ሲበዛ ይመራል
- ጨካኝ አልሞተ ፈሪም አልሞተ አጓጒለኛ ሞተ
- ጨዋታ ለሳቂ ወሬ ለጠያቂ። ጨዋ አይነቀፍ እሳት አይቀፍ
- ጬኸት ለአሞራ ሙብል ለቁራ
- ጫን ያለው ኮረቻውን ለምን ያለው ስልቻውን
- ጭምት ሲሞት ልቡን ንጉሥ ሲሞት ግምቡን
- ጮማ በልቶ ከብስና ጐመን በልቶ በጤና

## ስድ ምሳሌ

- ጠላና ጐተና በአንድ ቀን አይደርስም
- ጠባቂ ያላት በግ ላቷ እደጅ ያድራል
- ጠላ ባለቤቱን አያውቅም ጠላት የሌለው ወዳጅ አያሻውም
- ጠንቋይ ባያሳምን ያጠራጥራል። ጠንቋይ አባይ ቤት ያስፈታል። ጠጉራም ውሻ አለ ሲሉት ይሞታል

- ጣይ ያየው ሰው ሳያየው አይቀርም
- ጣይ ብልጭ ዎፍ ጭጭ ሲል። ጥይት የፈራትን ትወጋለች
- ጥቅልል ላለ ጠጉር ዘርዘር ያለ ሚዶ
- ጥኑ ወዳጅ ጥሩ ጠላት ጥሩ ጠላት ጥኑ ወዳጅ ይሆናል
- ጥላት ሸኚ ቤት አይገቡም። ጥጋቡን የማይችል አህያ ነው
- ጥጥና ሹም እያደረ ይከዳል። ጥርስና ከፍነር አብሮ ይደማል
- ጨው የሌለው ምግብና ሰው የሌለው ሰው አንድ ነው
- ጨቅጭቃ ሚስትና የሚያፈስ ቤት ፩ ናችው
- ጫማ ምንም ወርቅ ቢሆን ከአገር በታች ነው
- ጫን ካለ ጫን ይፈጃል። ጮሌ ሲያርጅ መጋኛ ይሆናል
- ጨካኝና ጭስ መውጫ አያጣም
- ጳጉሜን ሲወልስ ገበሬ ጐተራህን አብስ
- ፈሪ በገዛ ጠቡ ገላጋይ ይሆናል
- ፊት ከወጣ ጆሮ ኋላ የበቀለ ቀንድ በለጠ

## ፈ - ፊ - ፎ - ፍ

- ፈሪ ለናቱ ጀግና ለጀግንነቱ
- ፈርተው ደንጊያን ቢወረውሩ ጅብ ወጣ ከዱሩ
- ፈረስ ጥሎ ይደነግጣል አህያ (በቅሎ) ጥሎ ይረግጣል
- ፈሪ ፈርቶ እጉድባ ቢተኛ ጀሮውን በላው ያይጥ ቀበኛ
- ፈጅቶ ከሚያጠግበኝ እስኪበርድ ይራበኝ
- ፈጥኖ መስጠት ቶሎ ለመስጠት
- ፈጣሪ የሚያህል ጌታ ርስትን (ገነትን) ያህል ቦታ
- ፊት ጀሮ ይፈጠራል ኋላ ቀንድ ይበቅላል
- ፊተኛው ወዳጅህን በምን ቀበርከው በሻሽ ምነው? ኋለኛ እንደ ይሸሽ። ፊንጣ ብትቆጣ አንድ እግሯን ታጣ
- ፍርድ ለተቀማ ወጥ ለቀላዋጭ
- ፍቅርህን የፈለገ ልጅህን ጥልህን የፈለገ የላም ልጅህን
- ፍቅር ይሠራል ዕውቀት ያስከብራል ጥበብ ያኰራል
- ፍርድ አያውቅ ዳኛ ተገን አያውቅ እረኛ
- ፍርድና ፍትፍት ወደ ፊት። ፍረድ ለነፍስህ ብላ ለከርሥህ
- ፍርድ እንደ አሉላ ጽድቅ እንደ ላሊበላ
- ፍርድ ጐደለ ድሃ ተበደለ (የሚል ንጉሥ አይታጣ)
- ፍየል የለኝ ከነምር ምን አጣላኝ
- ፍየል ከመድረስዋ ቅጠል መበጠስዋ
- ፍየል መንታ ትውልድና አንዱ ለወናፍ ፩ዱ ለመጻፍ
- ፍየልና ቀበሮ ምጥማጥና ደሮ
- ፍጥም ያውላል አቧራ ያስላል
- ፍጥም ያቆማል ዕርቅ ያጠቃልላል
- ፍጥም አያናግር የጐናፍ ሙላት አያሻግር
- ፍቅር ሲጸና ቆሎ ያጓርሳም

## ጸ - ጺ - ጽ - ፅ

- ጸሎት ያለ ፍቅር ሃይማኖት ያለ ግብር (አረባም)
- ጸሎት ከፍቅር ሃይማኖት ከግብር (ይበጃል)
- ጸሎት በጽሞና ነገር በደመና
- ጻድቃን ባልተቃጠሩበት ይገናኖሉ ኃጥአን በተቃጠሩበት ይተጣጣሉ። ጽድቅ ለመንኳሸ ቀኝ ለከሳሽ
- ጽድቅ እንደ ላሊበላ ዕድሜ እንደ ማቱሳላ (ይስጥህ)
- ጽዋ በተርታ ሥጋ በገበታ
- ጽፈት በብራና ዘፈን በበገና



# ስለደራሲው በጥቂቱ

የሃይማኖት ፣ የፍልስፍና ፣ የምርምር መጻሕፍት ደራሲው ሊቀ መዘምራን ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ ከአቶ ዕቁበ ጊዮርጊስ ወልደ ኢየሱስና ከወ/ሮ ወለተ ትንሣኤ ኃይለ ሚካኤል በኤርትራ ክፍለ ሀገር በሐማሴን አውራጃ በለጎጭዋ ወረዳ ልዩ ስሙ ክትሞ ውሊዕ በተባለ መንደር መስከረም ፩ ቀን ፲፱፻፲፫ ዓ.ም ተወለዱ።

በ፲፪ ዓመታቸው በትምህርት ተኮትኩተው እንዲያድጉላቸው ወላጆቻቸው እምኒ ጸሊም ከነበሩት የኔታ እንድርያስ ዓሰቡ ከተባሉ መምህር ዘንድ ልከዋቸው ፊደል ቆጥረው የቃል ትምህርትንና ቁም ጽሕፈትን ተማሩ። ከዚያም ወደ ትግራይ ክፍለ ሀገር እንደርታ አውራጃ ደብረ ኃይል ገዳም ገብተው ስመ ጥር ከሆኑት ከመምህር ገብረ ሕይወት ጎምሎ ቅኔ ከነአገባቡ ተምረው በመምህርነት ተመርቀዋል። ከየኔታ ፈለቀ አቋቋምን ከተማሩ በኋላ ወደ ጎንደር ክፍለ ሀገር በመሻገር በደብረ ታቦር አውራጃና በዚሁ አካባቢ የጎንደርን አቋቋም የጸናጽሉን አወራረድና ይትብሃሉን አጠናቀው ከዚያም የትምህርት ፍላጎታቸው ስላልተሟላላቸው እንደገና የቅዱሳት መጻሕፍትን ትርጓሜ ለመማር በ፲፱፻፵፩ ዓ.ም ሸዋ ክፍለ ሀገር አዲስ አበባ መጥተው በዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ የመምህራንና የቀሳውስት ማሠልጠኛ ገብተው ከአለቃ ኀሩይ መጻሕፍተ ሊቃውንትን፥ አቡሻሕርን /ባሕረ ሐሳብ/ ተምረዋል። ከታወቁት ሊቅ ከዶክተር አለቃ አየለ ዓለሙ የመጻሕፍተ ሐዲሳት ትርጓሜን ጠንቅቀዋል።

የደራሲው ሥራዎች

1ኛ፡- መክሥተ ልሳን ዘሕፃናት
2ኛ፡- አንጋረ ፈላስፋ
3ኛ፡- ሰዓታት ምስለ ባሕረ ሐሳብ
4ኛ፡- ሥነ ፍጥረትና አምስቱ አዕማደ ምሥጢር
5ኛ፡- መድበል አምኅ ሰላም
6ኛ፡- ጥንታዊ ምሳሌ /በአማርኛ/
7ኛ፡- ጥንታዊ ምሳሌ /በትግርኛ/
8ኛ፡- መዝገበ ቃላት /በአማርኛ/
9ኛ፡- መርሐ ጽድቅ ባህለ ሃይማኖት ሲሆኑ በርካታ ያልታተሙ ጽሑፎች አሏቸው። ከእነርሱም መካከል፡-
  1ኛ፡- መዝገበ ቃላት ግእዝና አማርኛ
  2ኛ፡- ተስእሎተ አንጢያኮስ ውስጣዊ አትናሲስ /በአማርኛ/
  3ኛ፡- ዛንታ አበውና ተረታ - ተረት /በትግርኛ/
  4ኛ፡- መዝገበ ቃላት /በትግርኛ/
  5ኛ፡- ፊሳልጎስ ፈላስፋ /በአማርኛ/
  6ኛ፡- ፪. የኢትዮጵያ ሊቃውንት ቅኔ /በግእዝ/
  7ኛ፡- ፫ አስተዳደግ የሚሉ መጻሕፍት ናቸው።

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY